ገም ፤ በቃሌም ፡ ደስ ፡ አሰኘዋ
ለሁ ።

ወአንሰ ፡ አትፈሣሕ ፡ በእግዚአብሔር
ፅን ፡ ፫ ፡ ፲፰ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እ
ምኜ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

ፀፍ ፡ ወየ·ነልቁ ፡ ኃጥአን ፡ እምድር ።

ኃጥአን ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ባቢሎ
ናውያን ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ተለይ
ተው ፡ አንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
ይጠፋሉ ፡ ይጥፉ ።

ወወግዕያንሂ ፡ ኢይሄልዉ ፡ እንከ ።

ዐመፀኞችም ፡ ቢኖሩ ፡ ቢኖሩ ፡
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቀድ
ሞ ፡ የኖሩትን ፡ ያህል ፡ አይኖሩም ።

ትባርኮ ፡ ነፍስየ፡ለእግዚአብሔር ፡ ቍ፩።

ሰውነቴ ፡ አንድም ፡ ልቡናዬ ፡
እግዚአብሔርን ታመሰግነዋለች ።

መዝሙር ፡ ፻፱ ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለምን ፡
አሳልፎ ፡ የሚኖር ፤ አንድም ፡ ያህ ፡
ይላል ፡ በዓረብ ፡ ስብሐት ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፩ ፣ ግነዩ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወጸውዑ፡ስሞ
ስሙን ፡ እየጠራችሁ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ የምስጋና ፡ የሃይማ
ኖት ፡ አገዛዝ ፡ ተገዙ ።

ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።

ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ ያደረ
ረገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥ
ራውን ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፤
አስተምሯቸው ።

፪ ፣ ስብሑ ፡ ወዘምሩ ፡ ሎቱ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአ
ምልኮት ፡ እሱን ፡ አመስግኑት ፡
ለስሙም ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።

ወንግሩ ፡ ሡሙ ፡ መንክሮ ። ኢሳ ፡ ፲፪ ፡
፬ ። ፳፯ ፡ ፲፫ ።

ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ንገሩ ፤
አስተምሩ ።

፫ ፣ ውትከብሩ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ስሙ
ን ፡ በማመስገን ፡ (ለስሙ) ፡ ለማ
መስገን ፡ ትከበራላችሁ ።

ለይትፈሣሕ ፡ ልብ ፡ ዘየኀሥ ፡ ለእግዚ
አብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአም
ልኮ ፡ የሚሻው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ደስ ፡ ይለዋል ፤ ደስ ፡ ይበለው ።

፬ ፣ ኀሥሡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወትጸንዑ።

እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአም

ልኮት ፡ በጸሎት ፡ ሹት ፤ እን
ዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እሱን ፡
በማመን ፡ በማምለክ ፡ ፀንታችሁ ፡
ትኖራላችሁ ።

ወጎሙ ፡ ገጾ ፡ በሰሉ ፡ ጊዜ ።

ገጸ ፡ ምሕረት ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱንም ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሹ ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፮ ።

፭ ፡ ወተዘከሩ ፡ መንክር ፡ ዘገብረ ።

ያደረገውን ፡ ተአምራቱን ፡ አስ
ባችሁ ፡

ተአምሪሁ ፡ ወሶንኔ ፡ አፉሁ ።

ተአምራቱን ፡ ባንደበቱ ፡ የሠራ
ው ፡ ሕጉን ፡ አስባችሁ ፡

፮ ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ አግብርቲሁ ።

ማን ፡ ማን ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡
እኅሌ ፡ እኅሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡
ባለሚሎቹ ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡
መላችሁ ።

፮ ፡ ወደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ኅሩያኒሁ ።

ለክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ የተመ
ረጣችሁ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡
መላችሁ ።

ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በ
ዋቂ ፡ ነውና ።

ውስተ ፡ ኩሉ ፡ ምድር ፡ ሶንኔሁ ። መዝ ፡
፻፱ ፡ ፯፪ ።

ግዛቱ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ምሉዕ ፡
ነው ።

፰ ፡ ወተዘከረ ፡ ሥርዐቶ ፡ ዘለዓለም ።

ተዘከረ ፡ ዘለዓለም ፡ ሥርዓቶ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ ይላል ፤ ለዘላለም ፡ የሚ
ኖር ሥርዓቱን ፡ ሕጉን ፡ አሰበ ፡
ፈጸመ ።

ቃሎ ፡ ዘአዘዘ ፡ ለ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ትውልድ ።

ሥርዓቶ ፡ ያለውን ፡ ቃሎ ፡ ብሎ ፡
ገለጸው ፤ ለሺሕ ፡ ትውልድ ፡
የሠራውን ፡ ሕጉን ፡ አስቦ ፡ ሺሕ ፡
ትውልድ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፡ በፍ
ጹም ፡ ተናገረው ። እስመ ፡ አነ ፡
እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘእ
ገብር ፡ ምሕረተ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅ
ሩኒ ፡ እስከ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ትውል
ልድ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አምላክ ፡
ቀናዒ ፡ ዘእፈዲ ፡ ኃጢአተ ፡ አ
በው ፡ ላዕለ ፡ ውሉድ ፡ እስከ ፡
ሣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ትውልድ ፡
ለእለ ፡ ይጸልውኒ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡
፲፯ ፡ ፩ ። ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፭ - ፯ ።

፱ ፡ ዘሠርዐ ፡ ለአብርሃም ።

ለአብርሃም ፡ የሠራለት ፡ ሥርዓቱ
ን ፤ አንድም ፡ ለአብርሃም ፡ ሥር
ዓቱን ፡ የሠራለት ፡ እግዚአብሔር ፡
አሰበ ። አንድም ፡ ያዘዘለት ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ። ፪ኛ
ወመሐለ ፡ ለይስሐቅ ። ። ፶፩ ፡ ፶፩ ፡ ፮

ለይስሐቅ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ፡
አሰበ ። አንድም ፡ ለይስሐቅ ፡
የማለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰበ ።

አንድም ፡ የማለ ፡ እግዚ አብ ሔር ፡ ነው ።

፲ ፡ መአቀመ ፡ ስምኣ ፡ ለያዕቆብ ።

ለያዕቆብ ፡ ያፀናለት ፡ አምልኮ ቱን ፡ አሰበ ። አንድም ፡ ለያዕቆብ ፡ አምልኩቱን ፡ ያፀናለት ፡ እግዚ አብሔር ፡ አሰበ ። ለያዕቆብ ፡ አም ልኩቱን ፡ ያፀናለት ፡ እግ ዚ አብ ሔር ፡ ነው ።

ወለእስራኤልኒ ፡ ኪዳኖ ፡ ዘለዓለም ።

ያዕቆብ ፡ ያለውን ፡ እስራኤል ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ለእስራኤልም ፡ የማለውን፡ለዘላለም፡ፀንቶ፡የሚኖር ፡ መሐላውን ፡ አሰበ ። ዘፍ፡ ፴፭፡ ፲፡፲፪ ።

፲፩ ፡ ወይቤሎ ፡ ለክ ፡ እሁበክ ፡ ምድረ ፡ ከነዓን ።

ምድረ ፡ ከነዓንን ፡ ወርዷን ፡ ቁመ ቷን ፡ ለክ ፡ ወለዘርዕክ ፡ እሁበ ክሃ ፡ ብሎ ፡ የማለውን ፡ መሐላ ውን ፡ አስቦ ፡ አንድም ፡ እሰጥ ሃለሁ ፡ አለው ፡ ብለህ ፡ እሠር ።

ትኩንክሙ ፡ ሐብለ ፡ ርስትክሙ ።

ርስተ ፡ ሐብልክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የረዘመውን ፡ በጠፍር ፡ ያጠረውን ፡ በደግር ፡ ትካፈሉ ፡ ዘንድ ፡ ር ስት ፡ ልትሆናችሁ ። ዘፍ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።

፲፪ ፡ እንዘ ፡ ውኑዳን ፡ ጥቂ ፡ እሙንቱ ።

እሊህ ፡ ፈጽመው ፡ ጥቂት ፡ ሳሉ ፡ ይህን ፡ ተስፋውን ፡ ነገራቸው ።

ወፈላስያን ፡ ውስቴታ ።

ለከነዓን ፡ ነው ፡ በከነዓንም ፡ ስደ ተኞች፡ መፃተኞች ፡ ሁነው ፡ ሳሉ ።

፲፫ ፡ ወነለፉ ፡ እምሕዝብ ፡ ውስተ፡ሕዝብ

ካንዱ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ አንዱ፡ ነገድ ፡ ሄዱ ።

፲፬ ፡ ወእምነገሥት፡ውስተ ፡ ካልእ፡ሕዝብ

ካንዱም ፡ ንጉሥ ፡ ወዳንዱ ፡ ን ጉሥ ፡ ሄዱ ። አንድም ፡ ውስተ ፡ ነገሥተ ፡ ካልዕ ፡ ሕዝብ ፡ ይላል ፡ ካንዱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዳ ንዱ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ሄዱ ።

ወአኃደገ ፡ ይሥሐጦሙ ፡ ሰብአ ።

ሰው ፡ ይጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ፀቡ ን ፡ አልተወባቸውም ። አንድም ፡ አኃደገ ፡ ሰብአ ፡ ይሥሐጦሙ ፡ ይጣሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ አላሠለጠነባቸውም ።

ወገሠፀ ፡ ነገሥተ ፡ በእንቲአሆሙ ።

በሳቸው ፡ ምክንያት ፡ ስለሳቸው ፡ ነገሥታቱን ፡ ገሠፀላቸው ፡ እን ጂ ፡ አኃደገ ፡ ሰብአ ።

፲፭ ፡ ወኢትግሥሡ ፡ መሢሐንየ ።

ቅቡዓንየ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቀብቼ ፡ ያነገሥኋቸው ፡ ነገሥታቱን ፡ አት ጉዷቸው ፤ መቼ ፡ ተቀባና ፡ እን ዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ቅቡዓኑን ፡ ስለ ፡ ወለደ ፡ ብሎ ። አንድም ፡ ቅብር ፡

በድነከ ፡ ጎበ ፡ ዘፈቀድከ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ እምታ ፡ ሕዝ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ብለ ውታልና ። ዘፍ ፡ ፳ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪ ፡ ፯ ።

ወኢታኅሥሙ ፡ ዲበ ፡ ነቢያትየ ።

በነቢያትም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታ ምጡባቸው ፡ ብሎ ፡ ገሠፀላቸው ፡ እንጂ ፡ ኢኃደገ ፤ መቼ ፡ ነቢይ ፡ ተባለና ፡ ነቢያትየ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ነቢያትን ፡ ስለ ፡ ወለደ ፡ አንድም ፡ ፀውዕዎ ፡ ለእግዚአየ ፡ ይጸሊ ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ነቢይ ፡ ውእቱ ፡ ብላዋለችና ። ዘፍ ፡ ፳ ፡ ፯ ።(ታሪክ) ፡ አብርሃም ፡ በዘመኑ ፡ ረኀብ ፡ ሆነ ፡ ይልቁንም ፡ በከነዓን ፡ ፀንቷል ፤ ሚስቱን ፡ ሣራን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ተሰደደ ፤ ምድረ ፡ ግብፅ ፡ ሲደርሱ ፡ አእምር ፡ ከመ ፡ ሠናይተ ፡ ላህይ ፡ አንቲ ፡ ወእምከመ ፡ ርዕዩኪ ፡ ሰብአ ፡ ግብፅ ፡ ኪያየ ፡ ይቀትሉ ፡ ወኪያኪ ፡ ያሐይዉ ፡ ግበሪ ፡ ምሕረተ ፡ ምስሌየ ፡ ከመ ፡ እሕየው ፡ በዕብሬ ትኪ ፡ በሊዮሙ ፡ እኅቱ ፡ አነ ፡ ይላል ፤ እኔ ፡ እስካሁን ፡ ወጥቼ ፡ ወርጄ ፡ አገለገልኋችሁ ፡ እንግ ያዕ ፡ ወዲህ ፡ እላንተ ፡ ፈንታችሁን ፡ እኔን ፡ አገልግሉኝ ፤ አንቺን ፡ ሲሉ ፡ እንዳይጣሉኝ ፡ ምንሽ ፡ ነው ፡ ያሉሽ ፡ እንደሆነ ፡ እሱም ፡ ወንድሚ ፡ እኔም ፡ እኅቱ ፡ ነኝ ፡ በዪ ፡ አላት ፡ ከዚያ ፡ ሲወርዱ ፡ ሸማ ፡ አጣቦች ፡ አገኟቸው ፡ ያም ፡ ለኔ ፡ ትገባለች ፡ ያም ፡ ለኔ ፡ ትገባለች ፡ ብለው ፡ ተሻምተዋል ፡ አንድ ፡ ሕፅው ፡ ነበረ ፡ ይህችስ ፡ ለሁላችሁም ፡ አትገባም ፤ ለንጉሡ ፡ ትገባለች ፡ ብሎ ፡ ወሰዱ ፡ ለፈርዖን ፡ ሰጠው ፡ ምንህ ፡ ናት ፡ አለው ፡ እኅቴ ፡ ናት ፡ አለው ። እሷንም ፡ ምንሽ ፡ ነው ፡ አላት ፡ ወንድሚ ፡ ነው ፡ አለችው ፤ ከሱ ፡ ተቀብሎ ፡ ምግባቸውን ፡ መግቦ ፡ እሱን ፡ ከእንግዳ ፡ ቤት ፡ አሳድሩት ፡ አለ ፡ እሷን ፡ ከእልፍኝ ፡ አግብቶ ፡ ልድረስብሽ ፡ ቢል ፡ ንዑስ ፡ መሊሊቱ ፡ መከዳ ፡ ያህል ፡ አበጠ ፤ እጂ ፡ ሰለለ ፡ ነገሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ገልጸሽ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ፡ ብንፈራህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ እኮን ፡ ባሌ ፡ ነው ፡ አለችው ፤ ምን ፡ ይበጅኛል ፡ አላት ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ይጸልይልህ ፡ አለችው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስጠሩት ፡ ምነው ፡ እኅቴ ፡ ናት ፡ አላልከኝምን ፡ አለው ፡ አሕዛብ ፡ ዕኑዓን ፡ ናችሁና ፡ ብፈራህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሚስቴ ፡ ናት ፡ አለው ፤ ብትነግረኝ ፡ የኀልማሳ ፡ ሚስት ፡ እነሣ ፡ ነበርን ፡ አለው ፤ እሱም ፡ ወዲያው ፡ ጸልዮ ፡ አድኖታል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሱ ፡ ንዑስ ፡ መሊሊቱ ፡

መከዳ ፡ ያህል ፡ እንዳበጠ ፡ እጁ ፡ እንደ ፡ ሰለለ ፡ አስመስሎ ፡ ወርቅ ፡ አሠርቶ ፡ ሰጥቶታል ። እሳም ፡ አድለውኩ ፡ ለገጽኪ ፡ ፊትሽን ፡ ስላየሁ ፡ ብሎ ፡ ዐሥር ፡ ምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ለእጅዋ ፡ ለእግሯ ፡ አን ባር ፡ ሰጥቷታል ፡ ከአቢሜሌክም ፡ ቢሄዱ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተደርጓል ፡ ለሱም ፡ እንዲህ ፡ አድርጎለታል ፡ ለሳም ፡ ገረድ ፡ ደንገጥር ፡ ይሁ ኑሽ ፡ ብሎ ፡ አጋርንና ፡ ኬጡራን ፡ ሰጥቶ ፡ ሰድዷታል ። ዘፍ ፡ ፲፪ ፡ ፲ ። ፳ ፡ ፳ ። ፳ ፡ ፲፮ ።

፲፯ ፡ ወአምጽአ ፡ ረኀበ ፡ ለብሔር ።

ለሀገር ፡ ረኀብን ፡ አመጣ ፡ ይጠ ቅም ፡ ይመስል ፡ ለብሔር ፡ አለ ። አንድም ፡ አስቀድመው ፡ ተጠን ቅቀው ፡ የቄዩ ፡ ብዙ ፡ የተጠቀ ሙ ፡ አሉና ፡ አንድም ፡ በብሔር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በሀገር ፡ ረኀብን ፡ አመጣ ፡ ኩን ፡ ጠቢበ ፡ ለዕድ ውከ ፡ እንዲል ፡ ማቴ ።

ወአጥፍአ ፡ ዙሎ ፡ ኃይለ ፡ እክል ።

ዘመደ ፡ ዕክል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የህ ልን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ፡ አን ድም ፡ በቁመ ፡ የህሉን ፡ ኃይል ፡ አጠፋ ፡ ቢበሉትም ፡ ስልት ፡ ቀ ጠና ፡ ሁኖ ፡ አጥፍቷቸዋልና ፡ ወነሳኅክዎሙ ፡ እንዲል ።

፲፯ ፡ ፈነወ ፡ ብእሲ ፡ ቅድሜሆሙ ።

ከሳቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ዮሴፍን ፡ ላክ ፤ አሁን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረደ ፡ ብሎ ፡ የሚያመጣ ፡ ነውና ።

ተሠይጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ወኮነ ፡ ገብረ ።

ፈነወ ፡ ያለውን ፡ ተሠይጠ ፡ ብ እሴ ፡ ያለውን ፡ ዮሴፍ ፡ ብሎ ፡ አመጣው ፡ ዮሴፍ ፡ ተሸጠ ፡ በግ ብፅ ፡ ተገዢ ፡ ሁኖ ፡ ኖረ ።

፲፰ ፡ ወሐማ ፡ አገሪሁ ፡ በመዋቅሕት ።

እግሩ ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ታሥሮ ፡ ሠለሰለ ።

ወአምሠጠት ፡ ነፍሱ ፡ እምሐጺን ።

ሰውነቱ ፡ ከመታሠር ፡ አመለጠች።

፲፱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ቃሉ ።

አዘክረኒ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚአከ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ሳይ ደርስ ።

ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምከሮ ።

አመከሮ ፡ ይላል ፡ ቃለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ተፈታተነው ፡ ማለት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እንዲታሠር ፡ አደረገው ፤ አንድም ፡ (ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ቃሉ) ፡ አዘክረኒ ፡ በቅ ድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚአከ ፡ ያ ለው ፡ ቃሉ ፡ ከፈርዖን ፡ ሳይደርስ ፡ (ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምከሮ) ፡ የሁለቱን ፡ መኳንንት ፡ ሕልም ፡ እንዲፈታ ፡ አደረገው ፡ አንድም ፡ አዘክረኒ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚአከ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከፈር

ያን ፡ ሳይደርስ ፡ የንጉሡን ፡ ሕልም ፡ እንዲፈታ ፡ አደረገው ። ምነው ፡ የንጉሡን ፡ ሕልም ፡ የፈታው ፡ ኋላ ፡ አይደለምን ፡ በሉ ፡ የሁለቱን ፡ መኳንንት ፡ ሕልም ፡ በመፍታቱ ፡ ታውቋልና ። አንድም ፡ ፈርዖን ፡ ሕልሜን ፡ የሚፈታ ፡ አምጡልኝ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከዮሴፍ ፡ ሳይደርስ ፡ ንጉሡን ፡ ሕልም ፡ እንዲያይ ፡ አደረገው ። አንድም ፡ ፈትታችሁ ፡ አምጡልኝ ፡ ያለው ፡ ቃሉ ፡ ከዮሴፍ ፡ ሳይደርስ ፡ ሕልሜን ፡ የሚፈታ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ። ለያዕቆብ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ዐሥራ ፡ አንዱ ፡ በዮሴፍ ፡ ቀን ተውበት ፡ ለግብፃውያን ፡ ሸጡት ፤ እንያስ ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ነው ፡ የሸጡት ፡ እስማኤላውያን ፡ ለግብፃውያን ፡ ስለ ፡ ሸጡት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ በምን ፡ ምክንያት ፡ በሉ ፡ ያዕቆብ ፡ ራሄልን ፡ ይወዳታል ፡ ከሷ ፡ የሴፍን ፡ ብንያምን ፡ ይወልዳል ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይወደዋል ፤ ከመውደዱም ፡ የተነሣ ፡ ዐራት ፡ ጎብር ፡ አምስተኛ ፡ በወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ግምጃ ፡ አልብሶት ፡ ይኖራል ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ይቀኑበታል ፤ ኋላም ፡ እሱ ፡ ለያዘው ፡ ነዶ ፡ ወንድሞቹ ፡ የያዙት ፡ ነዶ ፡ ሲሰግድ ፡ አይቶ ፡ ላባቱ ፡ ነገረው ፡ ወንድሞችህ ፡ በረኑብ ፡ ምክንያት ፡ ይገዙልህ ፡ ይሆናል ፡ አለው ፡ ሁለተኛ ፡ ዐሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡ ላንድ ፡ ኮከብ ፡ ሲሰግዱ ፡ አይቶ ፡ ነገረው ፡ ዐሐይ ፡ የተባልሁ ፡ እኔ ፡ አባትህ ፡ ነኝ ፡ ጨረቃ ፡ የተባለች ፡ እናትህ ፡ ናት ፡ እናቱስ ፡ ከመንገድ ፡ መታ ፡ ቀርታለች ፡ ብሎ ፡ ካራቱ ፡ ዕቁባቱ ፡ አንዲቱ ፡ ዘለፋ ፡ አብራው ፡ ወርዳ ፡ ነበርና ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡ የተባሉ ፡ ወንድሞችህ ፡ ናቸው ፡ በረኑብ ፡ ምክንያት ፡ ይገዙልህ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለወንድሞችህ ፡ አትንገራቸው ፡ ይላለሃል ፡ አለው ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ የሚኖሩ ፡ ሣር ፡ ወሀ ፡ ካለበት ፡ ነውና ፡ ስንቃቸውን ፡ አሲዞ ፡ ይህን ፡ ሰጥተህ ፡ ወንድሞችህ ፡ ያሉበትን ፡ ጠይቀህ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፤ ሲፈልጋቸው ፡ ሰንብቶ ፡ አጣቸው ፡ መልአኩ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ተገልጾ ፡ ታየው ፤ አይቴ ፡ ይርእዩ ፡ አኃውየ ፡ አለው ፤ ቴምናስራህ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ዶታይን ፡ እንሂዳለን ፡ ሲሉ ፡ ሰምቻቸው ፡ ነበር ፡ አለው ፤ ሄዶ ፡ ከሩቅ ፡ አይተው ፡ ዐወቁት ፡ መጽአ ፡ ዝኩ ፡ እኁነ ፡ ሐላሜ ፡ ሕልም ፡ ንዑ ፡ ንቅትሎ ፡ ወንደዮ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ወንር

ዓይ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ አሕላሚሁ ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይነግሥብን ፡ እንደሆነ ፡ እናያለን ፡ አሉ ፡ ያመጣላቸውን ፡ ስንቅ ፡ ተቀብለው ፡ ከብበው ፡ እየተቀባበሉ ፡ ይመቱት ፡ ዠመሩ ፡ ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ምሳሌ ፡ ተቀብለው ፡ ከብበው ፡ እንደ ፡ መቱት ፡ ቤተ ፡ አይሁድም ፡ የጌታን ፡ ትምርቱን ፡ ይጠላሉ ፡ ተአምራቱን ፡ ይወዳሉና ፡ በእንተ ፡ ሠናይሰ ፡ ግብርከ ፡ ኢንዌግረከ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ጽርፈ ትከ ፡ እንዲል ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴፫ ሮቤል ፡ ያጥንታችንን ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችንን ፡ ቊራጭ ፡ ተዉ ፡ ብሎ ፡ አስጥሏቸዋል ፤ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ አባት ፡ ነውና ፡ አንድም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በባላ ፡ ምክንያት ፡ ካባቱ ፡ ከያዕቆብ ፡ ተጣልቶ ፡ ነበርና ፡ መታረቅያ ፡ ይሆነኛል ፡ ብሎ ፡ ዘፍ ፡ ፴፮ ፡ ፮፪ ፡ ዓዘቅት ፡ ሐዳስ ፡ ይላታል ፡ ወሀ ፡ ያልወጣላት ፡ ጉድጓድ ፡ አለች ፡ እሱን ፡ ከዚያ ፡ አግብተው ፡ ይመገቡ ፡ ዠመር ፤ ከብት ፡ የሚመልሱ ፡ በተራ ፡ ነው ፡ የሮቤል ፡ ተራ ፡ ደርሶት ፡ ሊመልስ ፡ ሄዶ ፡ እስማኤላውያን ፡ መጡ ፡ ይሁዳ ፡ የይሁዳ ፡ ሬታውራሪ ፡ ነውና ፡ ወንድማችንን ፡ ገድለን ፡ ብንቀብረው ፡ ምን ፡ ይረባናል ፡ ይጠቅመናል ፡ እንሽጠው ፡ አላቸው ፤ ወሜጥዎ ፡ ለጽ፡ ዲናር ፡ ይላል ፡ ለኻያ ፡ ወቄት ፡ ሸጠውታል ፤ በግብፅ ፡ ሠላሳ ፡ ይላልሳ ፡ ቢሉ ፡ የሚዛን ፡ ደግነት ፡ ነው ፡ በከነዓን ፡ ኻያው ፡ በግብፅ ፡ ሠላሳ ፡ ይሆናል፡ አንድም፡ ጴጥፋራ ፡ በሠላሳ ፡ ወቄት ፡ ገዝቶታል ፡ ኻያውን ፡ ሰጥቶ ፡ ዐሥሩን ፡ ከሹሙ ፡ ተቀበሉ ፡ ብሏቸው ፡ ሹሙ ፡ አስቀርቶባቸዋል ፤ ሮቤል ፡ መጥቶ ፡ ምነው ፡ እንዲህ ፡ አደረጋችሁ ፡ ያጥንታችንን ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋችንን ፡ ቊራጭ ፡ ወንድማች ነን ፡ አላቸው ። ጠቦት ፡ አርደው ፡ ልብሱን ፡ በደም ፡ ጠምተው ፡ ርኢ ፡ ለእመ ፡ ክዳኑ ፡ ውእቱ ፡ ለወልድከ ፡ ያን ፡ ብላቴና ፡ ወደኛ ፡ ሰደኸው ፡ ኑሯልን ፡ አውሬም ፡ በልቶት ፡ እንደሆነ ፡ ልብሱን ፡ እንዲህ ፡ ሁኖ ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ ላኩበት ፡ እያለቀሰ ፡ ዓይኑ ፡ ጠፍቷልና ። ዘፍ ፡ ፴፯ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ። ዮሴፍ ፡ የመለኮት ፡ ልብስ ፡ የትስብዕት ፡ ደም ፡ ከልብሱ ፡ እንጂ ፡ ከዮሴፍ ፡ እንዳልደረሰ ፡ ሕማም ፡ ሞትም ፡ ከትስብዕት ፡ እንጂ ፡ ከመለኮት ፡ ላለመድረሱ ፡ ምሳሌ ። ጴጥፋራ ፡ በዮሴፍ ፡ ምክንያት ፡ ከበረ ፡ አቢዳራ ፡ በታቦት ፡ ጽዮን ፡ ምክንያት፡ እንደ ፡ ከበረ ፤ ጴጥፋራ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከመጣ ፡ ገንዘቤ ፡ በዛ ፡ ብሎ ፡ የሜዳ ፡ ንስንሱን ፡ የቤት ፡ ጉስጉሱን ፡ ሰጥቼሃለሁ ፡

አለው ፡ ወወደየት ፡ አዕይንቲሃ ፡ ብእሲተ ፡ እግዚኡ ፡ እንዲል ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፡ እያየች ፡ ዓይኗን ፡ ጣለችበት ። ከዕለታት፡ ባንዳችው ፡ ነዓ ፡ ስክብ ፡ ምስሌየ ፡ ብላ ፡ ገል ጣ ፡ ነገረችው ፤ ጌታዬ ፡ በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ሲያሠለጥነኝ ፡ ባንቺ፡ ብቻ ፡ አላሠለጠነኝም ፡ አላት ። ከዕለ ታት ፡ ባንዱ ፡ ባሏ ፡ ለተግባሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ ከዕቃ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ግምጃ ፡ ሲያናፍስ ፡ ዕቃ ፡ ሲቆ ጥር ፡ አንት ፡ ባሪያ ፡ ዛሬ ፡ ገና ፡ አለቀቅሁኽም ፡ ብላ ፡ ተራምዳ ፡ ያዘችው ፤ ነጥቄ ፡ እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ ቀሚሱ ፡ ከወደ ፡ ኋላው ፡ ተቀደ ደበት ፤ ጨሌንካውን ፡ ሳንቃ ፡ ሰበረበት ፤ ብታፍር ፡ ቀሚሷን ፡ ከወደ ፡ ፊቷ ፡ ቀድዳ ፡ ጮኸች ፤ መጥተው ፡ ምን ፡ ሆንሽ ፡ አሏት ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ሲገዛ ፡ አፍንጫ ፡ ጕራዴ ፡ ፊተ ፡ ጨምዳዳ ፡ ራሰ ፡ ቆርዳዳ ፡ ይገዛል ፡ ቢሉት ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ባሪያ ፡ ገዝቶ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ቀሚ ሴን ፡ ቀድዶት ፡ ሄደ ፡ አለቻቸው ፤ አሕዛብ ፡ ፍርድ ፡ ጠንቃቆች ፡ ናቸውና ፡ ፈቃድስ ፡ ያንቺ ፡ ይመ ስላል ፡ ያማ ፡ ቢሆን ፡ የሱ ፡ በፊቱ ፡ ያንቺ ፡ በኋላሽ ፡ ባልተቀደደም ፡ ነበርን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይበ ልሽ ፡ ብለው ፡ አሰሩት ፡ ባሏ ፡ መጣ ፡ ለቅናት ፡ የለው ፡ ፅናት ፡ እንዲሉ ፡ አያደርግም ፡ አላለም ፡ ከፈርያን ፡ እስረኞች ፡ ወስዶ ፡ ደረበው ፡ ሹሙ ፡ እስረኞች ፡ አን ተ ፡ ባልካቸው ፡ ይውጡ ፡ ይግቡ ፡ ብሎታል ፤ ያለሹመት ፡ አላደ ረም ፤ ወኢኃደረ ፡ ዘእንበለ ፡ ሢመት ፡ ወኢርዕየ ፡ ገጸ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፴፱ ፡ ፩ ፡ ጵጥ* የፈርያን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊ ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ ታሥ ረው ፡ ነበረ ፤ ሕልም ፡ አይተው ፡ የሚተረጉምላቸው ፡ አጥተው ፡ አዝነው ፡ ሳሉ ፡ ፀሐይ ፡ ሲሞቅ ፡ ቆይቶ ፡ ገብቶ ፡ ምነው ፡ አዝናች ኋል ፡ አላቸው ፤ ዐሠሩ ፡ ለልብ ፡ ብሩህ ፡ ገጽ ፡ ወእምከመ ፡ ይቴ ክዝ ፡ ልብ ፡ ይዴምን ፡ ገጽ ፡ እን ዲል ፡ ሕልም ፡ አይተን ፡ የሚተ ረጉምልን ፡ አጥተን ፡ አሉት ፤ ሕልምን ፡ እንጂ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የገለጸለት ፡ ሰው ፡ ይተረጉመ ዋል ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ በነገሩ ፡ ሃይማኖቱን ፡ አመለከታቸው ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ ሦስት ፡ የወ ይን ፡ ዘለላ ፡ በጌታዬ ፡ ፅዋ ፡ አፅ ርቼ ፡ ለጌታዬ ፡ ስሰጠው ፡ አየሁ ፡ አለው ፤ ሦስት ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ምሳሌ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከሹመትህ ፡ ትመ ለሳለህ ፡ አለው ፤ ለዝያ ፡ ሲተረ ጕምለት ፡ ሰምቶ ፡ ሥጋ ፡ መልከ ኛውም ፡ በሦስት ፡ እንቅብ ፡ (መሶብ) ፡ አደራርቤ ፡ ፉገሬ ፡

ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስገባ ፡ አዕዋፍ ፡ ከላዬ ፡ ገልብጠው ፡ ሲመገቡት ፡ አየሁ ፡ አለው ፤ ሦስት ፡ እንቅብ ፡ ሦስት ፡ (መሶብ) ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ምሳሌ ፡ እንቅብ ፡ መሥፈሪያ ፡ እንደሆነ ፡ ዕለትም ፡ የዕጁ ፡ መሥፈሪያ ፡ ነው ።

እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ፈርዖን ፡ ይሰቅልሃል ፡ ንጉሥ ፡ የሰቀለውን ፡ አንበሳ ፡ የሰበረውን ፡ የሚነካው ፡ የለምና ፡ አዕዋፍ ፡ ይበሉሃል ፡ ብሎ ፡ ተረጐመበት ፤ ለዝያ ፡ ለተረጐመለት ፡ ለጸጅ ፡ አሳላፊው ፡ ቀድሞም ፡ በግፉዕ ፡ ተሸጫለሁ ፡ ዛሬም ፡ በግፍ ፡ ታሥሪያለሁና ፡ አዘክረኒ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአከ ፡ ፈርዖን ፡ አለው ፡ ይህም ፡ ለዮሴፍ ፡ ዕዳ ፡ ሆኖበት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ እንዲታሠር ፡ አድርጎ ታል ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ፈርዖን ፡ በዓል ፡ አደረገ ፤ አሕዛብ ፡ የተወለዱበትን ፡ ቀን ፡ ያከብራሉ ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ ተወልደን ፡ ከዚህ ፡ ማዕርግ ፡ የደረስንበት ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከጠባብ ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ የወጣንበት ፡ ሲሉ ፡ መኳንንቱ ፡ በዓሉን ፡ አክብረው ፡ እጅ ፡ ሊነሱ ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፡ እንደምን ፡ ሁናችሁ ፡ ዋላችሁ ፡ አላቸው ፤ መልካም ፡ ውለናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀድሞውን ፡ ጸጅ ፡ አሳላፊ ፡ የዛሬውን ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ ለሹመት ፡ የቀድሞውን ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ የዛሬውን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊ ፡ ለቅጣት ፡ ብለናል ፡ አሉት ፡ ያንን ፡ ወደሹመት ፡ መለሰው ፡ ያም ፡ ተቀጣ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይዘነጋዋል ፡ ዘፍ ፡ ፵ ፡ ፩-፳፫ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ ፈርዖን ፡ ሕልም ፡ አየ ፤ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ያለሁ ፡ ይመስለዋል ፡ ሰባት ፡ የወፈሩ ፡ የሰቡ ፡ ላሞች ፡ ወጥተው ፡ ሲሰማሩ ፡ ሰባት ፡ የከሱ ፡ ላሞች ፡ ወጥተው ፡ ውጠዋቸው ፡ ያልቀመሱ ፡ ሲመስሉ ፡ ሁለተኛ ፡ ሰባት ፡ ያፈሩ ፡ የለመለሙ ፡ እሸቶች ፡ ሲወጡ ፡ ሰባት ፡ የደረቁ ፡ የሰለቱ ፡ እሸቶች ፡ ወጥተው ፡ ውጠዋቸው ፡ ያልቀመሱ ፡ ሲመስሉ ፡ አየ ፤ ወአእመረ ፡ ፈርዖን ፡ ከመ ፡ ሕልም ፡ ውእቱ ፡ ይላል ፤ ሕልም ፡ እንደሆነ ፡ ዐወቀ ፤ ሕልምማ ፡ እንግዲያ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ምሳሌ ፡ ያለው ፡ ደግ ፡ ሕልም ፡ እንደሆነ ፡ ዐወቀ ፡ ወአስተጋብኦሙ ፡ ለጠበብቱ ፡ ጠበብቱን ፡ ጠርቶ ፡ ተርጉመልኝ ፡ አላቸው ፡ ወሰዕኑ ፡ ፈከሮቶ ፡ መተርጐም ፡ ተሳናቸው ፤ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ እዜከራ ፡ ለዘቀደመት ፡ ኃጢአትየ ፡ ዝንጋዔየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እኔና ፡ ባልንጀራዬ ፡ ታሥ

ረን ፡ ሳለን ፡ ሁለታችንም ፡ ሕል
ም ፡ አየን ፡ ለኔ ፡ ተረጐመልኝ ፡
ሆነልኝ ፡ በሱም ፡ ተረጐመበት ፡
ሆነበት ። አሁንም ፡ ከጴጥፋራ ፡
ባሪያ ፡ በቀር ፡ ሕልምህን ፡ የሚ
ተረጕምልህ ፡ የለም ፡ አለው ።

ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፩-፲፫ ።

፰ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ወፈትሖ ።

ንጉሡ ፡ ብላቴና ፡ ልኮ ፡ ፈታው ፡
ማለት ፡ ራሱን ፡ ላጭታችሁ ፡
ገላውን ፡ አጥባችሁ ፡ ጌጠኛ ፡
ልብስ ፡ አልብሳችሁ ፡ አምጡ
ልኝ ፡ አለ ። አመጡት ፡ ሄዶ ፡
እጅ ፡ ነሣ ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡
የሚተረጕምልኝ ፡ አጥቼ ፡ መተ
ርጐመ ፡ ሕልም ፡ ነህ ፡ ቢሉኝ ፡
ትተረጕምልኝ ፡ ብዬ ፡ አለው ።
ሕልምን ፡ እንጂ ፡ እግዚአ ብሔር ፡
የገለጸለት ፡ ይተረጕመዋል ፡ ንገ
ረኝ ፡ ልተርጕምልህ ፡ ብሎ ፡ ሃይ
ማኖቱን ፡ በነገሩ ፡ ያመለክተዋል ።
ነገረው ። ፭ዱ ፡ ውእቱ ፡ ሕልሙ ፡
ለእግዚአየ ፡ ሕልሙ ፡ አንድ ፡
ነው ፡ መደጋገሙ ፡ ምሳሌ ፡ ያለ
ው ፡ ደግ ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ ለማ
ለት ፡ ሰባት ፡ የሰቡ ፡ አልሕምት ፡
የለመለሙ ፡ ያፈሩ ፡ ሰዊት ፡ አንድ ፡
ወገን ፡ የሰባቱ ፡ ዘመን ፡ ጥጋብ ፡
ምሳሌ ፡ ሰባት ፡ የከሱ ፡ ላሞች ፡
ሰባት ፡ የደረቁ ፡ የሰለቱ ፡ እሸቶች ፡
አንድ ፡ ወገን ፡ የሰባቱ ፡ ዘመን ፡
ረኀብ ፡ ምሳሌ ፡ ውጠዋቸው ፡
ያልቀመሱ ፡ ሲመስሉ ፡ ማየትህ ፡
የሰባቱን ፡ ዓመት ፡ ጥጋብ ፡ የሚያ
ዘነጋ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ረኀብ ፡
ይሆናል ፡ የጥጋቡንም ፡ የረኀቡ
ንም ፡ ማየትህ ፡ ጥጋቡም ፡ ፈጥ
ቡም ፡ የሚሆን ፡ ባንተ ፡ ዘመን ፡
ነው ፡ ከወሀ ፡ ዳር ፡ መሆኑ ፡
ዝናም ፡ አይዘንምላቸውም ፡ ኑሯ
ቸው ፡ በመስኖ ፡ ነውና ፡ አን
ድም ፡ ጥጋብም ፡ ረኀብም ፡ በመ
ስኖ ፡ ነውና ። ቢገኝ ፡ ጥጋብ ፡
ቢታጣ ፡ ረኀብ ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡
ይበጀኛል ፡ አለው ፡ ሚም ፡ ማእ
ምረ ፡ ወለባዌ ፡ ብልሀ ፡ ሰው ፡
ሹም ፡ አለው ። ሹመት ፡ ተካሠሰ ፡
ወአልቦ ፡ ዘይጠበብ ፡ እምኔከ ፡
ተሠየም ፡ ሊተ ፡ ካንተ ፡ ወዲያ ፡
ዐዋቂ ፡ ማነን ፡ አገኛለሁ ፡ ተሾ
ምልኝ ፡ አለው ።

ሠሚም ፡ ሠልአከ ፡ አሕዛብ ።

ለአሕዛብ ፡ ገዢ ፡ አደረገው ፡
ማለት ፡ ብላቴን ፡ ጌትነትን ፡
ሾመው ። ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪-፵፫ ።

፳፩ ፡ ወረሰየ ፡ እግዚአ ፡ ለቤቱ ።

በቤቱ ፡ ሁሉ ፡ አዛዥነት ፡ ሾመው ።
ኢል ፡ አብሪኤል ፡ ዐዋጅ ፡ አብ
ሪል ፡ ጉብር ፡ ኮነ ፡ እግዚአ ፡ ማ
ለት ፡ ነው ። ሐቲም ፡ ቀለበቱን ፡
አድርጎ ፡ ከፋሩን ፡ አልብሶ ፡
መደቡት ፡ በምትባል ፡ በቅሎ ፡

አስቀምጦ ፡ ግብፅን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተመርታት ፡ ውሏል ፤ ወሰመ ዮ ፡ እስፍንቶፎኒህ ፡ ከሣቴ ፡ ምሥ ጢር ፡ መዝገበ ፡ ጥበብ ፡ ሊቀ ፡ ጠቢባን ፡ ማለት ፡ ነው ። ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፵፱ ፡ ወዲያው ፡ የወርቅ ፡ የ ብር ፡ የነፍጥ ፡ ግብሩ ፡ እህል ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፤ የሚነቅዘውን ፡ እያስወቀጠ ፡ እ ያስፈጨ ፡ እንደ ፡ ጡብ ፡ እያሠራ ፡ የማይነቅዘውን ፡ እያስወቃ ፡ እ ንደ ፡ እናርያ ፡ በጎታ ፡ በጎተራ ፡ በሪቅ ፡ ሰበሰበው ፤ በሰባት ፡ ዓመ ት ፡ ጥጋብ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ረኀብ ፡ አዘጋጀ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጆቹ ፡ በግብፅ ፡ እህል ፡ አለ ፡ ሲሉ ፡ ሰምቻለሁና ፡ ሽምታችሁ ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አሲሦ ፡ ሰደዳቸው ፡ ሄደው ፡ ካደ ባባይ ፡ ተቀመጡ ፡ ዮሴፍ ፡ አይ ቶ ፡ ዐወቃቸው ፡ ነገር ፡ ሲሰማ ፡ ሁዳድ ፡ ሲያስሆድድም ፡ ቢሉ ፡ ምንድር ፡ ናችሁ ፡ ብላችሁ ፡ ጠይቋቸው ፡ አለ ፤ ምንድር ፡ ናችሁ ፡ አሏቸው ፡ ሸማኞች ፡ ነን ፡ አሉ ፡ ሐሰታችሁ ፡ ነው ፡ ሰላ ዮች ፡ ናችሁ ፡ የከተማውን ፡ መዕ ናት ፡ አለመዕናት ፡ የሰውን ፡ መብ ዛት ፡ አለመብዛት ፡ ልትሰልሉ ፡ ነው ፡ የመጣችሁ ፡ አላቸው ። ሰላይ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ካንዱ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ተወግዕቶ ፡ ይመጣል ፡ እንጂ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ሁነን ፡ እንመጣ ለንን ፡ አሉት ። አንድ ፡ ሰው ፡ ዐሥር ፡ ልጆች ፡ ይወልዳልን ፡ አላቸው ፤ እረ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነበርን ፡ አሉት ፡ ሁለቱ ፡ ሄት ፡ ሄደዋል ፡ አላቸው ፡ አንዱ ፡ ሕ ፃን ፡ ሁኖ ፡ ከቤት ፡ ቀርቷል ፤ አንዱን ፡ አውሬ ፡ በላው ፡ ብለው ፡ አረዱት ። ማ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ፡ ፴፫ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯ ፡ ፳፱ ፡ ፴፯ ከቤት ፡ ያለውን ፡ ወንድማችሁን ፡ ያመጣችሁ ፡ እንደሆነ ፡ እየወጣ ችሁ ፡ እየገባችሁ ፡ ትሸምታላ ችሁ ፡ ያለዚያ ፡ ግን ፡ አይሆን ላችሁም ፡ ብሎ ፡ ስምዖንን ፡ መያ ዣ ፡ አድርጎ ፡ አስቀረው ፤ እስመ ፡ ወንዓ ፡ ቡቱ ፡ በቀዳሚ ፡ ተሠይ ይጠቱ ፡ ይላል ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ተናግሮት ፡ ነበርና ፡ መለየቱን ፡ ይቅመሰው ፡ ብሎ ፡ ለዮሴፍስ ፡ ይህ ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ሰውነቱ ፡ ተጎድቶ ፡ ነበ ርና ፡ መውጣት ፡ መውረዱን ፡ ይረፈው ፡ ብሎ ። ሹመ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ወርቅ ፡ ይዘው ፡ መጥ ዋል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ አትንካ ፡ እህሉን ፡ በየአይበታቸው ፡ እየመ ላህ ፡ ወርቁን ፡ በየአይበታቸው ፡ እያደረግህ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ፣ ያንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፡ ገፈራ ፡ የሚያበሉ ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ገፈራ ፡ ለማብላት ፡ አንዱ ፡

አይበቱን ፡ በፈታ ፡ ወርቁን ፡ አገ
ኘ ፡ ሊተሰ ፡ ገብአተኒ ፡ ወርቅየ ፡
አለ ፡ ሁሉም ፡ በየቤታቸው ፡ ሲ
ገቡ ፡ አገኙት ። ስምዖንስ ፡ አላ
ቸው ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ መያዣ ፡
አድርጎ ፡ አስቀረው ፡ አሉት ፤
በልተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ብንያምን ፡
ካላመጣችሁ ፡ አይሆንላችሁም ፡
ብሎናልና ፡ ብንያምን ፡ ስጠን ፡
ሸምተን ፡ እናምጣ ፡ አሉት ።
ዮሴፍ ፡ ኢሀሎ ፡ ስምዖን ፡ ኢሀሎ ፡
ዮሴፍን ፡ አውሬ ፡ በላው ፡ አላች
ሁኝ ፡ ስምዖንን ፡ መያዣ ፡ አድር
ጎ ፡ አስቀረው ፡ አላችሁኝ ፤ በማ
ናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ሙቶ ፡ ቢ
ቀር ፡ ወታወርድም ፡ ለርስዓንየ ፡
በጎዘን ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ እን
ዳዘንሁ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ልታወ
ርዱኝ ፡ ነው ፡ አላቸው ። ዘፍ ፡
፵፪ ፡ ፳-፴፰ ። ሮቤል ፡ እኔ ፡ ደህና ፡
ባልመልሰው ፡ የኔን ፡ ልጆች ፡
ግደል ፡ አለው ፤ ያላዋቂ ፡ አነጋ
ገር ፡ ይሁዳ ፡ እኔ ፡ ደህና ፡ ባልመ
ልሰው ፡ ዕዳው ፡ በኔ ፡ ይሁን ፡
አለው ፡ የሱን ፡ ተቀብሎታል ፡
እመቤታችን ፡ ጌታችን ፡ በጉል
በቱ ፡ ያሉ ፡ ነውና ። ከዚህም ፡
ቢሆን ፡ ረኀቡ ፡ ይገድለዋል ፡
ይዛችሁት ፡ ሂዱ ፡ ብሏቸዋል ፤
ከግብፅ ፡ መልሰው ፡ ያመጡትን ፡
ወርቅ ፡ ሌላም ፡ ያንን ፡ ያህል ፡
ወርቅ ፡ በግብፅ ፡ የሌለ ፡ በከነ
ዓን ፡ ያለ ፡ ሽቱ ፡ ማር ፡ ገጸ ፡ በረ
ከት ፡ አሲዞ ፡ ሰደዳቸው ፤ ሂደው ፡
ከጥንት ፡ ቦታቸው ፡ ተቀመጡ ፤
ዝኑ ፡ ውእቱ ፡ እጎክሙ ፡ ዘትብሉ፡
ናመጽኦ ፡ እናመጣዋለን ፡ ያላ
ችሁት ፡ ወንድማችሁ ፡ ይህ ፡
ነውን ፡ አላቸው ፡ አዎን ፡ አሉት ፤
እግዚአብሔር ፡ የሀሉ ፡ ምስሌከ ፡
እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ አይ
ለይህ ፡ ከኒህ ፡ ከክፉዎች ፡ ጋራ ፡
የምትኖር ፡ አለው ። ደኅንኑ ፡
ዝስኩ ፡ አረጋዊ ፡ አቡክሙ ፡ አላ
ቸው ፡ እወ ፡ ዳኅን ፡ አዎን ፡ ደኅና ፡
ነው ፡ አሉ ፤ ወዓዲ ፡ ሕያው ፡
ገና ፡ ከጉልበት ፡ ነውን ፡ አላቸው ፤
አዎን ፡ አሉ ፤ ቡሩክ ፡ ብእሲሁ ፡
አላቸው ፡ አባታችንን ፡ አመሰ
ገነልን ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነሡ ። ሹ
ሙን ፡ ከፈርዖን ፡ ደርሼ ፡ እስ
ክመለስ ፡ ከወንድማቸው ፡ አገና
ኛቸው ፡ አለው ፤ ቀድሞ ፡ ወስ
ደነው ፡ በነበረ ፡ ወርቅ ፡ ሊያግ
ዙን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀድሞ ፡
የወሰድነውን ፡ ወርቅ ፡ አምጥ
ተናል ፡ ሌላም ፡ ያን ፡ ያህል ፡
ይዘን ፡ መጥተናል ፡ አሉት ፤
ሠሚርየ ፡ ነሣእክዎ ፡ ጠብሼ ፡
ለዕዳ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቼዋለሁ ፡
አምላከ ፡ አቡክሙ ፡ ወሀበክሙ ፡
መድፍነ ፡ ያባታችሁ ፡ አምላክ ፡
ያልታወቀ ፡ ሸሽጎ ፡ ሰጥቷችሁ ፡
እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።

ገጸ ፡ በረከቱን ፡ አዘጋጁ ፤ ዮሴፍ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደርሶ ፡ ሲመለስ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ አበረከቱ ፤ ሦስት ፡ ማዕድ ፡ አሠራ ፡ አንዱ ፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ አንዱ ፡ ለግብጻውያን ፡ አንዱ ፡ ለወንድሞቹ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ የምትችል ፡ ሌማት ፡ አሠርቶ ፡ እንደ ፡ ትውልዳችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ፡ ሮቤል ፡ በቀኙ ፡ ብንያም ፡ በግራው ፡ ተቀመጡ ፤ ወአዕበየ ፡ ክፍሎ ፡ ለብንያም ፡ ኀምሰ ፡ እደ ፡ ይላል ፡ ደራርቦ ፡ ጣለለት ፡ እንያ ፡ ሁለተኛቸው ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ እንግዳ ፡ ነውና ። ዘፍ ፡ ፵፫ ፡ ፭-፴፬ ።

በልተው ፡ ጠጥተው ፡ ስድስቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁለቱ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ ሁለቱ፡ አንድ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ ይጫወታሉ ፡ ብንያም ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ምነው ፡ አትጫወትምን ፡ ብለህ ፡ ጠይቀው ፡ አለው ፡ እኒህ ፡ ስድስቱ ፡ ያንዲት ፡ ሁለቱ ፡ ያንዲት ፡ ሁለቱ ፡ ያንዲት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ እኔም ፡ ወንድም፡ ነበረኝ ፡ አውሬ ፡ በላው፡ አለው። ካንድ ፡ ላይ ፡ ኮራይ፡ ዘብሩር ፡ ካንድ ፡ ላይ፡ ገይበ፡ ብሩር ፡ ይላታል ፤በቀለበቱ፡ ሲመታት ፡ ትሰማለች ፡ ሮቤል፡ትላለች ፡ ሮቤል፡የሚባል ፡ ሰው ፡ አለን ፡ ይላቸዋል ፡ ስምዖን ፡ ትላለች ፡ ስምዖን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አለን ፡ ይላቸዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹሙ ፡ ቀድሞ ፡ የወሰዱትን ፡ ወርቅ ፡ ሌላም ፡ ያን፡ ያህል ፡ ጨምረው ፡ አምጥተዋል ፤ ይለዋል ፡ አትንካ ፡ እህሉን ፡ በየአይበታቸው ፡ እየመላህ ፡ ወርቁን ፡ በየአይበታቸው ፡ እያደረግህ ፡ ስደዳቸው ፡ ከታናሹ ፡ ልጅ ፡ አይበት ፡ የኔን ፡ ዕዋ ፡ አግብተህ ፡ እንደ ፡ ጥበብህ ፡ መልሰህ ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ። ጥቂት ፡ እልፍ ፡ እንዳሉ ፡ ተከትሎ ፡ ለምንት ፡ ሰረቀው ፡ ገይበ ፡ ዘያቀሪ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእየ ፡ የበጎነት ፡ ወረታ ፡ ክፉት ፡ ነውን ፡ ጌታዬ ፡ የሚጠጣበትን ፡ ዕዋ ፡ ለምን ፡ ሰረቃችሁ ፡ አላቸው ፡ እኛስ ፡ አልወሰድንም ፡ ከነዓን ፡ እንኳ ፡ ይዘን ፡ ሄደን ፡ የነበረውን ፡ መልሰን ፡ አምጥተናል ፡ አሉ ፡ የተኘገበት ፡ ይሙት ፡ አለ ፡ ሞትማ ፡ ለምን ፡ ይሞታል ፡ ባሪያ ፡ ሁኖ ፡ ይገዛ ፡ እንጂ ፡ አላቸው ፡ በሮቤል ፡ ይዞምራል ፡ ሰው ፡ ጠላቱን ፡ ሲያውቅ ፡ በወዳጁ ፡ እንዲጀምር ፡ ከብንያም ፡ ተገኘ ፤ ቀድሞ ፡ እናቱ ፡ ከመንግድ ፡ ሙታ ፡ የቀረች ፡ ከሷ ፡ የተወለደ ፡ ይህ ፡ እንዲህ ፡ አደረገን ፡ አሉ ፤ ዘፍ ፡ ፵፫ ፡ ፯ ።

ሮቤል ፡ እኔ ፡ ስለሱ ፡ ልገዛ ፡ እሱን ፡ አሰናብትልኝ ፡ አለው ፡ የተገኘበትን ፡ ትቼ ፡ ያልተገኘበትን ፡ አላው ፡ ዮሴፍ ፡ እንዲህ ፡

ማድረጉ ፣ በቀደመ ፣ ክፋታቸው ፣ ያሉ ፣ እንደሆነ ፣ ጥለውት ፣ ይሄዳሉ ፣ ብሎ ፣ ሊሰልላቸው ፣ ነው ፤ የተገኘበትን ፣ አምጣ ፣ ብልህ ፣ እሊህን ፣ ለምን ፣ አመጣኻቸው ፣ አለው ። ይሁዳ ፣ አባቴን ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ሰምቼዋለሁ ፣ አባቴ ፣ ሲሞት ፣ አላይም ፣ እኔ ፣ ስለሱ ፣ ልገዛ ፣ እሱን ፣ አሰናብትልኝ ፣ አለው ፤ የተገኘበትን ፣ ትቼ ፣ ያልተገኘበትን ፣ አልሻም ፣ አለው ፤ ይህ ፣ ሁሉ ፣ የወንድማችን ፣ ግፍዕ ፣ አይደለምን ፣ ያጥንታችንን ፣ ፍላጭ ፣ የሥጋችንን ፣ ቁራጭ ፣ ወንድማችንን ፣ ሸጠነው ፣ ይባባሉ ፣ ዝምሩ ፤ መተርጕም ፣ እንዳለ ፣ ባያውቁ ፣ አንድም ፣ መተርጕም ፣ የሴፍ ፣ እንዳለ ባያውቁ ፣ ዘፍ ፣ ፴፯ ፣ ፳ ፣ ፴፱ ፣ ከቤት ፣ ይዟቸው ፣ ገብቶ ፣ አነ ፣ ውእቱ ፣ የሴፍ ፣ እጐክሙ ፣ ዘሜ ጥክሙኒ ፣ አላቸው ፣ ደነገጡ ፣ አይዟችሁ ፣ አትደንግጡ ፣ እናንት ፣ ለክፋት ፣ አድርጋችሁት ፣ ነበረ ፤ አግዚአብሔር ፣ ግን ፣ ለበጎ ፣ ነው ፣ ያደረገው ፣ በዘመነ ፣ ረኃብ ፣ ልመግባችሁ ፤ እኔ ፣ ባል ኖር ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ ከሄት ፣ በተገኘ ፣ ነበር ፣ ብሎ ፣ ለወንድሞቹ ፣ ሁለት ፣ ሁለት ፣ ልብስ ፣ ለብን ያም ፣ አምስት ፣ ልብስ ፣ ሦስት ፣ መቶ ፣ ወቄት ፣ ወርቅ ፣ ላባቱም ፣ ይህን ፣ ያህል ፣ የሚመጣበትን ፣ ባሥር ፣ ወቄት ፣ የተገዛ ፣ ሠረገላ ፣ ፲ት ፣ አብቅለ ፣ ወኀተ ፣ አእዱገ ፣ የጓዝ ፣ መጫኛ ፣ ዐሥር ፣ በቅሎ ፣ ዐሥር ፣ አህያ ፣ ልኮለታል ፤ ክብርየ ፣ በብሔረ ፣ ባዕድ ፣ በባዕድ ፣ አገር ፣ ያገኘሁትን ፣ ክብሬን ፣ ላባቴ ፣ ንገሩት ። አመላልሽ ፣ እንዳልመግብህ ፣ ከሰባቱ ፣ ዓመት ፣ ረኀብ ፣ ሁለት ፣ ዓመት ፣ ተነሥቶልታል ፣ አምስት ፣ ዓመት ፣ ቀርቶለታል ፣ ብላችሁ ፣ ይዛችሁልኝ ፣ ኑ ፣ አንተ ፣ ሸጠኸው ፣ እንተ ፣ ሸጠኸው ፣ እያላችሁ ፣ አትጣሉ ፣ እላንት ፣ ለክፋት ፣ ብታደርጉት ፣ አግዚአብሔር ፣ ለበጎ ፣ ነው ፣ ያደረገው ፣ በዘመነ ፣ ረኀብ ፣ ልመግባችሁ ፣ እኔ ፣ ባል ኖር ፣ ይህ ፣ ሁሉ ፣ ወደኋት ፣ ይገኝ ፣ ነበር ፣ ብሏቸዋል ።

ወአኰነኖ ፣ ላዕለ ፣ ፈጵሶ ፣ ጥራቁ ።

በገንዘቡ ፣ ሁሉ ፣ አሠለጠነው ፣ በጅሮንድነት ፣ ሾመው ፣ ወአንሶአመ ፣ ውስተ ፣ ኩሉ ፣ ደወለ ፣ ግብፅ ፣ ይላል ፣ ግብፅን ፣ ዙሮ ፣ ተመርኵታልና ፣ እንዲህ ፣ አለ ።

ጸፍዐ ፣ ኀመ ፣ ይገሥፆሙ ፣ ለመላእክቲሁ ፣ ከ ማ ሁ ።

አለቆቹን ፣ ይሠራቸው ፣ ይቀጻቸው ፣ ዘንድ ፣ (ከማሁ) ፣ እሱ ፣ የተቀጻ ፣ የተሠራ ፣ እንደሆነ ፣

አንድም ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ፈርያን ፡ ሁኖ ።

ወከሙ ፡ ያጥብዖሙ ፡ ለሊቃውንቲሁ ፡ ከ ማ ሁ ።

ሥዩማኑን ፡ ያራቅቃቸው ፡ ዘንድ ፡ (ከማሁ) ፡ እሱ ፡ የተራቀቀ ፡ እንደሆነ ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ፈርያን ፡ ሁኖ ።

፸፫ ፡ ወቦአ ፡ እስራኤል ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ።

እስራኤል ፡ ግብፅ ፡ ገባ ።

ወያዕቆብኒ ፡ ኀደረ ፡ ምድረ ፡ ካም ።

እስራኤል ፡ ያለውን ፡ ያዕቆብ ፡ ቦአ ፡ ያለውን ፡ ኃደረ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ፡ ያለውን ፡ ምድረ ፡ ካም ፡ ብሎ ፡ ደገመው ፡ ያዕቆብም ፡ በ ካም ፡ ዕፃ ፡ አደረ ። ዘፍ ፡ ፵፮ ፡ ፭ ፡ ፮ ።

፸፬ ፡ ወአብዝኖሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ፈድፋደ ።

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ አበዛቸው ፡ አከበራቸው ።

ወአሰንያሙ ፡ እምፀሮሙ ።

ከጠላቶቻቸው ፡ ከግብፃውያን ፡ ይልቅ ፡ እሳቸውን ፡ አጸናቸው ።

፸፭ ፡ ወሜጠ ፡ ልቦሙ ፡ ከመ ፡ ይጽልኡ ሕዝቦ ።

ልቦሙ ፡ ለግብፅ ፡ ነው ፤ ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ይጠሉ ፡ ዘንድ ፡ የግ ብፃውያንን ፡ ልቡና ፡ መለሰ ፡ በመ ጀመሪያ ፡ ፈርያን ፡ ፍቅር ፡ ጸንቷ ል ። ዘፍ ፡ ፶፩ ፡ ፴፱ ፡ ፵፫ ።

በሁለተኛው ፡ ፈርያን ፡ ፍቅር ፡ ተከፍሏል ። ዘፀ ፡ ፩ ፡ ፰፤ ፡ በሦስተ ኛው ፡ ፈርያን ፡ ፀብ ፡ ፀንቷልና ። ዘፀ ፡ ፭ ፡ ፱ - ፲፱ ፡ አንድም ፡ ልቦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ነው ፤ ግብፃውያ ንን ፡ ይጠሉ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤ ልን ፡ ልባቸውን ፡ መለሰ ፤ ሕ ዝቦ ፡ አላቸው ፤ ግብፃውያን ፡ በተፈጥሮ ፡ ወገኖቹ ፡ ናቸውና ፡ ወአጐጉዕሙ ፡ ግብፃውያን ፡ ለዕብራውያን ፡ ወአዕሐብዎሙ ፡ ይላል ፡ ውጡልን ፡ ውጡልን ፡ ብለዋቸዋል ።

ወከሙ ፡ የሠላልዩሙ ፡ ለእግዚኡሁ ።

እስራኤልን ፡ ይዘርፏቸው ፡ ዘንድ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ገንዘባቸውን ፡ ይወስዱባቸው ፡ ነበርና ፤ አንድም ፡ እስራኤል ፡ ግብፃውያንን ፡ ይዘርፉቸው ፡ ዘንድ ፡ በልብሰ ፡ ጎስት ፡ ምክንያት ፡ ዘርፈዋቸዋልና ፤ አግብ ርቲሁ ፡ በተፈጥሮ ።

፸፮ ፡ ፈነወ ፡ ሙሴሃ ፡ ገብሮ ።

አገልጋዩ ፡ ባለሚሉ ፡ ሙሴን ፡ ከምድያም ፡ ላከ ።

ወ አ ሮ ን ሃ ፡ ኀሩዮ ።

የመረጠው ፡ ባለሚሉ ፡ አሮንንም ፡ ከሜኬም ፡ ላከ ።

፸፯ ፡ ወሤመ ፡ ቃለ ፡ ትእምርቶ ፡ ላዕሌሆሙ

ለሳቸው ፡ የምልክት ፡ ቃል ፡ ገለ

ጸላቸው ፡ ሰጣቸው ። ዘዳ ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ፴፬ ። ሙሴ፡ ከምድያም፡ አሮን፡ ከሴኬም ፡ ሲመጡ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመንገድ ፡ ተገናኝተዋል ፤ ጌታ ፡ ሙሴን ፡ ፈንዎሙአ ፡ ለሕዝ ብየ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ይፀመ ዱኒ ፡ በሐቅል ፡ ብለህ ፡ ለፈር ዖን ፡ ንገረው ፡ አለው ፡ ኀሥሥ ፡ ባዕደ ፡ ዘትልዕክ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ላዕላዓ ፡ ልሳን ፤ የምትልከው ፡ ሌላ ፡ ፈልግ ፡ እኔ ፡ ድዳ ፡ ጸያፍ ፡ ነኝ ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ አከናውኖ ፡ መናገር ፡ አይሆንልኝም ፡ አለው ። ጸያፍ ፡ እእ ፡ የሚል ፡ ነው ፡ ዲዳ ፡ ረን ፡ ለ ፡ የሚል ፡ ነው ፤ ለሰው ፡ የሚያይበትን ፡ ዓይን ፡ የሚናገር በትን ፡ አንደበት ፡ የሚሰማበ ትን ፡ ጉሮ ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ይመ ስልሃል ፡ እኔ ፡ አይደለሁምን ፡ ሂድ ፡ አለው ፤ አይሆንም ፡ አ ለው ። ወአሮን ፡ እጉከ ፡ ይኩ ንከ ፡ አፈ ፡ እኔ ፡ ላንተ ፡ እነግር ሃለሁ ፡ አንተ ፡ ለአሮን ፡ ንገረ ው ፡ አሮን ፡ ለሕዝቡ ፡ ይንገር ልህ ፡ አለው ። ማን ፡ ላከኝ ፡ ል በል ፡ አለው ፡ አኽያ ፡ ሸራኽያ ፡ አልሻዳ ፡ ላከኝ ፡ በል ፡ አለው ፤ አኽያ ፡ ዘሀሎ ፡ ሸራኽያ ፡ ወይ ሄሉ ፡ አልሻዳይ ፡ አምላክ ፡ ተስ ፋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ምን ፡ ምል ክት ፡ ላሳየው ፡ አለው ፤ ምን ፡ ይዘሃል ፡ አለው ፤ ምነው ፡ በትር ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ያውቅ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ማናገር ፡ ቢሻ ው ፤ ምንተ ፡ ትሬዒ ፡ አሞፅ ፡ ምንተ ፡ ትሬዒ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ። በትር ፡ ይጐለሁ ፡ አለው ፡ ከምድር ፡ ጣላት ፡ አለው ፡ ወገደፎ ፡ ጣለው ፤ ወኮነ ፡ አርፄ ፡ ምድር ፡ ወፈርሀ ፡ ሙሴ ፡ ወጐየ ፤ ከምድር ፡ ቢጥ ለው ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡ ሙሴ ፡ ፈ ርቶ ፡ ሸሸ ። ወአንሥአ ፡ በዘነቡ ፡ ዥራቱን ፡ ይዘህ ፡ አንሣው ፡ አለ ው ፡ ቢያነሣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ እጅህን ፡ ክብብትህ ፡ አግብተህ ፡ አውጣው ፡ አለው ፤ አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ለምፅ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ አግብተህ ፡ አው ጣው ፡ አለው ፡ አግብቶ ፡ ቢያ ወጣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ። ዘዳ ፡ ፯ ፡ ፲፱ ይህን ፡ ሁለቱን ፡ አድርገህ ፡ አሳይተህ ፡ ቢሰጥ ፡ ሰጠ ፡ ያልሰ ሰጠህ ፡ እንደሆነ ፡ ዘጠኝ ፡ መቅ ሠፍት ፡ ዐሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኩር ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ ሥጥመት ፡ አምጣበት ፡ አለው ። ፯ ፡ ፱ ፡ ፲፫ ሄዶ ፡ ፈንዎሙአ ፡ ለሕዝብየአ ፡ እስራ ኤል ፡ ከመ ፡ ይፀመዱኒ ፡ በሐ ቅል ፡ ብሎሃል ፡ አለው ፡ ማን ፡ ነው ፡ አለው ፡ አኽያ ፡ ሸራኽያ ፡ አልሻዳይ ፡ አለው ፡ ምን ፡ ምል ክት ፡ አለህ ፡ አለው ፡ በትሩን ፡ ከምድር ፡ ጣለው ፡ እባብ ፡ ሆነ ፤

ኧራቱን ፡ ይዞ ፡ ቢያነሣው ፡ ደኅና፡ ሆነ ፤ ሁለተኛ ፡ እጁን ፡ ከብብቱ ፡ አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ለምፅ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ደኅና ፡ ሆነ ፡ ይህንስ ፡ የኔም ፡ ካህናት ፡ ያደርጉታል ፡ ብሎ ፡ ኢያኔስ ፡ ኢያንበሬስ ፡ የሚባሉ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ካህናተ ፡ ጣኦት ፡ ነበሩት ፡ አስጠርቶ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ፡ ብትራቸውን ፡ ቢጥሉት ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡ መልሰው ፡ ቢያነሡት ፡ አልሆነላቸውም ፤ እጃቸውን ፡ ከብብታቸው ፡ አግብተው ፡ ቢያወጡት ፡ ለምፅ ፡ ሆነ ፡ መልሰው ፡ አግብተው ፡ ቢያወጡት ፡ ደኅና ፡ የማይሆንላቸው ፡ ሆነ ፤ ሙሴ ፡ በትሩን ፡ ቢጥላት ፡ እባብ ፡ ሆነች ፡ የነሱን ፡ በትር ፡ ውጣ ፡ እያባረረች ፡ ሰድዳቸዋለች ፤ ወጦዩ ፡ በሥላቅ ፡ ይላል ፡ የሙሴ ፡ በትር ፡ ልትነድፈን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ እየዘበቱ ፡ ሸሽተዋል ፤ ንጉሡንም ፡ ልትነድፈው ፡ ሄደች ። ለጊዜው ፡ እሰድዳችኋለሁ ፡ አድኑኝ ፡ አላቸው ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢያአምሮ ፡ ወለእስራኤልኒ ፡ ገብርየ ፡ አይፈንም ፡ አለ ፤ ዐሥር ፡ መቅሠፍት ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛ ፡ ሥጦመት ፡ አመጣባቸው ።

መመንከርሂ ፡ በምድረ ፡ ካም ።

በካም ፡ ዕፃ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራቱን፡ አደረገላቸው ።

ሸጋ ፡ ፈነወ ፡ ጽልመት ፡ ወአጽለሞሙ ።

ጨለማ ፡ አምጥቶ ፡ አጨለማቸው ፡ ማለት ፤ ጨለማ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ሆነ ፡ በግብፃውያን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጨለማ ፡ ሁኖባቸዋል ፤ ለእስራኤል ፡ ግን ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ፡ ይፈራረቅላቸው ፡ ነበር ።

ወአምረርዎ ፡ ለቃሉ ።

ፈንዎሙአ ፡ ያለውን ፡ ቃሉን ፡ አሳዘኑት ፡ ማለት ፡ አንቀበልም ፡ አሉ ። ዘፀ ፡ ፮ ፡ ፱ ።

ጽፍ ፡ ወረሰየ ፡ ማየሙ ፡ ደመ ።

ወሀውን ፡ ደም ፡ አደረገው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደም ፡ ሁኗል ፤ በእስራኤል ፡ ግን ፡ የወሀው ፡ ጽርየት ፡ አልተለወጠባቸውም ።

ወቀተለ ፡ ዓሣቲሆሙ ።

ዓሣቸውንም ፡ ገደለባቸው ፡ በዕምዕ ፡ አንድም ፡ ምግብ ፡ ቢለወጥባቸው ። ዘፀ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ።

ወ ፡ ወአውዕአት ፡ ምድሮሙ ፡ ቁርነንዓት

ምድራቸው ፡ ዛጐል ፡ ልብሱ ፡ ተሳቦ ፡ ጓጉንቸር ፡ አስገኘች ።

ውስተ ፡ አብያተ ፡ ነገሥቶሙ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ በነገሥታቱ ፡ ቤት ፡ ተደረገ ፡ አንድም ፡ በነገሥታቱ ፡ ቤት ። ዘፀ ፡ ፰ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ።

፴፩ ፡ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ ወኩኑ ።

ሳንጃ ፡ ተርብ ፡ ተቄናጣጭ ፡ ዝን ብ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፡ መጣ ።

፴፪ንትንያ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድሮሙ ።

ትንኝም ፡ በምድራቸው ፡ ሁሉ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፡ መጣ ፤ ሴቶቹም ፡ ልባልማ ፡ ወንዶቹም ፡ ሱሪ ፡ ቢያደርጉ ፡ ቀሚስ ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ቢያጠልቁ አላዳናቸውም ፡ ን ውስ ፡ መሌሲታቸውን ፡ እየመ ጠመጠ ፡ ፈጅቷቸዋል ። ዝሰ ፡ አፅባዕተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ብለ ዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፲፮ ፡ ፴፪ ።

፴፫ ፡ ወረሰየ ፡ ዝናሞሙ ፡ በረደ ።

ዝናማቸውንም ፡ በረድ ፡ አደረ ገባቸው ።

፴፬ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ምድሮሙ ።

በምድራቸው ፡ እሳት ፡ ዘነመ ፤ (ነደደ) ፡ በግብፅ ፡ ዝናም ፡ አይ ዘንምም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጊዜ ፡ ገጥ ሞት ፡ እሳትና ፡ በረድ ፡ እንደ ፡ ሰምና ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ ተጣምቶ ፡ ወርዷል ። ዘፍ ፡ ፱ ፡ ፳፬ ፡ ፴፫ ።

፴፭ ፡ ወቀተለ ፡ ወይኖሙ ፡ ወበለሶሙ ።

ወይናቸውንም ፡ በለሳቸውንም ፡ አደረቀባቸው ፡ ከላይ ፡ በረድ ፡ ያረግፋል ፡ ከታች ፡ እሳት ፡ ያቃ ጥላልና ።

፴፮ ፡ ወቀጥቀጠ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ብሔሮሙ ።

ያገራቸውን ፡ ዕንጨት ፡ ሁሉ ፡ ጨፈጨፈው ፤ አንድም ፡ ኵሉ ፡ ብለህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያገራቸውን ፡ ዕንጨት ፡ ጨፈጨፈው ።

፴፯ ፡ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ አንበጣ ።

ጌታ ፡ አንበጣ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ መጣ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ አንበጣ ፡ ይምጣ ፡ ብለው ፡ ጸለዩ ፤ መጣ ። አንበጣ ፡ የሚ ለው ፡ በራሪው ፡ ነው ።

፴፰ወደንብያ ፡ ዘአልቦ ፡ ጕልኮ ።

ጌታ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ኩብኩባ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤ መጣ ። አንድም ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ኩብኩባ ፡ ይምጣ ፡ ብለው ፡ ጸ ለዩ ፤ መጣ ። ዘፍ ፡ ፰ ፡ ፲፱ ። ፲፮ ፡ ፭ ።

፴፱ ፡ ወበልዐ ፡ ኵሉ ፡ ፍሬ ፡ ምድሮሙ ።

የምድራቸውን ፡ አዝመራ ፡ ሁሉ ፡ በላ ፡ አንድም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የም ድራቸውን ፡ አዝመራ ፡ በላ ።

፵ ፡ ወቀደመ ፡ ኵሉ ፡ ተግባሮሙ ።

አስቀድሞ ፡ የደረሰ ፡ መከራቸ ውን ፡ በላባቸው ፡ እንደ ፡ ጠበል ፡ እንደ ፡ ፈሾ ፡ ያለውን ።

፵፩ ፡ ወቀተለ ፡ ኵሉ ፡ በኵረ ፡ ብሔሮሙ

ያገራቸውን ፡ በኵር ፡ ሁሉ ፡ ገደ ለባቸው ፡ እምበኵረ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይውዕል ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መን

ግሥት ፣ እስከ ፣ በሱረ ፣ አመት ፣ ዘትውዕል ፣ ታሕተ ፣ እግረ ፣ ማሕ
ረፅ ፣ እንዲል ። ዘፍ ፣ ፲፪ ፣ ፲፫ ።

ሰባኒ ፣ መአውፅአሙ ፣ በወርቅ ፣ ወበብሩ፡
ወርቅ ፣ ብር ፣ ሰጥቶ ፣ አወጣቸ
ው ። አንድም ፣ በወርቅ ፣ በብር ፣
አስጊጦ ፣ ሰደዳቸው ። ጌታ ፣ ሙ
ሴን ፣ አሐቲ ፣ ተርፈተኒ ፤ ሞተ ፣
በሱር ፣ የማመጣ ፣ ነኝና ፣ መሥ
ዋዕት ፣ ሠውታችሁ ፣ ደሙን ፣
መቃን ፣ መድረኩን ፣ እርጩት ፣
ያን ፣ እያየ ፣ ሞተ ፣ በሱር ፣ እን
ዲመለስ ፣ አለው ፤ እስራኤልም ፣
ያዘዛቸውን ፣ እንዳዘዛቸው ፣ አደ
ረጉ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ በግብፃውያን ፣
ሞተ ፣ በሱር ፣ አመጣባቸው ፣ የግ
ብፃውያንን ፣ በሱር ፣ እያጠፋ ፣
ከእስራኤል ፣ ከተማ ፣ ደረሰ ፣
ደመ ፣ በግዕን ፣ አይቶ ፣ ፈራ ፤
ወሶበ ፣ ርዕየ ፣ ደመ ፣ በግዕ ፣
ፈርሃ ፣ ሞተ ፣ በሱር ፣ አእመረ ፣
ወለበወ ፣ ሞተ ፣ እግዚእነ ፣ ይላ
ል ፣ በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ድል ፣
ይነሳኝ ፣ ይሆን ፣ ብሎ ፣ ተመ
ልሶ ፣ የግብፃውያንን ፣ በሱር ፣
ይፈጽም ፣ ዝመረ ። የግብፅ ፣ ሰ
ዎች ፣ ሂደው ፣ አንተ ፣ በሱር ፣
ሚስትህ ፣ ልጅህ ፣ በሱር ፣ እላ
ንት ፣ ካለቃችሁ ፣ መንግሥቱ ፣
ለማን ፣ ይሆናል ፣ አትሰድዷቸ
ውምን ፣ ብለዋቸዋል ፤ ልጆቻ
ችሁን ፣ ትታችሁ ፣ ሂዱ ፣ አሏ
ቸው ፣ መሥዋዕት ፣ መሠዋት ፣
ከቀረ ፣ ብዙ ፣ ዘመን ፣ ሁኗል ፣
ልጆቻችንማ ፣ ከቀሩ ፣ በኋላ ፣ ዘ
መን ፣ ማንን ፣ አብነት ፣ አድር
ገው ፣ ይሠዋሉ ፣ ከብቶቻችሁን ፣
ትታችሁ ፣ ሂዱ ፣ አሏቸው ፤ ፈጣ
ሪያችን ፣ ፈረስ ፣ በቅሎ ፣ አህያ ፣
ላም ፣ በሬ ፣ በግ ፣ ፍየል ፣ ሠዉ ፣
ይለን ፣ እንደሆነ ፣ አናውቅ ፣
አሉ ፣ ውሰዱ ፣ አሏቸው ፤ በዚህም ፣
ላይ ፣ መክፈልት ፣ ሲሹ ፣ መቅ
ሠፍት ፣ እንዲሉ ፣ መሥዋዕት ፣
ስትሠዉ ፣ ንጹሕ ፣ ልብስ ፣ ለብ
ሳችሁ ፣ ሠዉ ፣ ይለናል ፣ እንዴት ፣
እናድርግ ፣ አሉት ፣ ለይትወሀስ ፣
ገብር ፣ እምእግዚኡ ፣ ወአመት ፣
እምእግዝእታ ፣ ወኃዳሪት ፣ እም
ኃደርታ ፣ ወንድ ፣ ባሪያ ፣ ከጌ
ታው ፣ ሴት ፣ ባሪያ ፣ ከመቤቷ ፣
ይዋሱ ፣ ብሎ ፣ ዐዋጅ ፣ ነገረላ
ቸው ፤ በስንት ፣ ቀን ፣ ትመለሳ
ላችሁ ፣ አላቸው ፤ ምሕዋረ ፣
ሠሉስ ፣ ዕለት ፣ ሰጊደነ ፣ ንገብዕ ፣
ጎቤክሙ ፣ አሉት ፤ በልብሰ ፣
ሕስት ፣ ምክንያት ፣ ገንዘባቸው
ን ፣ ዘርፈዋቸው ፣ ወጥተዋልና ፣
እንዲህ ፣ አለ ። ዘፍ ፣ ፲ ፣ ፳፬ ፣ ፳፱ ።

መአልቦ ፣ ደዌ ፣ ውስተ ፣ ሕዝቦሙ ።

በወገኖቻቸው ፣ በእስራኤል ፣ ግን ፣
ይህ ፣ ሁሉ ፣ ደዌ ፣ የልባቸውም ።

፵፮ ፡ ወተፈሥሑ ፡ ግብፅ ፡ በፀዐቶሙ ።

በእስራኤል ፡ መውጣት ፡ ግብፃውያን ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

አስመ ፡ ፈርሀዎሙ ።

ግብፃውያን ፡ በመቅሠፍት ፡ እንዳ ያጠፏቸው ፡ እስራኤልን ፡ ፈርተ ዋቸው ፡ ነበርና ፤ አንድም ፡ እስ ራኤል ፡ ከግብፅ ፡ በመውጣታቸው ፡ ደስ ፡ አላቸው ። እስመ ፡ ፈርሀዎሙ ፡ ግብፃውያንን ፡ ፈርተዋቸው ፡ ነበ ርና ።

፵፱ ፡ አንጠልዐ ፡ ደመና ፡ ወሠወሮሙ ።

ደመና ፡ ጋርዶ ፡ ሠወራቸው ። አንድም ፡ ደመና ፡ ጋረደላቸው ። ሠወራቸውም ።

እሳትኒ ፡ ከመ ፡ ያብርህ ፡ ሎሙ ፡ በሌሊት

እሳተኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እሳትንም ፡ በሌሊት ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘላቸው ። አንድም ፡ እሳትኒ ፡ እሳትም ፡ በሌሊት ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ ታዘዘላቸው ። ከግብፅ ፡ ወጥተው ፡ በበረኃ ፡ ሳሉ ፡ ሰባት ፡ ደመና ፡ ታዝዞላቸዋል ፤ አንዱ ፡ ከላይ ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ እንዳያገ ኛቸው ፡ ይጋርድላቸዋል ፤ አንዱ ፡ ከታች ፡ እሾህ ፡ እንቅፋት ፡ እን ዳያገኛቸው ፡ ይጐዘጉዝላቸዋል ፤ አንዱ ፡ በፊት ፡ አንዱ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ በቀኝ ፡ አንድ ፡ በግራ ፡ ይሆንላቸዋል ፤ ሰባተኛው ፡ የሁ ለት ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጕዳና ፡ ሲጠ ርግላቸው ፡ ውሎ ፡ ማታ ፡ እንደ ፡ ወምደ ፡ ብርሃን ፡ ሁኖ ፡ በደ ብተራ ፡ አሪት ፡ ላይ ፡ ሲያበ ራላቸው ፡ ያድራል ። ፈርያን ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሰገነት ፡ ወጥቶ ፡ ቢመለከት ፡ ከተማይቱ ፡ ጫ ፡ ብላ ፡ አይቶ ፡ ወይኔ ፡ ወይ ፡ ከገንዘቤ ፡ ወይ ፡ ከባሮቼ ፡ ሳል ሆን ፡ ቀረሁ ፡ ብሎ ፤ ጫን ፡ ታጠቅ ፡ አለ ። ሠራዊቱን ፡ አስከትቶ ገሥግሶ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ የተጓዙ ትን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ደረሰባቸው ። ወሰሰለ ፡ ደመና ፡ እምቅድሜሆ ሙ ፡ ወኃለፈ ፡ እንተ ፡ ድኅሬ ሆሙ ፡ ይላል ፡ መንገድ ፡ ጠ ራጊ ፡ ደመና ፡ ሂዶ ፡ ተጋርዶላ ቸው ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ እየተሰ ማሙ ፡ ባንድ ፡ ችካል ፡ ከብታቸ ውን ፡ እያሠሩ ፡ ሳይገኙ ፡ ተጉ ዘዋል ። ዘፀ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ - ፳ ።

፵፯ ፡ ሰአሉ ፡ ወመጽአ ፡ ፍርፍርት ።

ሥጋ ፡ ለመኑ ፡ ድርጭት ፡ የባ ሕር ፡ ዶሮ ፡ መልኳ ፡ ከሻዋ ፡ ውስጢ ፡ ሥብ ፡ ነው ፡ መጣላ ቸው ፡ (ታዘዘላቸው) ።

ወአጽገቦሙ ፡ ኅብስተ ፡ ሰማይ ።

ከሰማይ ፡ የወረደውን ፡ የተገኘ ውን ፡ ኅብስት ፡ አብልቶ ፡ አጠ ገባቸው ። ዘፀ ፡ ፲፮ ፡ ፲፫ ።

ግእ ፡ አንቅዐ ፡ ኰሐሐ ፡ ወአውጽዘ ፡ ማየ

ወሀ ፡ ከሞንጫ ፡ አፈለቀላቸው ።

ወሐሩ ፡ ውስተ ፡ አፍላግ ፡ በድው ።

ወንዝ ፡ ለወንዝ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ፤ አንድም ፡ እምአፍላግ ፡ በድወ ፡ ወንዙን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ፤ አንድም ፡ ውስተ ፡ አፍላግ ፡ በድወ ፡ በወንዙ ፡ ወደ ፡ በረኃ ፡ ሄዱ ።

ግፈ ፡ እስመ ፡ ተዘከረ ፡ ቃሎ ፡ ቅዱሰ ፡ ዘነበ ፡ አብርሃም ፡ ኀብሩ ።

ዘምስለ ፡ አብርሃም ፡ ሲል ፡ ነው ። ከባለሟሉ ፡ ካገልጋዩ ፡ ከአብርሃም ፡ ጋራ ፡ የተማማለውን ፡ ፅኑ ፡ መሐላውን ፡ አስቦአልና ፡ አሁን ፡ ዘንግቶት ፡ ኑሮ ፣ አሰበው ፡ ግለት ፡ አይደለም ፤ አደረገው ፡ ፈጸመው ፡ ሲል ፡ ነው ። ዘፀ፡፪፡ ፳፬

ግፍ ፡ ወአውጽአሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በትፍሥሕት

ወገኖቹ ፡ እስራኤልን ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ከግብፅ ፡ አወጣቸው ።

ወለኅሩያኑ ፡ በሕሤት ።

ለክህነት ፡ ለመንግሥት ፡ የመረጣቸው ፡ እስራኤልን ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ አወጣቸው ።

ግፉ ፡ ወወህቦሙ ፡ በሐውርተ ፡ አሕዛብ ።

የአሕዛብን ፡ አገር ፡ ሰጣቸው ።

ወወረሱ ፡ ሣሃ ፡ ባዕድ ።

ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ አሕዛብ ፡ የደከሙበትን ፡ ወረሱ ፡ ማለት ፤ የታነፁ ፡ ግምባቸውን ፡ ያደረሰ ፡ መከራቸውን ፡ አወረሳቸው ። ዳን፡፲፩፡ ፳፯

ግዴ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕጎ ።

እንዲህም ፡ ማድረጉ ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወይኅሱ ፡ ሥርዓቶ ።

ይጎሥሙም ፡ ይላል ፤ ሕጉን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ኢታምልክን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሕዝ ፡ ፲፩ ፡ ፳ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፩ ።

ሃሌ ። ሉያ ።

ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ።

ፅ ፡ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር። ዕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤

ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፡ ችር ፡ ነውና ፡ ቸር ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ። መዝ ፡ ፻፮ ፡ ፩ ። ፻፻፲፮ ፡ ፩ ። ፻፻፸፭ ፡ ፩ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለሆነ ፤ አንድም ፡ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለሆነ ።

፻፻ወመኑ፡ይነግር፡ኃያሉ፡እግዚአብሔር።

ይገብር ፡ ይቀድማል ፡ የ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ን ፡ ሕጉን ፡ ለራሱ ፡ የሚሠራ ።

ወይገብር ፡ ከመ ፡ ይስማዕ ፡ ኵሉ ፡ ስ ብ ሐ ቲ ሁ ።

ይነግር፡ሲል፡ነው፤ ለሌላው ፡ የሚ ያስተምር ፡ ማን ፡ ነው ፤ (ከመ ፡ ይስማዕ) ፡ ንዑ ፡ ኀቤየ ፡ ያለውን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ ኃይ ልና ፡ ስብሐት አንድ ፡ ወገን ፡ ተአምራቱን ፡ የሚያስተምር ፡ ማ ን ፡ ነው ፡ (ከመ ፡ ይስማዕ) ፡ የሚ ያስተምረው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንዲሰማ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስተ ምር ፡ ማን ፡ ነው ።

ፎ ፡ ብዑዓን ፡ አለ ፡ የዐቅቡ ፡ ፍትሐ ።

ፍርድ ፡ የሚጠነቅቁ ፡ ሕግ ፡ የሚ ጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡ ራን ፡ ናቸው ።

ወይገብሩ ፡ ጽድቀ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛውን ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ማለት ፡ ቸርነ ትን ፡ ለሰው ፡ የሚያደርጉ ።

ፙ ፡ ተዘከረን ፡ እግዚኦ ፡ በሣህልከ ፡ ሕ ዝ በ ከ ።

ተዘከረን ፡ ካለ ፡ ለሕዝብከ ፡ ሕዝ በከ ፡ ካለ ፡ ተዘከር ፡ ባለ ፡ በቀና ፡ ነበር ፡ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ እኛን ፡ ወገኖችህን ፡ በቸ ርነትህ ፡ አስበን ።

ወተሣሃለን ፡ በአድኅኖትከ ።

በትድግናህ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ፚ ፡ ከመ፡ንርአይ፡ሠናያተ፡ለኅሩያኪከ

የነቢያት ፡ የካህናትን ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በፍሥሐ፡ሕዝብከ።

በወገኖችህ ፡ በነቢያት ፡ በካህ ናት ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ንክበር ፡ ምስለ ፡ ርስትከ ።

ርስትህ ፡ ጉልትህ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከነ ቢያት ፡ ከካህናት ፡ ጋራ ፡ እን ከብር ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ (ከመ ፡ ንርአይ) ፡ የሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እናይ ፡ ዘንድ ። (ወከመ ፡ ንትፈሣሕ) ፡ በሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ (ወከመ ፡ ንክበር) ፡ ርስትህ ፡ ጉልትህ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከሁ ለቱ ፡ ነገድ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ከብረን ፡ ገንነን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ይላሉ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድ ።

ፚ ፡ አዘስን ፡ ምስለ ፡ አዘዊን ።

ትሩፍ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መኩራ ፡ የመጣብህ ፡ ብትበድል ፡ አይደ ለምን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ብን በድልም ፡ ካባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ እንዳባቶቻችን ፡ በደልን፡አት፡ ሣ፡ ኛሄ ፡ ኤር ፡ ፲፬ ፡ ፳ ።

ዓመፅነሂ ፡ ውጊያን ።

፪ ፡ ወነሥዓ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወየብሰት

ፊጽመን ፡ በደልን ።

ኤርትራን ፡ አርምሚ ፡ ተፈፀሚ ፡ ብሎ ፡ ገሠጻት ፡ (ወየብሰት) ፡ ከሥስት ፡ ካራት ፡ ተከፈለች ።

፮ ፡ ወአበውነሂ ፡ በብሔረ ፡ ግብፅ ፡ ኢያእመሩ ፡ መንክረከ ።

ወመርሐመ ፡ በቀላይ ፡ ከመ ፡ ዘበገዳም ።

አባቶቻችንም ፡ በግብፅ ፡ ሳሉ ፡ ያደረግህላቸውን ፡ ተአምራት ፡ አላወቁም ፡ ነበር ፤ በኛ ፡ ብርቁ ፡ ድንቁ ፡ ምንድን ፡ ነው ። አሁን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ኃጢአት ፡ ማዘከር ፡ አይደለም ፡ እልያ ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተው ፡ ቢመለሱ ፡ ይቅር ፡ አልሃቸው ፡ እኛም ፡ ኃጢአት ፡ ሠርተን ፡ ከተመለስን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

፯ ፡ ወአንገፎሙ ፡ ፡ እምእደ ፡ ጸሮ ሙ ። ሎቃ ፡ ፩ ፡ ፸፩ ።

ወአተዘከሩ ፡ ብዝኃ ፡ ምሕረትከ ።

እምእደ ፡ ጸላእቶሙና ፡ እምእደ ፡ ፀሮሙ ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ ከጠላቶቻቸው ፡ ከግብፃውያን ፡ እጅ ፡ አስለቀቃቸው ።

ብዙኃ ፡ ምሕረተከም ፡ ይላል ፡ የቸርነትህን ፡ ብዛት ፡ አንድም ፡ ብዙ ፡ የሚሆን ፡ ቸርነትህን ፡ አላወቁም ፡ ነበረ ።

፰ ፡ ወአምሰጠሙ ፡ ለባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ወየብሰት ፡ ከመ ፡ ዘበገዳም ።

፲ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ እምእደ ፡ ጸላኢ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ እምእደ ፡ ፀላፊ ።

ወአምሰጠሙ ፡ ለባሕረ ፡ ኤ ር ት ራ ።

የተከተሏቸው ፡ የከበቧቸው ፡ ግብፃውያንን ፡ ግን ፡ ባሕር ፡ ቀበራቸው ።

ኤርትራንም ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ አሳዝነውህ ፡ ነበረ ።

፲፩ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ።

ወአተረፈ ፡ አሐዱ ፡ እምውስቴቶሙ ።

ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስላለ ፡ አዳናቸው ፡ እንጂ ፡ ማለት ፡ አዳንካቸው ፡ እንጂ ፡ ሲል ፡ ነው ።

ከእስራኤል ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ፡ ሁሉም ፡ ተሻገሩ ፡ እንጂ ። አንድም ፡ ከግብፃውያን ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ፡ ሁሉም ፡ ሠጠሙ ፡ እንጂ ። ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ፡ ፴፩ ።

፲፪ ፡ ወአምኑ ፡ በቃሉ ።

ከመ ፡ ያርእዮሙ ፡ ኃይሉ ።

ለጊዜው ፡ አወርሰከሙ ፡ ባለው ፡ ቃሉ ፡ አመኑ ።

ከሃሊነቱን ፡ ይገልጽላቸው ፡ ዘንድ ።

ወሰብሕዎ ፡ በሰብሓቲሁ ።

በጥንተ ፡ ምስጋናው ፡ አመሰገ
ኑት ። ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፴፩ ።

፲፫ ፡ ወአፍጠኑ ፡ ረሲዓ ፡ ምግባሩ ።

ረሲዓ ፡ ምግባሮም ፡ ይላል ፡ ኃላ ፡
ግን ፡ ፈጥነው ፡ ሥራውን ፡ ዘነጉ ፡
አንድም ፡ ሥራውን ፡ መዘንጋት ፡
አፈጠኑ ።

ወኢተዓገሡ ፡ በምክሩ ።

አወጣችኋለሁ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡
(ነገር) ፡ አልፀኑም ፤ በሕጉ ፡ አል
ኖሩም ፡ ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፳፭ ። ፲፮ ፡ ፪ ።

፲፬ ፡ ወፈተዉ ፡ ፍትወተ ፡ በገዳም ።

በበረኃ ፡ ሳሉ ፡ የማይገባ ፡ ተም
ኔት ፡ ተመኙ ። የግብፃውያን ፡
ወንድ ፡ ወንዱ ፡ አልቆ ፡ ሴት ፡
ሴቱ ፡ ቀርቷል ፡ አንዳንዲቱን ፡
አግብተን ፡ እንኑር ፡ ብለዋልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ።

ወአምረርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በበድው
እግዚአብሔርን ፡ በበረኃ ፡ ሳሉ ፡
አሳዘኑት ።

፲፭ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ዘሰአሉ ።

እሱ ፡ ግን ፡ የለመኑትን ፡ ሁሉ ፡
ሰጣቸው ፡ ወሀ ፡ ቢሉ ፡ ወሀ ፡
መና ፡ ቢሉ ፡ መና ።

ፈነወ ፡ ጽጋበ ፡ ለነፍሶሙ ።

ለሰውነታቸው ፡ የሚያሻቸውን ፡
ምግብ ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ።

፲፮ ፡ ወአምዕዕዎ ፡ ለሙሴ ፡ በትዕይንት ።

ሙሴን ፡ በከተማቸው ፡ አሳዘኑት ።

ወለአሮን ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ።

ፅኑዓ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡረ ፡
እግዚአብሔር ፡ አሮንንም ፡ አሳ
ዘኑት ።

፲፯ ፡ አብቀወት ፡ ምድር ፡ ወውሕጠቶ ፡
ለዳታን ።

ዳታንን ፡ ምድር ፡ ተከፍታ ፡ አሠ
ጠመችው ።

ወደፈነቶሙ ፡ ለተዓይነ ፡ አቤሮን ።

አቤሮንንም ፡ ከነከተማው ፡ ከነ
ሠራዊቱ ፡ አሠጠመችው ።

፲፰ ፡ ወነደ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ተዓይኒሆሙ
ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ፳፯ ፡ ፲፯ ።

በሰፈራቸው ፡ በከተማቸው ፡ እ
ሳት ፡ ነደደ ፤ አንድም ፡ መቅሠ
ፍት ፡ ታዘዘ ።

ወአውዐዮሙ ፡ ነበልባል ፡ ለኃጥኣን ።

ኃጥአን ፡ ዳታንና ፡ አቤሮንንም ፡
የእሳት ፡ ላንቃ ፡ አቃጠላቸው ።
(ታ) ፡ ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ ነገደ ፡ ሌዊ ፡ ዳ
ታንና ፡ አቤሮን ፡ ነገደ ፡ ይሁዳ ፡
ናቸው ።

ደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ በአሮን ፡ ዳታንና ፡
አቤሮን ፡ በሙሴ ፡ እሱና ፡ ወን
ድሙ ፡ መንግሥትን ፡ ከክህነት ፡
አንድ ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ሌዊ ፡

አይወልደንም ፡ እኛስ ፡ ከበዙሩ ፡ ከሮቤል ፡ ተወልደን ፡ የለምን ፡ ብለው ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡባቸው ፤ ካህናት ፡ ፈሊጥ ፡ አዋቆች ፡ ናቸውና ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተነሣን ፡ እንደሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ የምቀኝነት ፡ እንደሆነ ፡ ያውቁብናልና ፡ እኛ ፡ አስቀድመን ፡ ክህነታችንን ፡ በሙሴ ፡ ዳኝነት ፡ እጅ ፡ እናድርግ ፡ እላንተም ፡ በኛ ፡ ዳኝነት ፡ ምስፍናችሁን ፡ እጅ ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ብለው ፡ ተሰብስበው ፡ ሄደው ፡ ሙሴን ፡ ሥጋ ፡ በገበታ ፡ (ነገር) ፡ በተርታ ፡ እንዲሉ ፡ ሹመት ፡ ፈንታችንን ፡ ስጠን ፡ እንሾም ፡ አሉት ። እሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አግኝቶ ፡ ተሹሞታል ፡ እላንተም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አግኝታችሁ ፡ ተሾሙት ፡ አላቸው ። ይህማ ፡ የማድላት ፡ አማርኛ ፡ አይደለምን ፡ ዛሬስ ፡ በገዛ ፡ ሹመታችን ፡ ሱባዔ ፡ ግቡበት ፡ ይለናል ፡ ሆነ ። ብለው ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ የሚበዙ ፡ ካህናት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ ለብሰው ፡ ማዕጠንት ፡ አበጅተው ፡ ይዘው ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ከደብተራ ፡ አሪት ፡ በር ፡ ቁመው ፡ ነበረ ። (ወሮድዎሙ ፡ ይላል) ፡ ገርምመዋቸው ፡ ገብተው ፡ ቢያጥኑ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኗቸውን ፡ ሳይነካ ፡ እንደ ፡ ተለበለበ ፡ ግንድ ፡ አድርጓቸዋል ። እንደምን ፡ ላድርጋቸው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢያመለክት ፡ እሳቸውን ፡ በመጐናጸፍያቸው ፡ እያወጣህ ፡ አፍስሳቸው ፡ ዕቃው ፡ ግን ፡ ክቡር ፡ ዕቃ ፡ ነውና ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ አሰራው ፡ ብሎታል ፡ ወተቀደሰ ፡ ማዕጠንታቲሆሙ ፡ በነፍሳቲሆሙ ፡ እንዲል ፡ ያዘዘውን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ። ዳታንና ፡ አቤሮንንም ፡ መሬት ፡ ተከፍታ ፡ አሥጥማቸዋለች ። ቆሬም ፡ ነገር ፡ ለማፅናት ፡ ሂዶ ፡ ነበር ፡ አብሮ ፡ ሠጥሟል ። ዘጉ ፡ ፲፯ ፡ ፩—፵ ።

፲፱ ፤ ወገብሩ ፡ ላሕመ ፡ በኮሬብ ።

በኮሬብ ፡ ስብኮ ፡ ላሕም ፡ አቆሙ ።

ወሰገዱ ፡ ለግልፎ ። ዘፀ ፡ ፴፪ ፡ ፩-፴፭ ። ሕገ ፡ ፵ ፡ ፲ ።

ለተቀረጸ ፡ ለተጐነፈ ፡ ጣዖት ፡ ሰገዱ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ።

፳ ፡ ወወለጡ ፡ ክብሮሙ ።

ክብራቸውን ፡ ለወጡ ።

በአምሳለ ፡ ላህም ፡ ዘይትረዐይ ፡ ሣዕረ ።

ወደ ፡ ሣር ፡ በሚሠማራ ፡ ሣርን ፡ በሚበላ ፡ ላም ፡ አምሳል ፡ ወርቅ ፡ ብራቸውን ፡ ለወጡ ። አንድም ፡ ወሊጠሙ ፡ ይላል ፤ ክብራቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለውጠው ፡ ሣርን ፡ በሚበላ ፡ ላሕም ፡ አምሳል ፡

የተሠራ ፤ ጣዖትን ፤ አመለኩ ።
ኤር ፤ ፪ ፤ ፲፩ ።

፳፭ ፤ ወረሥዕዎ ፤ ለእግዚአብሔር ፣ ዘአድኃኖሙ ።
ያዳናቸው ፤ እግዚአብሔርን ፤ ዘን ግተው ፤ ጣዖት ፤ አመለኩ ።

ዘገብረ ፤ ወቢያተ ፤ በግብፅ ።

በግብፅ ፤ ታላላቅ ፤ ተአምራት ፤ ያደረገ ፤ ማለት ፤ ዘጠኙን ፤ መቅ ሠፍት ፤ ያመጣ ፤ እሱን ፤ ረሥ ዕዎ ፤ ዘነጉት ። አንድም ፤ ያመጣ፡ እሱ ፤ ነው ። ኢሳ ፤ ፱፩ ፤ ፲፫ ።

፳፮ ፤ ወመንክረ ፤ በምድረ ፤ ካም ።

በካም ፤ ዕፃ ፤ ሞተ ፤ በሱርን ፤ ያደ ረገ ፤ እሱን ፤ ዘነጉት ። አንድም ፤ ሞተ ፤ በሱርን ፤ ያደረገ ፤ እሱ ፤ ነው ።
ወግሩመ ፤ በባሕረ ፤ ኤርትራ ።

በኤርትራ ፤ ባሕር ፤ ግሩም ፤ የሚ ሆን ፤ ሥጥመትን ፤ ያደረገ ፤ እግ ዚአብሔርን ፤ ዘነጉት ። አንድ ም ፤ ግሩም ፤ የሚሆን ፤ ሥጥመ ትን ፤ ያደረገ ፤ እሱ ፤ ነው ።

፳፯ ፤ ወይቤ ፤ ከመ ፤ ይሥርዎሙ ።

ያጠፋቸው ፤ ዘንድ ፤ አጠፋቸዋ ለሁ ፤ ባለ ፤ ጊዜ ፤

ሶበ ፤ አኮ ፤ ሙሴ ፤ ኀሩዩ ።

አማላጁ ፤ ሙሴ ፤ ባይሆን ፤ ቆመ ፤ ማንሻ ፤ እንድም ፤ ባለሟሉ ፤ ሙ ሴ ፤ ባማላጅነት ፤ ከፊቱ ፤ ባይ ቆም ።

ቆመ ፤ ቅድሜሁ ፤ አመ ፤ ብድብድ ።

ባለሟሉ ፤ ሙሴ ፤ ምን ፤ አደረገ ፤ ትለኝ ፤ እንደሆነ ፤ ዓባር ፤ ቸኑ ፈር ፤ በታዘዘበት ፤ ጊዜ ፤ ከእግ ዚአብሔር ፤ ፊት ፤ ባማላጅነት ፤ ቆመ ።

ከመ ፤ ይሚጥ ፤ መቅሠፍተ ፤ መዓቱ ።

ፈርዶ ፤ ያመጣውን ፤ መቅሠፍት፡ ይመልስ ፤ ዘንድ ።

ወከመ ፤ አይሥርዎሙ ።

ፈጽሞ ፤ አንድ ፤ ጊዜ ፤ እንዳያጠ ፋቸው ።

፳፱ ፤ ወመነኑ ፤ ምድረ ፤ መፍትወ ።

ለከ ፤ ወለዘርዕከ ፤ እሁበካሃ ፤ ለይ እቲ ፤ ምድር ፤ ብሎ ፤ ትንቢት ፤ ያናገረላቸውን ፤ ኢየሩሳምን ፤ ንቁ ዋል ፤ አቃልለዋልና ።

ወኢተአመኑ ፤ በቃሉ ።

ወኢተአመንዎ ፤ ለቃሉም ፤ ይ ላል ፤ አወርሰከሙ ፤ ባለው ፤ ቃ ል ፤ አላመኑም ።

፴፩ ፤ ወአንጐርጕሩ ፤ በውስተ ፤ ተ ዐ ይ ኒ ሆ ሙ ።

በለስ ፤ ወይን ፤ ከዚህ ፤ ወዴት ፤ አለ ፤ ብለው ፤ በከተማቸው ፤ ወ ስጥ ፤ አዘኑ ።

ወኢሰምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አል ሰሙም ፡ ማለት ፤ አልጠበቁም ።

ፀኀፈ ፡ ወአንሥአ ፡ እደው ፡ ላዕሌሆሙ ።

እሱም ፡ እንኪያስ ፡ ብሎ ፡ እደ ፡ መዓቱን ፡ አነሣባቸው ፡ (አመጣ ባቸው) ።

ከመ ፡ ይንዕኖሙ ፡ በገዳም ።

በበረኃ ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ማ ለት ፡ እንደ ፡ ሻሽ ፡ ተነጥፈው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈው ፡ እንደ፡ ግንድ ፡ ተረብርበው ፡ ይቀሩ ፡ ዘንድ ።

ፀፈፀ ፡ ወከመ ፡ ይንፃጎ ፡ ዘርዖሙ ፡ ውስተ አሕዛብ ።

የልጅ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ በአሕ ዛብ ፡ አገር ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ይዝርዎሙ ፡ ውስተ ፡ በሐውርት

ፋርስ ፡ ባቢሎን ፡ ፅርዕ ፡ ሚዶን ፡ ይበትናቸው ፡ ዘንድ ።

ፀፀ ፡ ወተፈዐሙ ፡ በብዔል ፡ ፈጎር ።

የብዔል ፡ ፈጎር ፡ ነን ፡ በማለት ፡ ተከተቡ ፡ (ሐ) ፡ በሐሳዊ ፡ መሲ ሕ ፡ ጊዜ ፡ ዘመርምያዋአስ ፡ ተብለ ው ፡ እንዲከተቡ ። አንድም ፡ ፈጎር ፡ ካህነ ፡ ጣዖት ፡ ነው ፤ ፈጎር ፡ የሚ ባል ፡ ካህነ ፡ ጣዖት ፡ ላቆመው ፡ ጣዖት ፡ የፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ተ ቀቡ ። በግዐ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲል ፡ በግዐ ፡ ቅብዓት ፡ ሲል ። አንድም ፡ ፈጎር ፡ የሚባል ፡ ጋኔን ፡ ላደረ በት ፡ ጣዖት ፡ ሰጌዱ ፤ መስገድ ፡ እንጂ ፡ በፊት ፡ ነው ። አንድም ፡ ፈጎር ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ የቆመ ፡ ጣዖትን ፡ በማምለክ ፡ ተፈጸሙ ፡ አለቁ ።

ወበልዑ ፡ መሥዋዕተ ፡ ምዉታ ።

ምውት ፡ መሥዋዕትን ፡ በሉ ፤ ሕያው ፡ መሥዋዕት ፡ አለና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፤ የማያድን ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ መሥዋ ዕተ ፡ ምውት ፡ ይላል ፡ ለምውት ፡ ጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ በሉ ።

ፀፀ፩ ፡ ወወሀከም ፡ በምግባረሆሙ ።

እግዚአብሔርን ፡ በሥራቸው ፡ አነሣሡት ፡ ማለት ፤ ቅሠፈን ፡ ቅሠፈን ፡ አሉት ።

ወበዝኃ ፡ ብድብድ ፡ ላዕሌሆሙ ።

አባር ፡ ቸነፈር ፡ በዛባቸው ፡ ማ ለት ፤ ፀናባቸው ።

፴ ፡ ተንሥአ ፡ ፊንሐስ ፡ ወአድኃኖሙ ።

ፊንሐስ ፡ በሥራ ፡ ተነሥቶ ፡ አዳ ናቸው ።

፴፩ ፡ ኀደገ ፡ ብድብድ ፡ ወተኰለቈ ፡ ጽድቀ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

አባር ፡ ቸነፈር ፡ ፀጥ ፡ አለ ፡ እ ስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ ለልጅ ፡

ልጅ ፡ (ተጐለቆ ፡ ጽድቀ) ጽድቅ ፡ ሁኖ ፡ ተሰጠው ፡ ከጽድቅ ፡ ተቈጠረለት ፡ (ታ) ፡ በለዓም ፡ የሚባል ፡ ሀብተ ፡ መርገም ፡ የተሰጠው ፡ ነበረ ፤ ባላቅ ፡ ወልዶ ፡ ሶፎር ፡ ግብፃውያንን ፡ በባሕር ፡ ያሠጠመ ፡ ዓግ ፡ ሲዎንን ፡ ንጉሥ ፡ አራድን ፡ ያጠፋ ፡ ጦር ፡ የማይመልሰው ፡ ኃይለኛ ፡ ጠላት ፡ መጥቶብኛልና ፡ መጥተህ ፡ ረግመህ ፡ አጥፋልኝ ፡ ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በፅንቊ ፡ አንፅልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፤ እደሩ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ልጠይቀው ፡ አላቸው ፡ አደሩ ፤ ፀውዓኒ ፡ ባላቅ ፡ ወልዶ ፡ ሶፎር ፡ እመስጴጦምያ ፡ ዘሶርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ርግሞ ፡ ሊተ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወፀዓሎ ፡ ሊተ ፡ ለእስራኤል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ አትሂድ ፡ አለው ፤ አልሆነላችሁም ፡ ሂዱ ፡ አላቸው ፤ ሄዱ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያንሰው ፡ መላክተኞቹ ፡ ተራ ፡ ቢሆኑበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አሲዞ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ አድርጎ ፡ ላከ ፤ እደሩ ፡ ፈጣሪዬን ፡ ልጠይቅ ፡ አላቸው ፡ ጠየቀው ፤ ሂድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አትርገም ፡ አለው ። ነገሩ ፡ ቀዋሚ ፡ አይደለምሳ ፡ መላላሽ ፡ ነውሳ ፡ ከሄድሁስ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ መርገሙን ፡ እያሰላሰለ ፡ ሲሄድ ፡ መልአኩ ፡ ሰይፉን ፡ መዝዞ ፡ ላህያው ፡ ታያት ፤ ፈርታ ፡ ቆመች ፤ ሂጂ ፡ እያለ ፡ ይመታት ፡ ዝመረ ፡ መልአኩ ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ፤ እልፍ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፤ ሂጂ ፡ እያለ ፡ ይመታት ፡ ዝመረ ፡ በሦስተኛው ፡ ከቅጽርና ፡ ከቅጽር ፡ መሐል ፡ ይዛው ፡ ገባች ። ወመለጠቶ ፡ እገሪሁ ፤ እግሩን ፡ ላጠችው ። አሮጌ ፡ ነቢይ ፡ ብለሽ ፡ ነው ፡ ብያ ፡ እንዲህ ፡ የምትጫወችብኝ ፡ ጦር ፡ በኖረኝ ፡ በወጋሁሽ ፡ ሰይፍ ፡ ቢኖረኝ ፡ በመታሁሽ ፡ ነበር ፡ አላት ፤ አኮኑ ፡ ዕድግትከ ፡ ዘትፄዓንኒ ፡ እምንዕስከ ፡ ከሕፃንነትህ ፡ ጀምሮ ፡ የምትቀመጥብኝ ፡ አህያህ ፡ አይደለሁምን ፡ ዳገቱን ፡ ውጭ ፡ ሜዳውን ፡ ሩጭ ፡ ብትለኝ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ እንቢ ፡ ብዬህ ፡ አውቃለሁ ፡ ካንተ ፡ የሚበልጥ ፡ መልአኩን ፡ አይቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አለችው ፤ ለሱም ፡ ተገልጾለት ፡ ፈርቶ ፡ ወርዶ ፡ ልመለስን ፡ አለው ፡ መሆኑን ፡ ሂድ ፤ ባሕቱ ፡ ዘወደየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ ኪያሁ ፡ ተዓቀብ ፡ ለነቢብ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልህን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አትናገር ፡ አለው ፤ ሄደ ፤ ባላቅ ፡ ወልደ ፡ ሶፎር ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ስለ ፡ መጣሁ ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ አለው ። ዘኍ ፡ ፳፪ ፡ ፭—፵፩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡

መሥዋዕት ፡ ሠውቶ ፡ ከመሥዋዕትህ ፡ ቁም ፡ አለው ፤ እያሚረተ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሂዶ ፡ ምንተ ፡ እረግም ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ኢረገመ ፡ ወምንተ ፡ እፄዕል ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ኢጸወለ ፡ አለ ፤ እርግምልኝ ፡ ብልህ ፡ ትመርቃቸዋለህን ፡ አለው ፤ ቀድሞስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለፀልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ ብዬ ፡ ነግሬህ ፡ የለምን ፡ አለው ፤ መሥዋዕት ፡ ቢያንስበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሰባት ፡ ላመ ፡ ሰባት ፡ በግ ፡ ሰባት ፡ ፍየል ፡ ሠውቶ ፡ እርገምልኝ ፡ አለው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ እያሚረተ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሂዶ ፡ ናሁ ፡ እምአርእስተ ፡ አድባር ፡ እሬእዮ ፡ ወእምአርእስተ ፡ አውግር ፡ እሌብዎ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ ምስሌሁ ፡ ሕዝብ ፡ ዘባሕቲቱ ፡ የኃድር ፡ አለ ፤ ይህ ፡ ሁለተኛህ ፡ ነው ፡ እርገምልኝ ፡ ብልህ ፡ ትመርቃቸዋለህን ፡ አለው ፤ ቀድሞስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ ብዬ ፡ ነግሬህ ፡ የለምን ፡ አለው ፤ ሰው ፡ ቢበዛበት ፡ ዓይን ፡ ቢፈራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ከሌለበት ፡ ወስዶ ፡ እርገምልኝ ፡ አለው ፡ ሚ ፡ ይሚኒ ፡ ተዓይኒከ ፡ ያዕቆብ ፡ ወእፎ ፡ አብያቲከ ፡ እስራኤል ፡ ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ወያዓትት ፡ ኃጢአተ ፡ እምእስራኤል ፡ አለው ፤ ደገኛው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሦስተኛህ ፡ ነው ፡ እርገምልኝ ፡ ብልህ ፡ ትመርቃቸዋለህን ፡ አለው ።

ቀድሞስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጸልኝን ፡ ነው ፡ የምናገር ፡ ብዬ ፡ ነግሬህ ፡ የለምን ፡ አለው ፤ ለኔማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ላንተ ፡ ቀረብህ ፡ ቤትህን ፡ በወርቅ ፡ በዕንቍ ፡ አንጽልሃለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበረ ፡ ቀረብህ ፡ እንጂ ፡ አለው ፤ ከብተ ፡ ነቢ ፡ እንዲሉ ፡ መቼስ ፡ አንተ ፡ የምትሻው ፡ ጥፋታቸውን ፡ አይደለምን ፡ አለው ፤ ሌላ ፡ ምን ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፡ እንክያስ ፡ ቁሜ ፡ ረግሜ ፡ ባላጠፋ ፡ ተቀምጬ ፡ ረግሜ ፡ (መክሬ) ፡ አጠፋልሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ በመና ፡ የተናደደ ፡ እስራኤል ፡ ሴት ፡ ሲያይ ፡ አያስችለውምና ፡ ሕፃናቱን ፡ ሴቶች ፡ ጣዖቱን ፡ አሳዝለህ ፡ ስደዳቸው ፡ እንድረስባችሁ ፡ ይሏቸዋል ፤ ለዚህ ፡ ስገዱ ፡ ይህን ፡ ብሉ ፡ ይበሏቸው ፡ ይሰግዳሉ ፡ ይበላሉ ፤ ፈጣሪያቸው ፡ ለአምልኮቱ ፡ ቀናዒ ፡ ነውና ፡ ያጠፋልሃል ፡ አለው ፤ እንደ ፡ ነገረው ፡ አድርጎ ፡ ሰደዳቸው ፤ እንዳለውም ፡ ተሻምተው ፡ እንድረስባችሁ ፡ አሏቸው ፤ ለዚህ ፡ ሰገዱ ፡ ይህን ፡ ብሉ ፡ አሏቸው ፡ ሰገዱ ፡

በሉ ፡ ቸነፈር ፡ ይፈጃቸው ፡ ጀ
መረ ፡ የይሁዳ ፡ የቤት ፡ አለቃ ፡
ዘምሪ ፡ ይባላል ፡ የአሕዛብ ፡ የቤ
ት ፡ አለቃ ፡ ልጅ ፡ ክስቢ ፡ ትባላ
ለች ፡ ተጠቃቅሰው ፡ ከእልፍኝ ፡
አንድም ፡ ከጕድጓዳ ፡ መሬት ፡
ሲገቡ ፡ ብላቴና ፡ አይቶ ፡ ለፊን
ሐስ ፡ ነገረው ፡ ለመባዕ ፡ የመጣ ፡
ዘገር ፡ ነበረ ፡ ያንን ፡ ይዞ ፡ ሂዶ ፡
ሥራቸውን ፡ ከሚሠሩበት ፡ አን
ድ ፡ አድርጎ ፡ ወጋቸው ፤ ፊንሐስ ፡
ወልደ ፡ አሮን ፡ ወልደ ፡ አልዓዛር ፡
አስተንፈስካ ፡ ለልብየ ፡ ብሎታል ፤
ቸነፈሩም ፡ ትታቸዋል ፡ በዚህም ፡
ምክንያት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ መዋ
ፅለ ፡ ክህነት ፡ ተሰጥቶታልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ። ዘጕ ፡ ፭፫ ፡ ፩-፴ ።
፬ ፡ ፩- ፭፩ ። ፭ ፡ ፩—፲፰ ።

፴፪ ፤ ወአምዕፅዎ ፡ በጎበ ፡ ማየ ፡ ቅስጥ።
ጸብ ፡ ክርክር ፡ ባለበት ፡ ውሃ ፡
አሳዘኑት ፤ ጌታና ፡ ሙቤ ፡ ሙሴና ፡
እስራኤል ፡ ተክራክረውበታልና ፡
እንዲህ ፡ አለ ።

ወሐመ ፡ ሙሴ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ዘፀ ፡
፲፮ ፡ ፩—፯ ።

ሙሴ ፡ በሳቸው ፡ ምክንያት ፡ ባለ
መክራ ፡ ሆነ ።

፴፫ ፤ እስመ ፡ አምረርዎ ፡ ለነፍሱ ።

ሰውነቱን ፡ አሳዝነዋታልና ።

ወአዘዘ ፡ በከናፍራሁ ።

ባንደበቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፤
ከዕለታት ፡ ባንዳቸው ፡ እስራ
ኤል ፡ ሙሴን ፡ ሙሴ ፡ ውሃ ፡
ሙሴ ፡ ውሃ ፡ እያሉ ፡ ዘበዘቡት ።
የወለደች ፡ እናት ፡ ያሳደገች ፡ ሞግ
ዚት ፡ ይመስል ፡ ምን ፡ ይዘበዝ
ቡኛል ፡ ብሎ ፡ ንሴብሐን ፡ ሳይ
ደግም ፡ ሰጣቸው ። ከዚያ ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ንሴብሐን ፡ ደግሞ ፡ እን
ክሙ ፡ ስትዩ ፡ ዘወሀበክሙ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ኪያሁ ፡ ሰብሑ ፡ ብሎ ፡
ነበር ፡ የሚሰጣቸው ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡
ግን ፡ ደክሞት ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡
ሳይል ፡ ሰጣቸው ፤ እነሱም ፡ ሳያ
መሰግኑት ፡ ጠጥተውታል ። ጌታ ፡
ሙሴን ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ኢትበውኦ ፡
ለኢየሩሳሌም ፡ በእንተ ፡ ዘኢቀ
ደስከኒ ፡ ብሎታል ። በዚህ ፡ ምክ
ንያት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አልገባም ፤
ምድረ ፡ ናባው ፡ ወድቆ ፡ ቀርቷል ።

፴፬ ፤ መኢሠረዉ ፡ አሕዛበ ፡ ዘይቤሎሙ
እግዚአብሔር ።

ሠርዉ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ እግዚ
አብሔር ፡ አጥፉ ፡ ያላቸውን ፡ አሕ
ዛብን ፡ አላጠፉምና። ፩ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፭፪

፴፭ ፤ ወተደመሩ ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ።

ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ በሥራ ፡ አንድ ፡
ሆኑ ።

ወተምህሩ ፡ ምግባሮሙ ።

የአሕዛብን ፡ ሥራ ፡ ተማሩ ፡ ማለ
ት ፡ ሠሩ ።

፴፯ ፡ ወተቀንዩ ፡ ለግልፎሙ ።

ለግልፎሙም ፡ ይላል ፤ ለተቀረጸ ፡ ለተጐነፈ ፡ ጣዖታቸውም ፡ ተገዙ ።

ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

ወከሖሙ ፡ ጌጋየ ።

ይኸውም ፡ ዕዳ ፡ ሆነባቸው ።

፴፯ ፤ ዘብሔ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወአዋልዲሆሙ ለአጋንንት ።

ወንድ ፡ ሴት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለአጋንንት ፡ ሠዉ ። ዘሌ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ዘዳ ፡

፴፱ ፤ ፲፮ ። ኤር ፡ ፴፪ ፡ ፴፭ ። ፭ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፳ ። ራእ ፡ ፱ ፡ ፳ ።

፴፰ ፤ ወከዐዉ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ።

ንጹሕ ፡ ደምን ፡ አፈሰሱ ።

ደመ ፡ ደቂቆሙ ፡ ወአዋልዲሆሙ ።

ንጹሕም ፡ ያልሁት ፡ የወንድ ፡ የሴት ፡ ልጆቻቸው ፡ ደም ፡ ነው ።

ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፭ ።

መሥዉ ፡ ለግልፎ ፡ ከነዓን ።

ከነዓን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ለሚያመልከው ፡ ጣዖት ፡ ሠዉ ። አንድም ፡ ከነዓን ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ለቆመ ፡ ጣዖት ፡ ሠዉ ።

መተቀትለት ፡ ምድር ፡ በደም ።

ተሜረየት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ምድር ፡ በደም ፡ ታለለች ። አንድም ፡ ተቀብዐት ፤ ደምን ፡ ተቀባች ፤ ተመስሐት ፡ ይላል ፡ በዐረቡ ፡ ተሜረየት ፡ ሲል ፡

፴፱ ፤ ወረኵሰት ፡ ምድር ፡ በምግባሪሆሙ ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፭ ።

ምድር ፡ በሥራቸው ፡ ጠፉች ።

ወዘመዉ ፡ በጣዖቶሙ ።

በጣዖታቸው ፡ ሰሰኑ ። መሰሰን ፡ ብቻ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ አይደለም ፤ ጣዖትም ፡ ማምለክ ፡ ሴሰኝነት ፡ ነውና ።

፵ ፤ ወተምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓተ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ፈጽሞ ፡ ፈረደባቸው ።

ወአስቈረሮሙ ፡ ለርስቱ ።

ርስቱ ፡ ጕልቱ ፡ የሚሆኑ ፡ እስራኤልንም ፡ ተጸየፋቸው ፡ ማለት ፤ በረድኤት ፡ ተለያቸው ።

፵፩ ፤ መአግብአሙ ፡ ውስተ ፡ እደ፡ዐሮሙ

በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አስማረካቸው ፡

ወቀንይዎሙ ፡ ጸላዕቶሙ ።

ጠላቶቻቸው ፡ ግብጻውያን ፡ አስጨንቀው ፡ አስጠብበው ፡ ገዟቸው ።

፵፪ ፤ ወአሕመምዎሙ ፡ ዐሮሙ ።

ጠላቶቻቸው ፡ መከራ ፡ አጸኑባቸው ።

ወኀሥሩ ፡ በታሕተ ፡ እደዊሆሙ ።

በእጃቸው ፡ ጭብጥ ፡ በእግራቸው ፡

እርግጥ ፡ ብለው ፡ በመገዛታቸው ፡ ተዋረዱ ፤ ጐሰቈሉ ።

ግእ ፡ ወዘልፈ ፡ ያድኅኖ ሙ ።

እሱ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ያድናቸው ፡ ነበረ ።

እመንቱስ ፡ አምረርዎ ፡ በምክሮ ሙ ።

እሳቸው ፡ ግን ፡ በሥራቸው ፡ አሳዘኑት ።

ወሐመ ፡ በንጢአቶ ሙ ።

ወደው ፡ በሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ባለመክራ ፡ ሆኑ ።

ግፀ ፡ ወርእዮ ሙ ፡ ከመ ፡ ተመንደበ ።

መከራው ፡ እንደ ፡ ጸናባቸው ፡ አየ ፤ አይቶ ፡ አየና ።

ወሰምዖ ሙ ፡ ጸሎቶ ሙ ።

ልመናቸውን ፡ ሰማቸው ።

ግጀ ፡ ወተዘከረ ፡ ኪዳኖ ።

መሐላውን ፡ አደረገ ፡ ፈጸመ ፤

ወነስሐ ፡ በከመ ፡ ብዝኀ ፡ ምሕረቱ ።

እንደ ፡ ቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመለሰ ።

ግፂ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ማህሎ ፡ በቅድመ ፡ ሠለጦሙ ፡ እለ ፡ ሄዉውዎሙ ።

ይንደዳቸው ፡ ይቀጫቸው ፡ ብሎ ፡ በማረካቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ይቅርታውን ፡ አደረገላቸው ።

ግፂ ፡ አድኅነን ፡ እግዚኦ ፡ አምላክነ ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፤ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የነሱን ፡ ይናገራል ፤ አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ከጠላቶቻችን ፡ እጅ ፡ አድነን ።

ወእስተጋብአነ ፡ እምአሕዛብ ።

ከፋርስ ፡ ከባቢሎን ፡ ከአርእ ፡ ከሜዶን ፡ ሰብስበን ፡

ከሠ ፡ ንግነይ ፡ ለስምከ ፡ ቅዱስ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብተን ፡ ጽኑዕ ፡ ከሃሊ ፡ ለሚሆን ፡ ስምህ ፡ እንገዛ ፡ ዘንድ ።

ወነሠመ ፡ ንትመካሕ ፡ በስብሐቲከ ።

ጌትነትህን ፡ በማመስገን ፡ ከብረን ፡ ገነን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ። እምከመ ፡ አድማዕነ ፡ መንግሥተ ፡ ንትሜካህ ፡ እንዲል ።

ግፃ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ እስራኤል ።

እስራኤልን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ ከምጽአትም ፡ በኋላ ፡ የሚኖር ።

ለይበል ፡ ሁሉ ፡ ሕዝብ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን

ራእ ፡ ፲፱ ፡ ፬ ። ፬ ፡ ፭ ።

ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡ ይ

በል ። እስከዚህ፡ ድረስ፡ ባራት፡ ለይ ኩን፡ባምስት፡ለይበሉ፡ተናግሮታል።

መዝሙር ፡ ፻፲፭ ።

፩ ፡ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ፡ ቸር፡ ነውና።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ለሰው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ ለዘላለም ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፪ ፡ ለይበሉ ፡ አለ ፡ አድኅኖሙ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ከመከራ ፡ ያዳናቸው ፡ ሁሉ፡ ግነዩ ።

ለይበሉ ፡ አለ ፡ አድኅኖሙ ፡ እምእደ ፡ ፀሮሙ ።

ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳናቸው ፡ ሁሉ ።

፫ ፡ መአሰተጋብኦሙ ፡ እምበሐውርት ።

ካራቱ ፡ መአዝን ፡ ሰበሰባቸው ፡ ኤር ፡ ሰሜ ፡ ጀ ።

እምጽባሕ ፡ ወእምዐረብ ፡ ወመስዕ ፡ ወባሕር ።

በሓውርት ፡ ያለውን ፡ ይዘረዝራል፤ እምጽባሕ ፡ ከፋርስ ፡ እምዐረብ ፡ ከግብጽ ፡ መስዕ ፡ ከባቢሎን ፡ ባሕር ፡ ከህንድ ፡ የሰበሰባቸው ፡ ትሩፋን፡ ግነዩ፡ ለይበሉ። አለ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፬ ፡ ወሳኩዮሙሰ ፡ ተሰ ፡ ዘይሙ ፡ ዝአልቦሙ ፡ ማይ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተቅበዘበዙ ፡ ባከኑ ።

፭ ፡ ወአረከበ ፡ ፍኖት ፡ ሀገረ ፡ ብሔሮሙ ።

ፍኖተ ፡ ሀገሮሙ ፡ ይላል ፤ ያገራቸውን ፡ መንገድ ፡ አላገኙምና ። (ሐ) ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ የሚወስዱትን ፡ በአገው ፡ አዙረው ፡ እንዲወስዱት ፡ እነሱም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የወሰድናቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እየኰበለሉ ፡ ይሄዱብናል ፡ ብለው ፡ አዙረው ፡ ወስደዋቸዋል ፤ የሀገራችንን ፡ መንገድ ፡ አገኘን ፡ እያሉ ፡ በየጐዳናው ፡ ወድቀው ፡ ወድቀው ፡ ቀርተዋል ።

፮ ፡ ጸምዑ ፡ ወርኀቡ ፡ ውኀልቶት ፡ ነፍሶሙ ፡ በላዕሌሆሙ ።

ተራቡ ፡ ተጸሙ ፡ ተዋሕዳቸው ፡ ያለች ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ አለች ።

፯ ፡ ወወሰዮሙ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳብ ፡ ተመንደቡ ።

እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።

ወአድኅኖሙ ፡ እምንዳቤሆሙ ።

እግዚአብሔርም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ አዳናቸው ።

፰ ፡ ወመርሐሙ ፡ ፍኖት ፡ ርቱዐ ።

የቀናውን ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መንገድ ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።

ነሙ ፡ ይሑሩ ፡ ፍኖተ ፡ ሀገሮሙ ።

በሀገራቸው ፡ መንገድ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ። ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሄዱ ትን ፡ ጐዳና ፡ ሥርጥ ፡ መንገድ ፡ አግኝተው ፡ (ተገልጸላቸው) ፡ በአ ርባ ፡ ቀን ፡ ደርሰዋል ።

፰ ፤ ንግሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ፡ ወመንክሮሂ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ንግሩ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምሕ ረቶ ፡ ወመንክሮ ሂ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። ይህን ፡ እንዲህ ፡ ያደረገ ፡ የእግዚአብ ሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለሰው ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

፱ ፡ እስመ ፡ አጽገበ ፡ ነፍሰ ፡ ርኁብተ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ የተራበች ፡ የትሩ ፍን ፡ ሰውነት ፡ ምግበ ፡ ሥጋን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኝቷልና ።

ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶፫ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፯ ።

ወመልኣ ፡ ለነፍስ ፡ ዕራቃ ፡ በረኀበት ።

የሰውን ፡ ዕራቁትነት ፡ በረከተ ፡ ሥጋን ፡ መልቷታልና ። አንድም ፡ ለዕርቅት ፡ ነፍስ ፡ ይላል ፤ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ከበረከተ ፡ ሥጋ ፡ የተራ ቈተች ፡ የትሩፍን ፡ ሰውነት ፡ በረከተ ፡ ሥጋን ፡ መልቷልና ። አንድም ፡ (እስመ ፡ አጽገበ) ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ረኀበ ፡ ነፍስ ፡ የተራበች ፡ የምእመንን ፡ ነፍስ ፡ በረከተ ፡ ነፍ ስን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ አሰኝቷልና ።

አምስት ፡ ሺሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ከበረከተ ፡ ነፍስ ፡ የተ ራቈተች ፡ የምእመንንም ፡ ሰው ነት ፡ በረከተ ፡ ነፍስን ፡ መልቷ ታልና ። ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፳፭ ።

፲ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ወጽላሎተ ፡ ሞት ።

በባቢሎን ፡ በቈላተ ፡ ጎዞር ፡ ለሚ ኖሩ ፤ አንድም ፡ በጎልዮ ፡ በነ ቢብ ፡ በገቢር ፡ ፍዳ ፡ ለተያዙ ።

ወሙቋሕን ፡ በንዴት ፡ ወበጎጂን ።

በመከራ ፡ በንዴት ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ የታሰሩትን ፤ አንድም ፡ በፍዳ ፡ በቍራኝነት ፡ የተያዙ ትን ፡ ኢሳ ፡ ፵፪ ፡ ፯ ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ አምረሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር

ኢታምልክ ፡ ያለ ፡ አንድም ፡ ኢት ብልው ፡ ያለ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብ ሔር ን ፡ አሳዝነዋልና ፡ ማለት ፤ አንቀበልም ፡ ብለዋልና ።

ወአምዕሰው ፡ ምክረ ፡ ልዑል ።

መክሮ ፡ የሠራቸው ፡ ዘጠኙን ፡ ሕገጋትም ፡ አንቀበልም ፡ ብለ ዋልና ።

፲፪ ፡ ወሠርሐ ፡ በሕማም ፡ ልቦሙ ።

ልበ ፡ ሥጋቸው ፡ በመከራ ፡ ሥጋ ፡ ልበ ፡ ነፍሳቸው ፡ በመከራ ፡ ነፍ ስ ፡ ደከመ ።

ደወዩ ፡ ውኅጦ ፡ ዘኢ ፡ ረድኤ ።

ደወዩ ፡ የሞት ፡ ደዌ ፡ ታመሙ ፤

አጥቦ ፡ ገንዞ ፡ የሚቀብራቸው ፡ አጡ ። አንድም ፡ በጎጢአት ፡ ደዌ ፡ ታመሙ ፤ የሚያጠምቃቸው፡ አጡ ። አውቀረ ፡ ላቲ ፡ ጥምቀተ ፡ መቃብረ ፡ ነፍስ ፤ ውነተማ ፡ በአእባን ፡ ሠላስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ የሚያስጠይፍ ፡ ሆኑ ፤ በድን ፡ ር ኩስ ፡ እንዲል ።

፲፫ ፡ ወዐውየዉ ፡ ጎበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ተመንደቡ ።

እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።

ወአድኀንዎሙ ፡ እምንዳቢሆሙ ።

እሱም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ አዳናቸው ።

፲፬ ፡ ወአውፅአሙ ፡ እምጽልመት ወጽላሎተ ፡ ሞት ።

ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ከባቢሎን ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ ከቄላተ ፡ ጎዞር ፡ አወጣቸው ። አንድም ፡ ምእመናንን ፡ የጎልዮ ፡ የነቢብ ፡ የግቢር ፡ ፍዳ ፡ ካለበት ፡ ከሰአል ፡ ከገሃነም ፡ አወጣቸው ።

ወሠበረ ፡ መዋቅሕቲሆሙ ።

እግር ፡ ብረታቸውን ፡ ሰብሮ ፡ አንድም ፡ ቍራኝነታቸውን ፡ አጥፍቶ።

፲፭ ፡ ንግሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቱ ። ወመንክሮሂ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ ሠበረ ፡ ኖጎተ ፡ ብርት ።

ጎያላኑን ፡ አጥፍቷልና ። እንድም ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡ ነፍስን ፡ ሰራዊተ ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቷልና ። ማር ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።

ወቀጥቀጠ ፡ መናሥግኑ ፡ ዘነጸን ።

ነገሥታቱን ፡ መኳንንቱን ፡ ጎያላኑን ፤ አንድም ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡ ነፍስን ፡ ሊቃነ ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቷልና ። ኢሳ ፡ ፵፩ ፡ ፪

፲፯ ፡ ወተወክፉሙ ፡ እምፍኖት ፡ ጌጋዮሙ በድለው ፡ ከሄዱበት ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ በረድኤት ፡ አንድም ፡ ከመከራ ፡ በንስሓ ፡ ተቀበላቸው ። አንድም ፡ ጎጢአት ፡ ሠርተው ፡ ከሄዱበት ፡ አገር ፡ ከሲኦል ፡ በልጅነት ፡ ከመከራ ፡ በንስሓ ፡ ተቀበላቸው ።

እስመ ፡ ሐሙ ፡ በኀጢአቶሙ ።

ወደው ፡ በሠሩት ፡ ጎጢአት ፡ ባለመከራ ፡ ሁነዋልና ።

፲፰ ፡ ወኵሎ ፡ መብልዐ ፡ አስቆረረት ፡ ነፍሶሙ ።

ሰውነታቸው ፡ መብሉን ፡ ሁሉ ፡ ተጸየፈችው ፡ ማለት ፡ አግኝታው ፡ አይደለም ፤ አጥታው ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡ መሥዋዕቱን ፡

ተጸየፈችው ፤ የሚያስጸይፍ ፡ መ
ሥዋዕት ፡ አለን ፡ ቢሉ ፡ አለማ
ዳኑን ፡ መናገር ፡ ነው ። ወዙልን ፡
ኮነ ፡ ኅሱራን ፡ ወኮነ ፡ ጽድቅነ ፡
ከመ ፡ ጸርቀ ፡ ትክቶ ፤ ፈወስናሃ ፡ ለ
ባቢሎን፡ ወኢተፈወሰት ፡ እንዲል ።
አንድም ፡ ሰውነታቸው ፡ በሞት ፡
አስጸየፈች ፤ በድን ፡ ርኩስ ፡ እን
ዲል ። አንድም ፡ ነፍሳቸው ፡
ምግቡን ፡ ተጸየፈችው ፤ በነፍስ ፡
ምግብ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፤ የክብ
ሩን ፡ መቅረት ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወቀርቡ ፡ ኀበ ፡ አናቅጸ ፡ ሞት ።

ሞት ፡ ገድሎ ፡ ገድሎ ፡ ወደሚ
ያወርድበት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡
ሊወርዱ ፡ ቀረቡ ፤ አናቅጽ ፡ ብሎ ፡
አበዛ ፡ በሀገራቸው ፡ መቃብር ፡
ሲቈፍሩ ፡ ዐፈር ፡ አይመልሱም ፤
እልፍኝ ፡ ካዳራሽ ፡ አድርገው ፡
ያንጸሉ ፤ የኖረውን ፡ እፊት ፡ በእ
ልፍኝ ፡ ትኩሱን ፡ ባዳራሽ ፡
ያደርጉታል ፤ ሽቱ ፡ ለመቅባት ፡
እንዲመቻቸው ፡ ነው ። አንድም ፡
ወደ ፡ ገሃነም ፡ ሊወርዱ ፡ ቀረቡ ።

፲፱ ፡ ወአውየዉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሶበ ፡ ተመንደቡ ።

መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ።

ወአድኃኖሙ ፡ እምኀበ ዘሖሩ ።

እሱም ፡ ከመከራቸው ፡ አዳና
ቸው ። ሉቃ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ።

ሶ ፡ ፈነወ ፡ ቃሎ ፡ ወአሕየዎሙ ።

ረድኤቱን ፡ ሰዶ ፡ አዳናቸው ፤ አን
ድም ፡ ልጁን ፡ በሥጋ ፡ ሰዶ ፡ አዳ
ናቸው ።

ወአድኀንዎሙ ፡ እምኀበ ።

ከሞተ ፡ ሥጋቸው ፡ አንድም ፡
ከሞተ ፡ ነፍሳቸው ፡ አዳናቸው ።

ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፩ ።

፳፩ ፤ ንግሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቶ ።

ወመንክሮሂ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ተአ
ምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፤
አስተምሩ ።

፳፪ ፤ ወይሠውዑ ፡ ሎቱ ፡ መሥዋዕተ ፡
ስብሐት ።

ሠው ፡ ካልሁ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡
ብሏል ፡ እንጂ ፡ የጌትነት ፡ ምስ
ጋና ፡ ያመስግኑት ፡ ሲል ፡ ነው ።

ወይንግሩ ፡ ግብሮ ፡ በትፍሥሕት ።

ሥራውን ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይነ
ግሩ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ።

፳፫ ፤ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡
በ አ ሕ ማ ር ።

በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ወደ ፡
ባሕር ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ።

ወይትገበሩ ፡ ተግባሮሙ ፡ ውስተ ፡ ማይ
ብ ዙ ኅ ።

ስፋሕ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በሰፊ ፡
ውሃ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ሥራቸውን ፡

ይሠራሉ ፤ ሐር ፡ ይጐነጕናሉ ፤ ምንጣፍ ፡ ይታታሉ ፤ ቀለም ፡ ያገባሉ ፤ ነፍጥ ፡ ይጠርጋሉ ፤ ጋሻ ፡ ይሰጕዳሉ ።

፰ ፤ እሙንቱስ ፡ ደኢምሩ ፡ ግብረ እግዚአ ብሔር ።

በየብስ ፡ ካሉ ፡ ይልቅ ፡ በባሕር ፡ ያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያውቃሉ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡ ያኽል ፡ ሁኖ ፡ ሲነሣ ፡ እያዩ ።

፱ መሰንክሮሂ ፡ በውስተ ፡ ልኅት ።

ድንቅ ፡ ሥራውንም ፡ በጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ያውቃሉ ።

፲ ፤ ይቤ ፡ ወመጽአ ፡ መንፈሰ ፡ ዐውሎ ።

ይብል ፡ ይላል ፤ ጌታ ፡ ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ ያዛል ፤ ይመጣል ።

፲፩ ፡ ወተለዐለ ፡ ማዕበል ።

ወይትሌዐል ፡ በል ፤ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ (ወደ ፡ ላይ ፡ ይወጣል) ።

፲፪ ፤ የዐርጉ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ።

ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይዟቸው ፡ ይወጣል ።

፲፫ ወይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ቀላያ ።

ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ያወርዳቸዋል ።

፲፬ ተተመሰወት ፡ ነፍሶሙ ፡ በሕማም ።

ትትመሰው ፡ በል ፡ በመከራው ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ትላለች ፤ ሰውነታቸው ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ትቀልጣለች ።

፲፯ ፤ ደንገፀ ፡ ወተሀውኩ ፡ ከመ ፡ ሰከረ ፡ ወይትሀወኩ ፡ በል ፤ እንደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ ደንግጠው ፡ አእምሯቸው ፡ ይለያቸዋል ።

፲፰ ወተሰዮመ ፡ ኵሉ ፡ ጥበቦሙ ።

ወይሰጠም ፡ ይላል ፤ ጥበባቸው ፡ ሁሉ ፡ ይሰወራቸዋል ፡ ማለት ፤ መልሕቅ ፡ መጣል ፡ ዐላማ ፡ መትከል ፡ ይሳናቸዋል ።

፲፱ ፤ ወዐውየዉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ተመንደቡ ። ወአድኀኖሙ እምንዳቤሆሙ

የዐወይዉ ፡ ወያድኅኖሙ ፡ በል ፤ እንዲህ ፡ መከራ ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር መልሰው ፡ ይለምናሉ ፤ እሱም ፡ ካገኛቸው ፡ መከራ ፡ ያድናቸዋል ።

፳፬ ፤ አጥፍአ ፡ ለዐውሎ ፡ ወአርመመ ፡ ባሕር ።

ያጠፍአ ፡ ወያረምም ፡ ነው ፤ ጥቅሉን ፡ ነፋስ ፡ ያጠፋዋል ፤ ባሕሩ ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

፳፭ ወአርመመ ፡ ማዕበል ።

ወያረምም ፤ ማዕበሉም ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

፰ ፡ ወተፈሥሑ ፡ እስመ ፡ አዕረፉ ።

ወይትፈሥሑ ፤ ከመከራው ፡ ያ
ርፉሉ ፤ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ወመርሐሙ ፡ ውስተ ፡ መርሶ፡ገዘ፡ ፈቀዱ.

ይመርሐሙ ፡ ነው ፤ ሊሄዱበት ፡
ወደሚወዱት ፡ ወደብ ፡ መርቶ ፡
ያወጣቸዋል ።

አንድም ፡ (እለ ፡ ይወርዱ) ፡ በመ
ርከብ ፡ ተሜነው ፡ ወደ ፡ ደሴት ፡
የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ (ይትጌበሩ) ፡
በደሴት ፡ ሁነው ፡ ሥራቸውን ፡
ይሠራሉ ፤ ተክል ፡ ተክለው ፡ ነው።
(እሙንቱሰ) ፡ በየብስ ፡ ካሉ ፡
ይልቅ ፡ በደሴት ፡ ያሉ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያውቃሉ ፤
ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተራራ ፡ ተራራ ፡
ያኽል ፡ ሁኖ ፡ ሲነሣ ፡ እያዩ ።
(ወመንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡ ሥራ
ውንም ፡ በደሴት ። (ይቤ) ፡
ጌታ ፡ መከራ ፡ ይምጣ ፡ አለ ፤
መጣ ። (ወተለዐለ) ፡ መከራው ፡
ጸና ። (የዐርጉ) ፡ ለኤልያስ ፡ ለኢ
ያሱ ፡ የተለመንህ ፡ አምላክ ፡
ተለመነን ፡ ይላሉ ። (ወይወርዱ ፡
ለሙሴ) ፡ የተለመንህ ፡ አምላክ ፡
ተለመነን ፡ ይላሉ ። (ወተመስወ
ት) ፡ ነፍሳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ በመ
ከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ አለች።
(ደንገፀ) ፡ ደነገፀ ፤ እንደ ፡ ሰከ
ረ ፡ ሰው ፡ አእምሯቸው ፡ ተለያ
ቸው ፡ (ወተሰጥመ) ፡ የነቢያት ፡
ትንቢታቸው ፡ የካህናት ፡ ትም
ርታቸው ፡ ጠፋባቸው ። (ወዐ
ውየዉ) ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡
ጊዜ ፡ ወደ እግዚአብሔር ፡ መል
ሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድ፡ነኖሙ) ፡
እሱም ፡ ልመናቸውን ፡ ሰማቸው ።
(አጥፍአ) ፡ ብልጣሶርን ፡ አጠ
ፋው ፤ መከራው ፡ ጸጥ ፡ አለ ።
(ወአርመመ) ፡ የመከራው ፡ ጽናት፡
ጸጥ ፡ አለ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከመ
ከራ ፡ ሥጋ ፡ ዐርፈዋልና ፡ ደስ ፡
አላቸው ። (ወመርሐሙ) ፡ ሊሄዱ
በት ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ኢየ
ሩሳሌም ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።
አንድም ፡ (እለ፡ ይወርዱ) ፡ በ፡ነ
ያላኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡
ከተማ ፡ የሚሄዱ ፡ ትሩፋን ፡
(ይትጌበሩ) ፡ ሥራቸውን ፡ ይሠ
ራሉ ። የቆመውን ፡ ይቈርጣሉ ፡ የ
ተጋደመውን ፡ ይፈልጣሉ ፤ (እሙ
ንቱሰ) ፡ በአፍአ ፡ ካሉ ፡ ከለዕ'ን
ባቆም ፡ ይልቅ ፡ በከተማ ፡ ያሉ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያው
ቃሉ ። (ወመንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡
ሥራውንም ፡ በከተማ ፡ ያውቃሉ ።
(ይቤ) ፡ ጌታ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይምጣ
አለ ፡ መጣ ። (ወተለዐለ) ፡ ጦሩ ፡
ጸና ። (የዐርጉ) ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡
ይሆናሉ ። (ወይወርዱ) ፡ ቋሚ ፡
ለጓሚ ፡ ይሆናሉ ። ገብሮ ፡ ገዶ ፡
አመቶ ፡ ወለቶ ፡ ተበለው ፡ ይሰ
ደባሉ ። (ወተመስወት) ፡ ሰውነ

ታችው ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ትላለች ። (ደንገፁ) ፡ እን ደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ አእምሯቸው ፡ ተለያቸው ። (ወተሰጥመ) ፡ በግራ ፡ እጃቸው ፡ መመከት ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ መወርወር ፡ ይሳናቸ ዋል ። (ወዐውየዉ) ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መልሰው ፡ ይለምናሉ ። (ወአድኀኖሙ) ፡ እሱም ፡ ካገ ኛቸው ፡ መከራ ፡ ያድናቸዋል ። (አጥፍአ) ፡ ናቡከደነጾርን ፡ አጠፋ ው ። (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕ በል ፡ አንድ ፡ ወገን ፤ መከራው ፡ ጸጥ ፡ አለ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከ መከራው ፡ ዐርፈዋልና ፡ ደስ ፡ አ ላቸው ። (ወመርሐሙ) ፡ ይሄዱበ ት ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።

አንድም ፡ (እለ ፡ ይወርዱ) ፡ በጎ ያላኑ ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ እሳት ፡ የሚሄዱ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ። አሌሎን ፡ ለአሕማር ፡ እንዲል ። (ይትጌበሩ) ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ሁነው ፡ እግዚ አብሔርን ፡ ያመሰግናሉ ። (እሙንቱሰ) ፡ ከእ ቶን ፡ እሳት ፡ በአፍአ ፡ ካሉ ፡ ከነዳ ንኤል ፡ ይልቅ ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ያሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ ሥራውን ፡ ያውቃሉ ። ተአምራት ፡ ተደርጎላቸው ፡ (ወመ ንክሮሂ) ፡ ድንቅ ፡ ሥራውንም ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ (ይቤ) ፡ ናቡከደ ነጾር ፡ ምስል ፡ ይቁም ፡ ብሎ ፡ አ ዘዘ፤ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ደረቱ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ጣያት ፡ በሐቅለ ፡ አዶራን ፡ ቆመ ። (ወተ ለዐለ) ፡ እሳቱ ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተመዘ ፡ ወጣ ። (የዐርጉ) ፡ ይባርክዎ ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ (ወይወርዱ) ፡ ይባርክዎ ፡ ቀላያት ፡ ብለው ፡ ያመሰግናሉ ። (ወተመስወት) ፡ ሰው ነታቸው ፡ በመከራው ፡ እለይ ፡ እ ለይ ፡ አለች ፤ ለነሱ ፡ ስለ ፡ መሰ ላቸው ። (ደንገፁ) ፡ ስለ ፡ መሰ ላቸው ፤ (ወተሰጥመ) ፡ የባቢሎ ናውያን ፡ ጥበባቸው ፡ ሁሉ ፡ ተሰ ወራቸው ። ወውስተ ፡ እሳቱሰ ፤ ይወድዩ ፡ ፒሳ ፡ እንዲል ። (ወዐው የዉ) ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ መከራ ፡ በጸናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድኀኖሙ) ፡ እሱም ፡ ካገ ኛቸው ፡ መከራ ፡ አዳናቸው ፤ (አጥ ፍአ) ፡ ዮልማሮዱትን ፡ አጠፋ ው ፤ (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕ በል ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የመከራው ፡ ጽናት ፡ ጠፋ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከመ ከራው ፡ ዐርፈዋልና ፡ ስላረፉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ (ወመርሐሙ) ፡ ይሄዱበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወደ ዱት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መርቶ ፡

አወጣቸው ። አንተም ፡ ሲድራቅ ፡ ወሚሳቅ ፡ ወዐብደናጎ ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ንዑ ፡ ፃኡ ፡ ብሏቸዋል ። አንድም ፡ (እሰ ይወርዱ) ፡ በቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ተገሥጸው ፡ ከመምህራን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ የሚሄዱ ፡ ባሕታውያን ፡ (ይትጌበሩ) ፡ በገዳም ፡ ሁነው ፡ የገዳሙን ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። ተክል ፡ ተክለው ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዘው ፡ ራሳቸውን ፡ ረድተው ፡ ይኖራሉ ። (እመንቱሰ) ፡ ካልመነኑት ፡ ይልቅ ፡ የመነኑት ፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ፡ ያውቃሉ ። ግርማ ፡ አራዊትን ፡ ጸብአ ፡ አጋንንትን ፡ ዕጸበ ፡ ገዳምን ፡ እያዩ ። (ወመንክሮሂ) ፡ በገዳም ፡ ድንቅ ፡ ሥራውን ፡ ያውቃሉ ። (ይቤ) ፡ ጌታ ፡ ሰይጣን ፡ ለፈተና ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ ያዛል ፡ ይመጣል ። (ወይትሌዐል) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ይጸናል ። (የዐርጉ) ፡ ከፍጹምነት ፡ ይደርሳሉ ። (ወይወርዱ) ፡ ወደ ፡ ወጣኒነት ፡ ይመለሳሉ ። (ወትትመሰው) ፡ ሰውነታቸው ፡ በመከራው ፡ እለያ ፡ እለይ ፡ ትላለች ። (ይደነግፀ) ፡ አእምሯቸው ፡ ይለያቸዋል ። (ወይሰጠም) ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ማጣተብ ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ፡ መቀረት ፡ ይጠፋባቸዋል ። (ወዐውየመ) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ በአናባቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልሰው ፡ ለመኑ ። (ወአድኀኖሙ) ፡ እሱም ፡ ከጸብአ ፡ አጋንንት ፡ አዳናቸው ። (አጥፍአ) ፡ ጸብአ ፡ አጋንንትን ፡ አጠፋ ። (ወአርመመ) ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ አንድ ፡ ወገን ። ጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፋ ። (ወተፈሥሑ) ፡ ከጸብአ ፡ አጋንንት ፡ ዐርፈዋልና ፡ ስላረፉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። (ወመርሐመ) ፡ ይሄዱበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መርቶ ፡ አወጣቸው ።

፬፩ ። ንግሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምሕረቱ ። ወመንክሮሂ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነቱን ፡ ተአምራቱን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ንገሩ ፡ አስተምሩ ።

፬፪ ። ወያዐብይዎ ፡ በማኅበረ ፡ አሕዛብ ።

በአሕዛብ ፡ አንድም ፡ በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ያክብሩታል ።

ወይሴብሕዎ ፡ በመንበረ ፡ ሊቃውንት ።

በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ አንድም ፡ በሐዋርያት ፡ በሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ጉባኤ ፡ ያመሰግኑታል ።

፬፫ ። ወረሰዮሙ ፡ ለአፍላግ ፡ በድወ ።

በዔዋዊ ፡ ጊዜ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ወንዞች ፡ የብስ ፡ ያደረጋቸው ፡ አንድም ፡ የልጅነት ፡ መገኛ ፡

የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ልጅነት ፡ እንዳይገኝባት ፡ ያደረገ ፡

ወረሰየ ፡ ምጽማኅ ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ።

የውሃ ፡ መገኛ ፡ የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በሚዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መጸምያ ፡ ያደረገው ፡ ማለት ፡ ውሃ ፡ እንዳይገኝበት ፡ አደረገው ። አንድም ፡ ልጅነት ፡ ይገኝበት ፡ ትምርት ፡ ይነገርበት ፡ የነበረ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ልጅነት ፡ እንዳይገኝበት ፡ ትምርት ፡ እንዳይነገርበት ፡ አደረገ ። ኢሳ ፡ ፲፭ ፡ ፮ ።

፴፬ ፡ ወረሰያ ፡ ለምድር ፡ ዒወ ፡ እንተ ፡ ትፈሪ ። ማእከ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

ኢየሩሳሌምን ፡ ጨው ፡ የምታፈራ ፡ አደረጋት ፤ አንድም ፡ ለምድር ፡ እንተ ፡ ትፈሪ ፡ ረሰያ ፡ ጸወ ፤ እኽል ፡ ተክል ፡ የምታፈራ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ጨው ፡ አደረጋት ፡ ማለት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የማታፈራ ፡ አደረጋት ፤ አንድም ፡ የልጅነት ፡ መገኛ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የማይገኝባት ፡ አደረጋት ።

ኤር ፡ ፲፪ ፡ ፬ ።

በእከዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብርዋ ።

ወርሰዋት ፡ በሚኖሩ ፡ በእስራኤል ፡ ክፋት ፤ አንድም ፡ በአይሁድ ፡ ክፋት ።

፴፭ ፡ ወረሰዮ ፡ ለበድው ፡ ሙሐዘ ፡ ማይ ።

የአሕዛብ ፡ አገር ፡ ባቢሎንን ፡ በዜዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ አደረገው ፤ ይህስ ፡ አይደለም ፤ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ ውሃ ፡ አልነበረበትም ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በዜዋዌ ፡ ጊዜ ፡ የብስ ፡ የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ አደረጋት ። አንድም ፡ የልጅነት ፡ የትምርት ፡ መገኛ ፡ አደረጋት ።

ወለምድረ ፡ በድው ፡ ቀላያተ ፡ ማያት ።

ምድረ ፡ በዳ ፡ ሁኖ ፡ የነበረ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የውሃ ፡ መገኛ ፡ አደረገው ፤ አንድም ፡ ልጅነት ፡ ትምርት ፡ ታጥቶበት ፡ የነበረ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የልጅነት ፡ የትምርት ፡ መገኛ ፡ አደረገው ።

ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፮ ። ፵፩ ፡ ፲፰ ።

፴፮ ፡ አንበረ ፡ ህየ ፡ ርኁባነ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ ተይዘው ፡ የነበሩ ፡ ትሩፋንን ፡ ከዚያ ፡ አኖራቸው ። አንድም ፡ (ርኁባን) ፡ ሐዋርያትን ፡ በመምርነት ፡ ከዚያ ፡ አኖራቸው ።

ሐነፁ ፡ አህጉረ ፡ ኀበ ፡ ይነብሩ ።

ቤት ፡ ሠሩ ፡ አገር ፡ አቀኑ ፤ አንድም ፡ ለዘላለም ፡ የሚኖሩባት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በወንጌል ፡ አዘጋጁ ።

፴፯ ፡ ተከሉ ፡ መይን ፡ መዘርዉ ፡ ገራውህ ።
ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፭ ።

ወያንን ፡ ተከሉ ፤ ዘርንም ፡ በእ

ርሻቸው ፡ ላይ ፡ ዘሩ ። አንድም ፡ ሐዋርያት ፡ አስተማሩ ፡ አሳመኑ ፤ አጠመቁ ።

ወገብሩ ፡ ግዕረረ ፡ አክል ።

መከር ፡ አበጁ ፤ አንድም ፡ ከፍ ጹምነት ፡ አደረሱ ።

ፀሮ ፡ ባረከሙ ፡ ወበዝኑ ፡ ፈድፋደ ።

አከበራቸው ፡ አበዛቸው ፤ ፈጽ መው ፡ በዙ ።

ወኢያውጽኦ ፡ ሎሙ ፡ እንስሳሆሙ ።

ከብቶቻቸውን ፡ አንድም ፡ መም ሮቻቸውን ፡ አላሳነሰባቸውም ። ወእደ ፡ አልቦ ፡ አልሕምት ፡ ምፅ ንጋዕ ፡ ንጹሕ ፡ ወእደ ፡ ብዙኅ ፡ እክል ፡ ይትዐወቅ ፡ እምኀይለ ፡ ላሕሙ ፡ እንዲል ።

ፀፀ ፡ ደወዩ ፡ ወውኀዱ ።

ብሉዩን ፡ ይዞ ፡ ይሄዳል ፤ የሞት ፡ ደዌ ፡ ታመሙ ፡ እንስንስ ፡ አሉ ።

በሕማም ፡ እኩይ ፡ ወበጸዕር ፡ ኢሳ ፡ ፭፬ ፡ ፮

በዜዋዌ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ በሚ ጠት ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ጠፉ ።

ፀ ፡ ውተክዕወ ፡ ጎሣር ፡ ዲበ ፡ መላእክት።

ባለቆቹ ፡ መቅሠፍት ፡ በዝቶ ፡ ታዘዘባቸው ።

ወአስሓቶሙ ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ ዘኢኮነ ፍ ኖ ተ ።

መንገድ ፡ ባይደለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አቅበዘበዛቸው ። አንድም ፡ (ወአሥጎቶሙ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ዘኢኮነ ፡ በድወ) ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ባይደለ ፡ መንገድ ፡ አሳረፋቸው ።

ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

ፀፈ ፡ ወረድአ ፡ ለነዳይ ፡ በተጽናሱ ።

በተጽናሱ ፡ ዘሩባቤልን ፡ በችጋሩ ፡ ጊዜ ፡ አሳረፈው ።

ወረሰዮ ፡ ከመ ፡ አባግዐ ፡ ብሔር ።

እንደ ፡ አገር ፡ በጎች ፡ ያደረገው ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ እንዳገር ፡ መንጋ ፡ አደረገው ። ያ ፡ ሲወጣ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኝ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

ፀፀ ፡ ይርአዩ ፡ ራትዓን ፡ ወይትፈሥሑ ።

ነቢያት ፡ ካህናት ፡ ይህን ፡ አይ ተው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ። አንድም ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ይዩ ።

ወትትፈጸም ፡ አፉሃ ፡ ኵላ ፡ ዐመፃ ።

ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ እንገዛቸ ዋለን ፡ የሚሉ ፡ የባቢሎናውያን ፡ አንደበት ፡ ምላሽ ፡ ታጣለች ።

ፀ፫ ፡ መኑ ፡ ጠቢበ ፡ ዘየዐቅቦ ፡ ለዝ ።

ይህን ፡ የሚያስተውለው ፡ ብልኅ ፡ ዐዋቂ ፡ ማነው ፡ እያለ ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ ያነቃቃል ።

ወየአምር ፡ ከመ ፡ መሐረ ፡ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ቸር ፡ እንደሆነ ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ፡ እያለ ። ሆሴ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፯ ።

፳፱ ፤ ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እግዚኦ ፡ ጥቡዕ ፡ ልብየ ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ፤ አቤቱ ፡ ልቡናዬ ፡ ትጉህ ፡ ነው ።

ጥቡዕ ፡ ልብየ ፡ እሴብሕ ፡ ወእዜምር ።

ልቡናዬ ፡ ትጉህ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ ፈጽሜ ፡ አመሰግናለሁ ።

፴ ፤ ወይትነሣእ ፡ ክብርየ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ክብሬ ፡ ይመለስልኛል ፤ ይመለስልኝ ።

፴፩ ፤ ወእትነሣእ ፡ በመዝሙር ፡ ወበመሰንቆ

በገናዬን ፡ መሰንቆዬን ፡ ይገር ፡ እነሣለሁ ።

ወእትነሣእ ፡ በጽባሕ ።

ፈጥኜ ፡ እነሣለሁ ።

፴፪ ፤ እገኒ ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በአሕዛብ ፡ ጉባኤ ፡ እገዛልሃለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለከ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ።

በሕዝቡም ፡ ጉባኤ ፡ ምስጋና ፡ አቀርብልሃለሁ ።

፴፫ ፤ እስመ ፡ ዐብየት ፡ እስከ ፡ ሰማያት ፡ ምሕረትከ ።

ቸርነትህ ፡ በዝታ ፡ ተደርጋለችና ።

እስከ ፡ ደመናት ፡ ጽድቅከ ።

ይቅርታህም ፡ እስከ ፡ ደመና ፡ ደርሳለችና ።

፴፬ ፤ ተለዐለ ፡ እግዚኦ ፡ መልዕልተ ሰማያት ።

እግዚኦ ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ እስራኤልን ፡ ታድጎ ፡ ልዕልናውን ፡ ገለጸ ።

ወበኵሉ ፡ ምድር ፡ ስብሐቲሁ ።

ጌትነቱም ፡ ባራቱ ፡ መአዝን ፡ ተነገረ ።

፴፭ ፤ ከመ ፡ ይድኑ ፡ ፍቁራኒከ ።

ወዳጆችህ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ።

አድኅን ፡ በየማንከ ፡ ወሰምዐኒ ።

ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ በሥልጣንህ ፡ አድነኝ ።

፴፮ ፤ እግዚኦ ፡ ነበበ ፡ በመቅደሱ ።

እግዚኦ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አድሮ ፡ ተናገረ ።

እትሐሠይ ፡ ወእትካፈል ፡ ሰኬማ ።

ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ምርኮውን ፡ እካፈላለሁ ፤ ምህርካ ፡ ያለውን ፡ ሰቂማ ፡ አለው ።

ወእሳፈር ፡ አዕጻዳተ ፡ ቂላት ።

የአሕዛብን ፡ አውራጃ ፡ እሰፍር ዘንድ ፡ ባታለሁ ።

፳ ፤ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ገለዓድ ፡ ወዚአየ ። ም ና ሴ ።

ነገደ ፡ ገለዓድ ፡ ነገደ ፡ ምናሴ ፡ የኔ ፡ ወገን ፡ ነው ።

ወኤፍሬም ፡ ሰዋቀ ፡ ርእሰየ ።

ምስማከ ፡ ርእሰየ ፡ ያለውን ፡ ሰዋቀ ፡ ርእሰየ ፡ አለው ። ነገደ ፡ ኤፍሬ ም ፡ መጠጊያዬ ፡ ነው ።

ወይሁዳ ፡ ንጉሥየ ።

ነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ንጉሤ ፡ ነበር ።

፳፩ ፤ ወሞዓብ ፡ ካህን ፡ ተስፋየ ።

ካህነ ፡ ሞአብም ፡ አገልጋዬ ፡ ነበር ።

ዲበ ፡ ኤዶምያስ ፡ እሰፍሕ ፡ መከየድየ ።

እግሬን ፡ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ እዘረጋ ፡ ነበር ።

ሊተ ፡ ይእዝዩ ፡ ኢሎፍሊ ።

ኢሎፍላውያን ፡ ለኔ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ።

፳፪ ፤ መኑ ፡ ይወስደኒ ፡ ሀገረ ፡ ጥቅም ።

ወደ ፡ ጥቅመ ፡ ኢያሪኮ ፡ ማን ፡ በወሰደኝ ።

ወመኑ ፡ ይመርሐኒ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ።

እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ መርቶ ፡ ማን ፡ ባወጣኝ ።

፳፫ ፤ አኮኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ዘገደፍከነ

አቤቱ ፡ በመከራ ፡ የጣልከን ፡ አንተ ፡ አይደለህምን ።

ወኢትወፅእ ፡ አምላክነ ፡ ምስለ ፡ ኃይልነ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንደ ፡ ቀ ድሞ ፡ ከጎይላችን ፡ ከሰራዊታ ችን ፡ ጋራ ፡ የማትመጣ ፡ ሆንኽ ።

፳፬ ፤ ሀበነ ፡ ረድኤተ ፡ ለምንዳቤነ ።

ለመከራችን ፡ ረዳት ፡ ስጠን ።

ወከንቱ ፡ ተአምኖ ፡ በሰብእ ።

በሰው ፡ ማመን ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

፳፭ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ንገብር ፡ ኃይለ ።

በእግዚአብሔር ፡ አምነን ፡ ጎይ ልን ፡ እናደርጋለን ፡ እንጂ ።

ወውእቱ ፡ ያንስሮሙ ፡ ለአለ ፡ ይሣቅዩነ

መከራ ፡ የሚያጸኑብንን ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ያጠፋቸዋል ።

መዝሙር ፡ ፻፳ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ ኢትጸመመኒ ፡ ስእለትየ ።

ስለ ፡ መቃብያን ፡ ተናግሮታል ።

፪ ፤ እስመ ፡ አፈ ፡ ሀማኒ ፡ ወአፈ ፡ ኃጥእ ፡ አብቀዉ ፡ ላዕሌየ ።

ተበቅዉ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፤ የኃ

ጥአን ፡ የዐማፅያን ፡ የባቢሎና ውያን ፡ ነገር ፡ በዝቶብኛልና ።

አንድም ፡ ኃጥአን ፡ ዐማፅያን ፡ የሚሆኑ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ነገ ራቸውን ፡ አብዝተውብኛልና ።

መነበቡ ፡ ላዕሌየ ፡ በልሳነ ፡ ዐመፃ ።

በኔ ፡ ዐመፅን ፡ በሚናገር ፡ አንደበት ፡ ይናገራሉ ።

ፎ ፡ ዐገቱኒ ፡ በጽልዕ ።

በጸብ ፡ ከበቡኝ ፤ በፍቅር ፡ መክበብ ፡ አለና ።

መጸብውኒ ፡ በከንቱ ።

በግፍ ፡ ተጸሉኝ ።

፱ ፤ ዘአምአፍቀሩኒ ፡ አስተዋደዩኒ ።

ከወደዱኝ ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ መውደድ ፡ ሁሉ ፡ መውደድን ፡ ይመስል ፤ አንድም ፡ ከመውደድ ፡ ወጥተው ፡ አጣሉኝ ፡ አዋቀሡኝ ፤ አካሰሱኝ ።

መእንሰ ፡ እጼሊ ።

ለመሙ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እጸልይላቸዋለሁ ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ናውና ።

፫ ፤ ፈደዩኒ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት ።

በጎስ ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ የክፋት ፡ ብድራት ፡ ከፈሉኝ ።

መጸልዑኒ ፡ ህየንተ ፡ ዘአፍቀርክዎሙ ።

ስለ ፡ ወደድኋቸው ፡ ፈንታ ፡ ጸሉኝ ፤ አሁን ፡ እኔ ፡ ምን ፡ እላለሁ ።

፮ ፤ ሚ ፡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኃጥአ ።

ባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ አንግሥባቸው ። አንድም ፡ በይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ ባዕድ ፡ ማትያስን ፡ ሹምበት ። በኃጥእ ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ ኃጥእ ፡ አለው ።

መሰይጣን ፡ ይቁም ፡ በየማኑ ።

በአንጥያኮስ ፡ ጽኑ ፡ ባለጋራ ፡ ይቁም ፡ ይነሣበት ። ወአቀመ ፡ አዴርሃ ፡ ሰይጣነ ፡ ላዕለ ፡ ሰሎሞን ፡ እንዲል ። አንድም ፡ በይሁዳ ፡ ሰይጣን ፡ ይደርበት ።

፯ ፤ ወሶበሂ ፡ ይትዋቀሥ ፡ ይፃዕ ፡ ተመዊያ

በተጻላ ፡ በተከራከረ ፡ ጊዜ ፡ ተረትቶ ፡ ተመትቶ ፡ ይመለስ ።

ወጸሎቱሂ ፡ ትኩኖ ፡ ጌጋየ ።

ልመናው ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ ትሁንበት ።

፰ ፤ ወይኩና ፡ መዋዕሊሁ ፡ ኀጸጠ ።

ዘመኑም ፡ ይነስ ፤ ኃጥእ ፡ ዘመኑን ፡ አይፈጽምምና ።

ወሚመቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ።

መንግሥቱንም ፡ ባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ ይውሰድበት ። አንድም ፡ የይሁዳን ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡ ባዕድ ፡ ማትያስ ፡ ይውሰድበት ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩ ፡ ፳ ።

፱ ፤ ወይኩኑ ፡ ደቂቁ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኖቹ ፡ ድኾች ፡ (ድኻ ፡ አደግ) ፡ ይሁኑ ።

ወብእሲቱሂ ፡ ትኩን ፡ መበልተ ።

ያንጥያኮስ ፡ ሚስቱ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኑ ፡ ድኻ ፡ አደግ ፡ ትሁን ።

፲ ፡ ይትሀወኩ ፡ ደቂቁ ፡ ይ ፍ ል ሱ ፡ ወ ያ ስ ተ ፍ ዕ ሙ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኖቹ ፡ ይታወኩ ፤ ከሀገራቸው ፡ ወጥተው ፡ አፍ ፡ ሙሉ ፡ ቍራሽ ፡ ለመቀላወጥ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ አገር ፡ ተሰደው ፡ ይሂዱ ። አንድም ፡ የሚያቀላውጣቸው ፡ አጥተው ፡ ይሙቱ ።

ወይስድድሞ ፡ እምአብያቲሆሙ ።

እንቀላውጣለን ፡ ብለው ፡ ከሄዱበት ፡ ቤታቸው ፡ አስወጥተው ፡ ይስደዷቸው ። አንድም ፡ ከራሳቸው ፡ ቤት ፡ አስወጥተው ፡ ይስደዷቸው ። አንድም ፡ ሥላሴ ፡ አይሁድን ፡ ከሀገራቸው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አስወጥተው ፡ ይስደዷቸው ። አንድም ፡ ከገነት ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አስወጥተው ፡ ይስደዷቸው ። ኤር ፡ ፲፮ ፡ ፰፮

፲፩ ፡ ወይበርብሮ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ኵሎ ፡ ጎ ሯ ሁ ።

ባለጋራ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ይዝረፈው ። አንድም ፡ ይሁዳን ፡ ባለጋራው ፡ ማትያስ ፡ ይዝረፈው ፡ ማለት ፤ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡ ይውሰድበት ፡

ወየሐብልዮ ፡ ኀኪር ፡ ኵሎ ፡ ተግባሮ ።

የአፍአውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ባዕድ ፡ ይውሰድበት ። አንድም ፡ ማትያስ ፡ ክብሩን ፡ ይውሰድበት ።

፲፪ ፡ ወኢይርከብ ፡ ዘይረድኦ ።

በከብት ፡ በጕልበት ፡ የሚረዳው ፡ አይኑር ፤ አያግኝ ።

ወኢይምሐርምሙ ፡ ለዕንለ ፡ ማውታሁ ።

ያንጥያኮስን ፡ ልጆቹን ፡ የይሁዳን ፡ ወገኖቹን ፡ አይዘኑላቸው ፡ አይራሩላቸው ፡ ሥላሴ ፡ ይቅር ፡ አይበሏቸው ።

፲፫ ፡ ወይሠረዉ ፡ ደቂቁ ።

ያንጥያኮስ ፡ ልጆቹ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኖቹ ፡ ይጥፉ ።

በአሐቲ ፡ ትውልድ ፡ ትደምሰስ ፡ ስሙ ።

ያንጥያኮስ ፡ ስሙ ፡ ባንዲት ፡ ትውልድ ፡ ትጥፋ ፤ ምነው ፡ ልጅ ፡ ወልዶ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ልጁ ፡ ልጅ ፡ ስላልወለደ ፤ የይሁዳ ፡ የተመቸ ።

፲፬ ፡ ወትዘከር ፡ ኃጢአተ ፡ አቡሁ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

ያባቱ ፡ ኀጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትታሰብ ።

ወኢደምሰስ ፡ ጌጋየ ፡ ለእሙ ።

የናቱም ፡ ኀጢአት ፡ አይሰረይላት ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ስለምን ፡

ቢሉ ፡ እነሱም ፡ እሱን ፡ መስለ ው ፡ ከሠሩ ፡ ብሎ ።

፲፭ ፡ ወየሀሉ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በ ሎ ሉ ፡ ጊ ዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔ ር ፡ ፊት ፡ ይታሰብ ፤ ይታሰብ ፡ እን ጂ ፡ ኢይደምሰስ ።

ወይጥፋዕ ፡ እምድር ፡ ዝክሩ ።

ስም ፡ አጠራሩ ፡ ከሰው ፡ ተለ ይቶ ፡ አንድም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጥፋ ። ኢዮ ፡ ፲፰ ። ፲፯ ። ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፲፪ ።

፲፮ ፡ እስመ ፡ ኢተዘከረ ፡ ይግበር ፡ ምጽዋተ

አንጥያኮስ ፡ ምጽዋትን ፡ ይመ ጸውት ፡ ዘንድ ፡ አላሰበምና ። አኮ ፡ ዘያጽሕቆ ፡ ምሕረ ፡ ነዳ ያን ፡ አላ ፡ እስመ ፡ ሰራቂ ፡ ው እቱ ፡ የወቅብ ፡ አስከሬን ፡ እን ዲል ።

ሰዶዶ ፡ ብእሲ ፡ ነዳየ ፡ ወምስኪነ ።

ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ የሚሆን ፡ መቃ ቢስን ፡ አስወጥቶ ፡ ሰዷልና ። አንድም ፡ ይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ ነ ዳይ ፡ ምስኪን ፡ የሚሉት ፡ ጌታ ን ፡ በሞት ፡ አስወጥቶ ፡ ሰዷ ልና ።

ጥቡዕ ፡ ልቡ ፡ ለቀቲል ።

ያንጥያኮስ ፡ ልቡናው ፡ ለመግ ደል ፡ ጽኑ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ የይ ሁዳ ፡ ልቡናው ፡ ጽኑ ፡ ነው ።

ኢዮ ፡ ፳፪ ፡ ፯ ። አር ፡ ፵፰ ፡ ፲፬ ።

፲፯ ፡ አብዶራ ፡ ለመርገም ፡ ወትምጽአ ።

መርገምን ፡ የመረጣት ፡ የወደ ዳት ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ትምጻበት ። አንድም ፡ ዘአብደራ ፡ መርገም ፡ ለትምጻ አ ፡ የመረጣት ፡ የወደዳት ፡ መር ገም ፡ ትምጣበት ።

ዘአበያ ፡ ለበረከት ፡ ወትርኃቅ ፡ እምኔሁ ።

በረከትን ፡ አልቀበልም ፡ ያላት ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ትለየው ። አንድም ፡ ዘአበያ ፡ በረከት ፡ ለትርሐቅ ፡ እምኔሁ ፤ አልቀበልም ፡ ያላት ፡ በረከት ፡ ትለየው ።

፲፰ ፡ ወለብሳ ፡ ለመርገም ፡ ከመ ፡ ልብስ ።

ይልበሳ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ መርገ ምን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ይጐናጸፋት ።

ወቦአ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ውስተ ፡ አማዑቱ ።

ይባእ ፡ በል ፤ ውሃ ፡ ከሰውነት ፡ ገብቶ ፡ እንዲስማማ ፡ መር ገም ፡ ከሰውነቱ ፡ ይስማማ ።

ወከመ ፡ ቅብዕ ፡ ውስተ ፡ አዕፅምቲሁ ።

ዘይት ፡ ቅቤ ፡ ከሰውነት ፡ እንዲ ስማማ ፡ መርገም ፡ ይስማማው ።

፲፱ ፡ ለትኩኖ ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ዘይትዐጸፍ።

እንደሚጐናጸፋት ፡ ሸማ ፡ ትሁ ንበት ፡ ማለት ፤ ያ ፡ ከአካል ፡ እንዳይለይ ፡ አትለየው ።

ወከመ ፡ ቅናት ፡ ዘይቀንት ፡ ዘልፈ ።

ዘወትር ፡ አዙረው ፡ አዙረው ፡ እንደሚታጠቁት ፡ ድግ ፡ ትሁንበት ፤ ያን ፡ መልሰው ፡ መልሰው ፡ እንደ ፡ ታጠቁት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አትለየው ።

ጽ ፡ ገ ፡ ግብር ፡ ለእለ ፡ ያስተዋድዩኒ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ዝ፡መርገም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ መርገም ፡ እኔን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በሚያጣሉኝ ፡ በሚያሳጡኝ ፡ በጠላቶቼ ፡ ይሁንባቸው ።

ወለእለ ፡ ይነቡ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ ነፍስየ ።

በሰውነቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ በሚናገሩብኝ ፡ ሁሉ ፡ ይሁንባቸው ።

ጽ፩ ፡ አንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚአየ ፡ ግበር ፡ ሣህለከ ፡ ላዕሌየ ፡ በእንተ ፡ ስምከ ።

ሊተሰ ፡ በል ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ለኔ ፡ ግን ፡ ስምየኒ ፡ መሓሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስላልህ ፡ ቸር ነትህን ፡ አድርግልኝ ።

እስመ ፡ ሠናይ ፡ ምሕረትከ ።

ቸርነትህ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

ጽ፪ ፡ አድኅነኒ ፡ እስመ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ፡ አነ ።

እኔ ፡ ነዳይ ፡ ምስኪን ፡ ነኝና ፡ አድነኝ ።

ልብየኒ ፡ ደንገፀኒ ፡ በውስጥየ ።

ልብየ ፡ በውስጥየ ፡ በሰውነቴ ፡ ያለ ፡ ልቡናዬ ፡ ደነገፀብኝ ፡ ማለት ፤ አእምሮዬ ፡ ተለየች ።

ጽ፫ ፡ ውኅሰቂ ፡ ከመ ፡ ጽላሎት ፡ ዘኀለፈ ።

እንዳለፈ ፡ ጥላ ፡ ሆንሁ ፤ ያ ፡ ታይቶ ፡ እንዲጠፋ ፡ በመከራው ፡ ተፈጸምሁ ።

ወተነፍኩ ፡ ከመ ፡ አንበጣ ።

ውርጭ ፡ እንዳደረበት ፡ አንበጣ ፡ በመከራ ፡ ረገፍሁ ። አንበጣ ፡ ከቦታው ፡ ከወጣ ፡ አይመለስም ፤ በየበረሓው ፡ ረግፎ ፡ ይቀራል ። እኔም ፡ እንደዚያ ፡ ባለ መከራ ፡ ሆንሁ ።

ጽ፬ ፡ ወደክመኒ ፡ ብረክየ ፡ በጸም ።

ብርክ ፡ ሥጋዬ ፡ በቀጠና ፡ ደከመ ።

ወሥሕከ ፡ ሥጋየ ፡ በነጠአ ፡ ቅብዕ ።

ሰውነቴ ፡ ዘይት ፡ ባለመብላት ፡ ቅቤ ፡ ባለመጠጣት ፡ ሻከረ ፡ ማለት ፡ ጐሰቈለ ። ኢሳ ፡ ፭፬ ፡ ፲፮ ።

ጽ፭ ፡ ወአንሰ ፡ ተጽዕልኩ ፡ በኀቢሆሙ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የተሰደብሁኝ ፡ ሆንሁ ።

ሶበ ፡ ይሬእዩኒ ፡ የሐውሱ ፡ ርእሶሙ ።

ባዩኝ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውን ፡ ይነቀንቁብኛል ።

ሸኗ ፡ ርድአኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ።
አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ርዳኝ ።

ወአድኅንኒ ፡ በእንተ ፡ ምሕረትከ ።
ስለ ፡ ቸርነትህም ፡ አድነኝ ።

ሸኟ ፡ ወያእምሩ ፡ ከመ ፡ እጁከ ፡ ይእቲ ፡ ዛቲ ።
ይህቺ ፡ ሥልጣንህ ፡ በኔ ፡ መከራ ፡ እንዳመጣችብኝ ፡ በሳቸውም ፡ መከራ ፡ አምጥታባቸው ፡ በፍዳ ፡ ይወቋት ። አንድም ፡ ያስማረከችኝ ፡ ይህቺ ፡ ሥልጣንህ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እነሱም ፡ ይወቁ ።

እንተሰ ፡ እግዚኦ ፡ ገበርከ ።
አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አትራገሙ ፡ አትሳደቡ ፡ ብለህ ፡ ሥራት ፡ ሠርተህ ፡ ነበር ።

ሸፏ ፡ እመንቱሰ ፡ ይረግሙ ፡ ወአንተ ፡ ባርክ ።
እሳቸው ፡ ይሳደባሉ ፡ ይረግማሉ ፡ (ወአንተ) ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አክብር ፡ አብዛ ።

ይትኃፈሩ ፡ እለ ፡ ይትነሥኡ ፡ ላዕሌየ ።

በጸላትነት ፡ የሚነሡብኝ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፤ ይዋረዱ ። አንድም ፡ ያፍራሉ ፤ ይዋረዳሉ ።
ወገብርከሰ ፡ ይትፈሣሕ ።

ባሪያህ ፡ መቃቢስ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ደስ ፡ ይበለው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።

ሸፐ ፡ ወይልበሱ ፡ ኀፍረተ ፡ ወኀሣረ ፡ እለ ፡ ያስተዋድዩኒ ።

እኔን ፡ የሚያጸሉኝ ፡ ግን ፡ ኀፍረትን ፡ ተዋርዶን ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ይጐናጸፉ ።

ወይትዐጸፍዋ ፡ ከመ ፡ ዐጽፍ ፡ ለኃጢአቶሙ ።
ኀጢአታቸውን ፡ እንደ ፡ ዐጽፍ ፡ ይጐናጸፉት ። አንድም ፡ በፍዳ ፡ ይቅመሷት ።

ሸፑ ፤ እገኒ ፡ በአፉየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈድፋደ ።
ለእግዚአብሔር ግን ፡ ባንደበቴ ፡ ፈጽሜ ፡ አመሰግናለሁ ።

ወእሴብሖ ፡ በማዕከለ ፡ ብዙኅን ።
በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ መኻል ፡ አመሰግነዋለሁ ።

ሸፒ ፡ እስመ ፡ ቆመ ፡ በየማነ ፡ ነዳይ ።
በይሁዳ ፡ መቃቢስ ፡ በስተቀኝ ፡ በረድኤት ፡ ተገለጸ ።

ከመ ፡ ያድኅና ፡ ለነፍሰየ ፡ እምእለ ፡ ሮድዋ
ሰውነቴን ፡ ከከበቧት ፡ ከጽርኣውያን ፡ ያድናት ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ (እስመ ፡ ቆመ) ፡ ጌታ ፡ በፈያታዊ ፡ ዘፀጋም ፡ ቀኝ ፡ በፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ ግራ ፡ ተሰቀለ ። (ከመ ፡ ያድኅና) ፡ ነፍሴን ፡ ከከበቧት ፡ አጋንንት ፡ ያድናት ፡ ዘንድ ።

መዝሙር ፡ ፺፱ ።

፩ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር በየ ማንየ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይባላል ። ጌታዬ ፡ አብ ፡ ጌታዬ ፡ ወልድን ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። አሁን ፡ በሥላሴ ፡ ቀኝ ፡ ግራ ፡ ኑሮባቸው ፡ አይደለም ፤ ዕሪናቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ። ንበር ፡ ማለቱ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ።

እስከ ፡ አገብኦሙ ፡ ለጸላዕትከ ፡ ታሕተ መከየደ ፡ እገሪከ ።

ጠላቶችህን ፡ በግርህ ፡ ርግጥ ፡ በእጅህ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጌ ፡ እስካስገዛልህ ፡ ድረስ ፡ ንበር ፡ አለው ፡ (ሐ) ፡ መከየደ ፡ እግር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሥልጣን ፡ ምእመናን ፡ መላእክት ፤ ጸላእት ፡ አይሁድ ፡ መናፍቃን ፤ አጋንንት ፡ ግዳይ ፡ ይጥሏቸዋልና ። ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፵፬ ፤ ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፮ ። ሉቃ ፡ ፳ ፡ ፵፪ ። ግብ ፡ ፪ ፡ ፴፭ ።

፪ ፤ በትረ ፡ ኃይል ፡ ይፈኑ ፡ ለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምጽዮን ።

እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ኀይል ፡ ያለው ፡ ሥልጣንን ፡ ከጽዮን ፡ ሰማያት ፡ ይልክልኻል ፡ ማለት ፤ ገንዘብ ፡ ያደርግልኻል ። አንድም ፡ በማሕፀን ፡ ማርያም ፡ በተዋሕዶ ፡ አምላክነትን ፡ ይሰጥኻል ፤ ይፈኑ ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ እንግድነት ። አንድም ፡ በትረ ፡ ኀይል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በአምሳለ ፡ ርግብ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ይልክልኻል ፡ ማለት ፤ ለምስክርነት ። አሜሃ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ወወልድ ፡ ዘበአማን ፡ እንዲል ።

ወትኬንን ፡ በማዕከለ ፡ ጸላዕትከ ።

በጸላቶችኽ ፡ በአይሁድ ፡ በመናፍቃን ፡ በአጋንንት ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ። መዝ ፡ ፪ ፡ ፮ ። ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፬ ። ዳን ፡ ፯ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ፳፪ ። ማቴ ። ፩ ፡ ፲፱ ። ፳፭ ። ራእ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።

፫ ፡ ምስሌከ ፡ ቀዳማዊ ፡ በዕለተ ፡ ኃይል ።

ቀዳማዊ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ነበረ ። ይህስ ፡ አይደለም ፤ ሰሚው ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ። አንድም ፡ ወልድ ፡ ቀዳማዊ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፍጥረት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ዓለም ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ኀበ ፡ ቦ ፡ አምጥቶ ፡ ፈጥሮበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ።

በብርሃኖሙ ፡ ለቅዱሳን ።

በቅዳሴሆሙ ፡ ለመላእክት ፡ ሲል፡ ነው ፤ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ባመሰገኑበት ፡ ቀን ። ወዝንቱ ፡ ብርሃን ፡ ኮኖሙ ፡ ጥበበ ፡ ወአእምሮ ፡ እንዲል ።

ወለድኩከ ፡ እምከርሥ ፡ እምቅድመ ፡ ኮከብ ፡ ጽባሕ ።

ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ወለድኩኽ ። አንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ፅንስ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ ተፀንሶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ በትንቢቶሙ ፡ ለነቢያት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ በተፈጸመበት ፡ ቀን ። (ወለድኩከ) ፡ ከዲያብሎስ ፡ መፈጠር ፡ አስቀድሞ ፡ ወለድኩኽ ። እፎ ፡ ወድቀ ፡ ኮከበ ፡ ጽባሕ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ልደት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ በኀቴም ፡ ድንግልና ፡ ተወልዶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ በቅዳሴሆሙ ፡ ለመላእክት ፤ በኀል ፡ ተጥሎ ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቅልሎ ፡ አይተውት ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥምረቱ ፡ ለሰብእ ፡ ብለው ፡ ባመሰገኑበት ፡ ቀን ፡ (ወለድኩከ) ፡ ከዶሮ ፡ ጩኸት ፡ በኋላ ፡ ካጽቢያ ፡ ኮከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከማሕፀን ፡ ማርያም ፡ አንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ስብከት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ተአምራት ፡ አድርጎበታል ፡ ድውይ ፡ ፈውሶበታል ፡ ሙት ፡ አንሥቶበታል ፡ ጋኔን ፡ አውጥቶበታል ፡ ኀብስት ፡ አበርክቶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ ለሐዋርያት ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ። አንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ሰባት ፡ ተአምራት ፡ ተደርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ ብርሃናቸውን ፡ ባጡበት ፡ ቀን ። ወርኢኩ ፡ ረሲዓን ፡ እንዘ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ቅዱስ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ ነፍሳት ፡ ብርሃንን ፡ ባገኙበት ፡ ቀን ። እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ፃኡ ፡ ወእለ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ተከሥቱ ፡ ወርእዩ ፡ ብርሃነ ፡ ዐቢየ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ (ምስሌከ) ፡ በዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፤ ሥስት

መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሥቶበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ ለሐዋርያት ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ሰብል፡ ይላል ፤ እንደ ፡ ተደመፀ ፡ ብራና ፡ ሁነ ዋልና ። (ወለድኩክ) ፡ ካጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዶሮ ፡ ጩኸት ፡ በኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ ወለድኩኽ ።

አንድም ፡ (ምስሌክ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በስብከተ ፡ ሐዋርያት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፤ ተአምራት ፡ ተደርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ ለምእመናን ፡ ዕውቀት ፡ በተሰጠበት ፡ ቀን ።

አንድም ፡ (ምስሌክ) ፡ በዕለተ ፡ ዕርገት ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ነበር ፤ በይባቤ ፡ መላእክት ፡ አርጎበታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ በቅዳሴሆሙ ፡ ለመላእክት ፤ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ ባመሰገኑበት ፡ ቀን ።

አንድም ፡ (ምስሌክ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ወልድ ፡ አብ ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ በህልውና ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፤ ይህን ፡ ዓለም ፡ እምጎበ ፡ ቦ ። ጎበ ፡ አልቦ ፡ ያሳልፍ በታልና ፡ ዕለተ ፡ ኀይል ፡ አለው ። (በብርሃኖሙ) ፡ በዕሴቶሙ ፡ ለጻድቃን ፤ ጻድቃን ፡ ዋጋቸውን ፡ በሚያገኙበት ፡ ቀን ።

፪ ፡ መሐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይኔስሐ እግዚአብሔር ፡ ማለ ፡ ከማለም ፡ መሐላውን ፡ አያፈርስም ፤ በመሐላው ፡ አይጸጸትም ። አንድም ፡ መሐላውን ፡ የማያፈርስ ፡ በመሐላው ፡ የማይጸጸት ፡እግዚአብሔር ፡ ማለ ። ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀን ፡ ጥሎኝ ፡ ጠጅ ፡ አስክሮኝ ፡ ሰው ፡ አገብሮኝ ፡ ልማልን ፡ ብሎ ፡ ይጸጸታል ፤ እሱ ፡ ግን ፡ አያደርገውን ፡ አይናገር ፡ የተናገረውን ፡ አያስቀርምና ።

አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ ።

እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ያለ ፡ ሹመት ፡ ተሹመኽ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ የዓለም ፡ አገልጋይ ፡ አንተ ፡ ነኽ ። መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ጌታን ፡ በምን ፡ ይመስለዋል ፡ ቢሉ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅን ፡ ዘአልቦ ፡ አብ ፡ ወእም ፡ ይለዋል ፤ ምነው ፡ በስንክሳር ፡ ተጽፎ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በሌዋውያን ፡ ክታብ ፡ ስለ ፡ ሌለ ፤ ጌታም ፡ ለቀዳማዊ ፡ ልደቱ ፡ እናት ፡ ለደኃራዊ ፡ ልደቱ ፡ አባት ፡ የለውምና ። አንድም ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡

በስንዴ ፡ በወይን ፡ ያስታዙት ፡ ነበር ፤ ጌታም ፡ ሥጋውን ፡ በስንዴ ፡ ደሙን ፡ በወይን ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቶናልና ። አንድም ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኝ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አለፈ ፡ አይባልም ፤ ጌታም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኝ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያልፋል ፡ አይባልምና ። አልቦ ፡ ጥንት ፡ ለዘመኑ ፡ ወአልቦ ፡ ተፍጻሜት ፡ ለመዋዕሊሁ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ዘእምነገዱ ፡ ለካም ፡ ይለዋል ፡ ከቤተ ፡ ሌዊ ፡ ሳይወለድ ፡ ከካም ፡ ተወልዶ ፡ ክህነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓል ፤ ጌታም ፡ ከቤተ ፡ ሌዊ ፡ ሳይወለድ ፡ ከቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ተወልዶ ፡ ክህነትን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጓልና ።

ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፰ ። መዝ ፡ ፴፩ ፡ ፲፩ ። ዳን ፡ ፯ ፲፬ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፴፬ ። ዕብ ፡ ፭ ፡ ፯ ። ፯ ፡ ፳፩ ።

፭ ፡ እግዚአብሔር ፡ በየማንከ ።

እግዚአብሔር ፡ በዕሪናህ ፡ አለ ።

ይቀጠቅጦሙ ፡ ለነገሥት ፡ በዕለተ ፡ መዓቱ

በዕሪናህ ፡ ሁኖ ፡ መዓቱን ፡ በሚፈጽምበት ፡ (በሚያመጣበት) ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ነገሥታቱን ፡ ቀጥቅጦ ፡ ያጠፋቸዋል ።

፮ ፡ ወይኬንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወያብዝኅ አብድንተ ።

በአሕዛብ ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ አስከሬኑን ፡ ያበዛል ፡ ማለት ፤ አንዱን ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ይከፍለዋል ፡ ማለት ፡ እይደለም ፤ የሚፈርድባቸው ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ። እንድም ፡ የኃጥኣንን ፡ ብዛት ፡ የጻድቃንን ፡ ማነስ ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወይሰብር ፡ አርእስተ ፡ ብዙኃን ፡ በዲበ ምድር ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ቸብቸቦ ፡ ይቈርጣል ፡ ማለት ፤ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ሥልጣን ፡ ያጠፋል ፡ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፫ ።

፯ ፡ እምውኂዝ ፡ ሰትዩ ፡ ማየ ፡ በፍኖት ።

ትሩፋን ፡ በጐዳና ፡ ውሃ ፡ ጠጡ ። አንድም ፡ ምእመናን ፡ ከቀኝ ፡ ጐኑ ፡ በፈሰሰ ፡ ማየ ፡ ገቦ ፡ ተጠመቁ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጅነትን ፡ አገኙ ።

ወበእንተዝ ፡ ይትሌዐል ፡ ርእስ ።

ስለዚህ ፡ ዘሩባቤል ፡ ይነግሣል ፤ ጌታ ፡ ይሰቀላል ። ንሕነ ፡ አባል ፡ ወውእቱ ፡ ርእስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ ለምእመናን ፡ ልጅነትን ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ ርእስ ፡ ጌታ ፡ ይሰቀላል ፤ እስመ ፡ ዓዲሁ ፡ ኢወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡ ዘኢተሰብሐ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲል ፡

መዝሙር ፡ ፻፲ ።

፩ ፤ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ።
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ አቤ
ቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ እገዛ
ልኻለሁ ።

፪ ፤ በምክረ ፡ ራትዓን ፡ በማኅበረ ፡ ዐቢይ
በምክረ ፡ ራትዓን ፡ ግብረ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ በማኅበር ፡ ዐቢይ ፤
የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ በሚ
ሆኑ ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ትም
ርት ፡ ጸንቼ ፡ በብዙ ፡ ጉባኤ ፡ እገ
ዛልኻለሁ ።

፫ ፤ ወትትነሠሥ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ፈቃዱ ።
ቅጽል ፡ አድርገህ ፡ ፈቃዱ ፡ አ
ሚን ፡ በል ።

፬ ፤ አሚን ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ምግባሩ ።
በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ትሻለች ፤ ጌታ ፡
ሰው ፡ ሊያምን ፡ ምግባር ፡ ሊሠ
ራ ፡ ይወዳልና ። አንድም ፡
አሚን ፡ ትትነሠሥ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ ፡ ፈቃዱ ፤ ሃይማኖት ፡ ወዶ ፡
በፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ትሻለች ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ክሂል ፡
እያጣ ፡ ይቀርበታል ፡ እንጂ ፡ ሊ
ያምን ፡ ምግባር ፡ ሊሠራ ፡ ይወ
ዳልና ። (ወዕበየ ፡ ስብሐት ፡ ም
ግባሩ) ፡ ዐቢየ ፡ ስብሐት ፡ መባ
ልም ፡ ለጌታ ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ።

፭ ፤ ወጽድቁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።
ቸርነቱም ፡ ለዘላለም ፡ ሲደረግ ፡
ይኖራል ።

፮ ፤ ተዝካረ ፡ ግብረ ፡ ለስብሐቲሁ ።
ቸርነቱን ፡ ለጌትነቱ ፡ መታሰ
ቢያ ፡ አደረገ ።

መሐረ፡ ወመስተሣህል፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ፤ ይ
ቅር ፡ ባይም ፡ ነው ።

፯ ፤ ወወሀቦሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ለእለ ፡
ይፈርሀም ።
ለሚፈሩት ፡ ለሚያመልኩት ፡ ለት
ሩፋንም ፡ ምግባቸውን ፡ ሰጣ
ቸው ።

ወተዘከረ ፡ ኪዳኖ ፡ ዘለዓለም ።
ተዘከረ ፡ ዘለዓለም ፡ ኪዳኖ ፡ ዘለ
ዓለም ፤ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚ
ኖር ፡ መሐላውን ፡ አሰበ ። አን
ድም ፡ አስቦ ፡

፰ ፤ ወአርአዮሙ፡ለሕዝቡ፡ኃይለ፡ምግባሩ
ለወገኖቹም ፡ በሥልጣኑ ፡ የሚ
ሠራውን ፡ ሥራ ፡ ገለጸላቸው ።

ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ርስተ ፡ ለአሕዛብ ።
ለሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ርስታቸ
ው ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይሰጣቸው ፡
ዘንድ ። አንድም ፡ ርስተ ፡ ዘአሕ

ዛብ ፤ የአሕዛብን ፡ ርስት ፡ ለእ
ስራኤል ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ።

የእጁ ፡ የቃሉ ፡ ሥራ ፡ የሚሆኑ ፡
ጽድቅ ፡ ኢታምልክ ፡ ርትዕ ፡
ዘጠኙ ፡ ሕግጋት ። አንድም ፡ ጽ
ድቅ ፡ ወንጌል ፡ ርትዕ ፡ አሪት ፡
ናቸው ።

መእሙን ፡ ኵሉ ፡ ትእዛዙ ።

ወነበቦ ፡ ወነበቦ ፡ ያለውም ፡ የታመ
ነ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ዳን ፡ ፱-፴፯ ።

፯ ፡ ወጽኑዕ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ወግቡር ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ።

በሚገባ ፡ በውነት ፡ የተሠራ ፡
ነው ።

፱ ፡ መድኃኒተ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለ ሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ለወገኖቹ ፡ ሚ
ጠትን ፡ አደረገላቸው ። አንድም ፡
ጌታን ፡ በሥጋ ፡ ሰደደላቸው ።

ወአዘዘ ፡ ሥርዐቶ ፡ ዘለዓለም ።

ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕ
ጉን ፤ አንድም ፡ አሪትን ፡ ሠራላ
ቸው ።

ቅዱስ ፡ ወማሩም ፡ ስመ ፡ ዚአሁ ።

ስሙ ፡ የሚያስፈራ ፡ የሚያስገ
ርም ፡ ጽኑዕ ፡ ከሃሊ ፡ ነው ።

፲ ፡ ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር

የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ። አንድ
ም ፡ የዘጠኙ ፡ አበጋዝ ፡ ኢታም
ምልክ ፡ ናት ።

ምክር ፡ ሠናይት ፡ ለኵሉ ፡ ዘይገብራ ።

ዘጠኙም ፡ ለሚሠራት ፡ በጎ ፡ ትም
ርት ፡ ናት ።

መስብሐቲሁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ጌትነቱ ፡ ለዘላለም ፡ ሲነገር ፡ ይኖ
ራል ።

ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡
ዓለም ፡ አሜን ።

መዝሙር ፡ ፻፲፩ ።

፩ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሀ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፤

እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሕ
ዝቅያስ ፡ ንኡድ ፡ ክቡር ፡
ነው ።

መዘይፈትድ ፡ ትእዛዞ ፡ ፈድፋደ ።

ትእዛዙንም፡ የሚጠብቅ ፤ አንድም፡ ዘጠኙንም ፡ ፈጽሞ ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፤ አንድም ፡ ሕዝቅያስ፡ንኡድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ኢሳ ፡ ፶፯ ፡ ፪ ።

፪ ፡ መይከውን ፡ ጽኑዐ ፡ ዘርዑ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ሚራ ፡ ፴፯ ፡ ፲፯ ።

ልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ ከብሮ ፡ ገኖ ፡ ይኖራል ፤ (የጸና ፡ ይሆናል) ።

ትውልደ ፡ ጻድቃን ፡ ይትባረኩ ።

የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ እለ ፡ ኢሳይያስ ፡ እለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከብረው ፡ ገነው ፡ ይኖራሉ ።

፫ ፡ ክብር ፡ ወብዕል ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።

ክብረ ፡ ሥጋ ፡ ክብረ ፡ ነፍስ ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ብዕለ ፡ ነፍስ ፡ በቤቱ ፡ አንድም ፡ በወገኖቹ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ወጽድቁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ሞተ ፡ ሰናክሬም ፡ ሚጠተ ፡ ፀሓይ ፡ ሲነገርለት ፡ ይኖራል ።

፬ ፡ ሠረቀ ፡ ብርሃን ፡ ለራትዓን ፡ በውስተ ጽ ል መ ት ።

ለኢሳይያስ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ተደረገላቸው ።

መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነው ፤ ይቅር ፡ ባይም ፡ ነው ።

ወጻድቅ ፡ አምላክነ ።

ወጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ይላል ፤ ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፭ ፡ ብእሲ ፡ መሐሪ፡ወመስተሣህል፡ውእር

ሕዝቅያስም ፡ እንዳቅሙ ፡ ለሰው ፡ የሚያዝን ፡ የሚራራ ፡ ነው ፤ ይቅር ፡ ባይም ፡ ቸርም ፡ ነው ።

ወይዔቅም ፡ ቃሎ ፡ በሙስተ ፡ ፍትሕ ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ ቅኑርጥ ፡ አድርጎ ፡ ይፈርዳል ። እንደ ፡ ሰው ፡ ውዝፍ ፡ አድርጎ ፡ አይተውም ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይዋል ፡ ይደር ፡ ይላል ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ፈርዶ ፡ ያሰናብታልና ። ኢሳ ፡ ፲፭ ፡ ፱ ።

፮ ፡ ወኢይትሀወክ ፡ ለዓለም ።

ለዘላላም ፡ መከራ ፡ መጥቶበት ፡ በመከራ ፡ አይታወክም ።

ዝክረ ፡ ጻድቅ ፡ ለዓለም ፡ ይሄሉ ።

የጻድቅ ፡ የሕዝቅያስ ፡ አንድም ፡ የጻድቅ ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ለዘላለም ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ።

፯ ፡ መኢይፈርህ ፡ እምነገር ፡ እኩይ ።

ከክፉ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ አይፈ

ራም ። አንድም ፡ እምነገረ ፡ እ
ኩይ ፡ ይላል ፤ ከረፋስቂስ ፡ አነ
ጋገር ፡ የተነሣ ፡ አይፈራም ።

ጥቡዕ፡ልቡ ፡ ለተወክሎ ፡ በእግዚአብሔር

በእግዚአብሔር ፡ ለማመን ፡ የሕ
ዝቅያስ ፡ ልቡናው ፡ ትጉህ ፡ ነው ።

፫ ፡ ጽኑዕ ፡ ልቡ ፡ ወኢይትሀወክ ፡ ለዓለም

ልቡናው ፡ ጽኑዕ ፡ ነው ፤ ለዘላ
ለም ፡ መከራ ፡ አግኝቶት ፡ በመ
ከራ ፡ አይታወክም ።

እስከ ፡ ይሬኢ ፡ በጸላዕቲ ።

ጠላቶቹ ፡ ጠፍተው ፡ እስኪያይ ፡
ድረስ ፡ ጽኑዕ ፡ ልቡ ። ዘረወ ፡ ማ
ንሻ ፤ አንድም ፡ ጠላቶቹ ፡ ጠፍ
ተው ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡

፱ ፡ ዘረወ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳያ ።

ገንዘቡን ፡ ለነዳይ ፡ በተነ ፡ ማለት ፡
መጸወተ ፡ ሰጠ ።

ወጽድቂኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይላል ።

ሚጠተ ፡ ፀሓይ ፡ ሞተ ፡ ሰናክ
ሬም ፡ ሲነገርለት ፡ ይኖራል ።

ወይትሌዐል ፡ ቀርኑ ፡ በክብር ።

ሥልጣኑ ፡ ከብሮ ፡ ገኖ ፡ ይኖራል ።

፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፲ ፡ ይሬኢ ፡ ኃጥእ ፡ ወይትመዐዕ ።

ኃጥእ ፡ ሰናክሬም ፡ የኔን ፡ መፈ
ወስ ፡ የሱን ፡ መሞት ፡ ያያል ፤
አይቶ ፡ ይበሳጫል ፤ ተበሳጭቶ ፡
እሱን ፡ የሚጐዳው ፡ ሆኖ ፡ አይ
ደለም ፤ ብስጩ ፡ ለልማዱ ፡ ባል
ጋው ፡ በመከዳው ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡
እንዲሉ ።

ወየሐቂ ፡ ስነኒሁ ፡ ወይትመሰው ።

ጥርሱን ፡ እያፋጨ ፡ እንደ ፡
ሠም ፡ ቀልጦ ፡ ይጠፋል ።

ወተ፡ነልቅ ፡ ፍትወቶሙ ፡ ለኃጥኣን ።

የነሰናክሬም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ እን
ዲህ ፡ እያሉ ፡ ትፈጸማለች ።

መዝሙር ፡ ፻፲፪ ።

፩ ፡ ሰብሕዎ ፡ አግብርቲሁ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ።
የእግዚአብሔር ፡ ባሮች ፡ ትሩፋን ፡
እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት ።

ወሰብሑ ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ።

ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ምስጋና ፡
አቅርቡ ፤ ስሙን ፡ አመስግኑ ።

ማር ፡ ፻፰ ፡ ፹፯ ።

፪ ፡ ወይኩን ፡ ቡሩከ ፡ ስሙ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ይክበር ፡
ይመስገን ።

አምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ፡ ድረስ ። ኢሳ ፡ ፭፬ ፡ ፲፫ ።

፫ ፡ እምሥራቀ ፡ ፀሐይ ፡ እስከነ ፡ ዐረብ ።

ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ ፀሓይ ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ።

ይትአኩት ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአብሔር ።

አላልተህ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፤ አጥብቀህ ፡ ይከብራል ፡ ይመሰገናል ።

፬ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዕልተ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ።

እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡ በላይ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ነው ።

ወሙስተ ፡ ሰማያት ፡ ስብሓቲሁ ።

ጌትነቱም ፡ በሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ሲነገር ፡ ይኖራል ። አንድም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፡ ሲመሰገን ፡ ይኖራል ።

፮ ፡ መኑ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ

እንደ ፡ ፈጣሪያችን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማዳን ፡ መታደግ ፡ የሚቻለው ፡ ማነው ።

፯ ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ወይሬኢ ዘበታሕቱ ።

በአርያም ፡ ሁኖ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አንድም ፡ በበርባኖስ ፡ የሚያረ ገውን ፡ ነገር ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ።

በሰማይኒ ፡ ወበምድርኒ ።

ይነብር ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ በሰማይ ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ ቢለው ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ የሚደረገውን ፡ ዐውቆ ፡ የሚሠራ ፡ አንድም ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ ምሉእ ፡ ነው ። ኢዮ ፡ ፳፮ ፡ ፭ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፰ ።

፯ ፡ ዘያነሥኦ ፡ እምድር ፡ ለነዳይ ።

ድኻውን ፡ ከትቢያነቱ ፡ የሚያነሣው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወያሌዕሎ ፡ እመሬት ፡ ለምስኪን ።

ለምስኪን ፡ እመሬት ፡ ለማለት ፡ ደኀመው ። ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፩ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፵፰

፰ ፡ ከመ ፡ ያንብሮ ፡ ምስለ ፡ መላእክቲሁ ።

ካለቆቹ ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ።

ወምስለ ፡ መላእክተ ፡ ሕዝቡ ።

ከሕዝቡ ፡ አለቆችም ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ። ፩ ፡ ነገ ፡ ፪ ፡ ፰ ።

ዘያነብራ ፡ ለመካን ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ።

መክና ፡ የምትኖር ፡ የእስራኤልን ፡ ሴት ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚያኖራት ፡ እሱ ፡ ነው ። ነቢያት ፡ የሚጠትን ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምታ ፡ ሚጠት ፡ ሲደረግ ፡ ልጅ ፡ ረጅ ፡ የለኝ ፡ ማን ፡ ያወጣኛል ፡ ስትል ፡ ዘሩ ባቤልን ፡ አንግሦ ፡ አውጥቷታልና ።

ወያስተፈሥሓ ፡ ለእሙ ፡ ውሉድ ።
የልጆች ፡ እናት ፡ የምትሆን ፡ የእስራኤልን ፡ ሴት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ እሱ ፡ ነው ። ሚጠትስ ፡ ቢደረግ ፡ በጀርባዬ ፡ ልጅ ፡ በራሴ ፡ ትብትብ ፡ ምንጣፍ ፡ ተሸክሚ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ይሆንል ኛል ፡ ስትል ፡ ዘሩባቤልን ፡ አን ግሦ ፡ አውጥቷታልና ። አንድም ፡ (ዘያነሥአ) ፡ ቋሚ ፡ ለጓሚ ፡ የነበረ ፡ ዘሩባቤልን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚያደርገው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወያሌዕሎ) ፡ ደገመው ። (ከመ ፡ ያንንብሮ) ፡ ካለቆቹ ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ (ወምስለ ፡ መላእክት) ፡ ከሕዝቡ ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ (ዘያነብራ) ፡ ነቢያትን ፡ በሕዝቡ ፡ መኻል ፡ የሚያኖራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ሰባ ፡ ዘመን ፡ ከትንቢት ፡ ተከልክለዋልና ፤ መካን ፡ አላቸው ።

(ወያስተፈሥሓ) ፡ ካህናትንም ፡ በሕዝቡ ፡ መኻል ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ። ልጅ ፡ ከናፍቱ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲገኝ ፡ ትምርትም ፡ የሚነቃ ፡ ከባሕርያቸው ፡ ነውና ። አንድም ፡ (ዘያነሥአ) ፡ አዳምን ፡ ከመሬት ፡ የፈጠረ ፡ እሱ ፡ ነው ። ወነሥአ ፡ መሬተ ፡ እማእከለ ፡ ምድር ፡ ወገብሮ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ ሥጋን ፡ ከመቃብር ፡ ያነሣው ፡ እሱ ፡ ነው ። (ወያሌዕሎ) ፡ ለምስኪን ፡ ለማለት ፡ ደገመው ። (ከመ ፡ ያንብሮ) ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፤ (ወምስለ ፡ መላእክት) ፡ ከመላእክት ፡ አለቆች ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ። (ዘያነብራ) ፡ ወንጌልን ፡ እንድትነገር ፡ የሚያደርግ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ መካን ፡ አላት ፡ በመልከ ጼዴቅ ፡ ጊዜ ፡ ታይታ ፡ ጠፍታለችና ። አንድም ፡ (ዘያነብራ) ፡ ምእመናንን ፡ በገነት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚያኖራቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ መካን ፡ አላቸው ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ልጅነት ፡ አጥተዋልና ። (ወያስተፈሥሓ) ፡ አሪትን ፡ እንድትነገር ፡ አድርጎ ፡ ሕዝቡን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እመ ፡ ውሉድ ፡ አላት ፡ ከሙሴ ፡ ከአሮን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሐና ፡ እስከ ፡ ቀያፋ ፡ ድረስ ፡ ሥራቷን ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ አላጠፋባትምና ። አንድም ፡ ምእመናንን ፡ ከሲኦል ፡ አውጥቶ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ እሱ ፡ ነው ።

ኤዮ ፡ ፴ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፫ ።

፩ ፤ አመ ፡ ይወፅኡ ፡ እስራኤል ፡ እምግብጽ
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የምእመናንንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። አመ ፡ ወፅኡ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አመ ፡ ይትባሀሉ ፡ ለሰይጣን ፡ እንዲል ። ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡

ወቤተ ፡ ያዕቆብ ፡ እምሕዝበ ፡ ዐር ።
ሁለቱም ፡ ነገድ ፡ ፀርነት ፡ ካላቸው ፡ ከግብጻውያን ፡ ተለይተው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡

፪ ፤ ወኮነ ፡ ይሁዳ ፡ መቅደሶ ።
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ማደሪያው ፡ ሆነ ።

ወእስራኤልኒ ፡ ምኵናኖ ።
እስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ ዐሥሩ ፡ ነገድም ፡ ርስቱ ፡ ጕልቱ ፡ ሆኑ ። አንድም ፡ (አመ ፡ ይወፅኡ) ፡ እስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ ከሲኦል ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፤ ወሰመያ ፡ ለሲኦል ፡ ግብጻ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ በወጡበት ፡ ወራት ። (ወቤተ ፡ ያዕቆብ) ፡ ያዕቆብ ፡ ዘነፍስም ፡ ፀርነት ፡ ካላቸው ፡ ከአጋንንት ፡ ተለይተው ፡ በወጡበት ፡ ወራት ፡ (ወኮነ ፡ ይሁዳ ፡ መቅደሶ) ፡ ይሁዳ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ። (ወእስራኤልኒ) ፡ እስራኤል ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፤ ኀበ ፡ ያዕቆብ ፡ ኀድሪ ፡ ወቤተ ፡ እስራኤል ፡ ተዋረሲ ፡ እንዲል ።

፫ ፤ ባሕርኒ ፡ ርእየት ፡ ወጐየት ።
ኤርትራ ፡ በሙሴ ፡ በአሮን ፡ አድሮ ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ አይታ ፡ ሸሸች ።

ወዮርዳኖስኒ ፡ ገብአ ፡ ድኅሬሁ ።
ፈሳሹም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ።

፬ ፤ አድባር ፡ አንፈርወጹ ፡ ከመ ፡ ሐራጊት
ሙሴ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ጊደር ፡ ዘለሉ ።

ወአውግርኒ ፡ ከመ ፡ መሐስሀ ፡ አባግዕ ።
ሰብዓ ፡ ሊቃናትም ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ ዘለሉ ። ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፭ ። ሃሬ ፡ ፲፱ አንድም ፡ (ባሕርኒ) ፡ ዮርዳኖስ ፡ ጌታን ፡ አይታ ፡ ሸሸች ፤ (ወዮርዳኖስኒ) ፡ ፈሳሹም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ። (አድባር) ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ጊደር ፡ ዘለሉ ። (ወአውግርኒ) ፡ ሰብዓ ፡ አርድእትም ፡ እንደ ፡ ጠቦት ፡ ዘለሉ ።

፭ ፤ ምንተ ፡ ኮንከ ፡ ባሕር ፡ ዘጐየይከ ።
ኤርትራ ፡ አንድም ፡ ዮርዳኖስ ፡ እረ ፡ የሸሸሽ ፡ ምን ፡ ሁነሻል ።

ወአንተኒ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ዘገባእከ ፡ ድኅሬከ ።
አንተስ ፡ ፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ኋላህ ፡ የተመለስህ ፡ ምን ፡ ሁነሃል ።

፮ ፡ አድባር ፡ ዘአንፈርዐፅነሙ ፡ ከመ ሐራጊት ።

ተራሮች ፡ አንድም ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ አንድም ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ጌደር ፡ የዘለላችሁ ፡ ምን ፡ ሁናችኋል ።

ወእውግርኒ ፡ ከመ ፡ መሐስዐ ፡ አባግዕ ።

ሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ አንድም ፡ ሰብዓ ፡ አርድእት ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ የዘለላችሁ ፡ ምን ፡ ሁናችኋል ።

፯ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አድለቅለቀት ፡ ምድር ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጸ ፡ ምሕረት ፡ ገጸ ፡ ረድኤት ፡ ከመገለጹ ፡ የተነሣ ፡ ባሕር ፡ ተከፍሎላችሁ ፡ ጠላት፡ ጠፍቶላችሁ፡ ይገባችኋል ፤ ይኸውም ፡ ሲያንሳችሁ ፡ ነው ። አንድም ፡ እላንት ፡ ባትነግሩኝ ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ጠላቶቻችሁ ፡ አይሁድ ፡ መናፍቃን ፡ አጋንንት ፡ ጠፍተውላችሁ ፤ ይገባችኋል ፤ ይኸውም ፡ ሲያንሳችሁ ፡ ነው ።

እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ገጸ ፡ ምሕረቱ ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ።

፰ ፡ ዘይፈሰያ ፡ ለከ ፡ ሶሐ ፡ አንቅዕተ ፡ ማያት

ዘረሰያ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህችን ፡ ዓለም ፡ በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ እብነ ፡ ሙሴን ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡ ኢየሩሳሌምን፡ በሚጠት ፡ ጊዜ ፡ የውሃ ፡ መፍሰሻ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወለእዝኅ ፡ ዐዘቃተ ፡ ማያት ።

እብነ ፡ ሙሴን ፡ የውሃ ፡ መገኛ ፡ ያደረጋት ፡ እሱ ፡ ነው ። እብነ ፡ ብልቲት ፡ ይላታል ።

፱ ፡ አኮ ፡ ለነ ፡ እግዚኦ ፡ አኮ ፡ ለነ ።

አቤቱ ፡ ይህ ፡ ለኛ ፡ የሚገባን ፡ አይደለም ፤ ለኛ ፡ አይደለም ።

ለስመ ፡ ዚአከ ፡ ነሀብ ፡ ስብሐተ ።

ስምህ ፡ እንዲመሰገን ፡ አድርግ ፡ አንድም ፡ ነሀብ ፡ ስብሐተ ፡ ስምህን ፡ እንድናመሰግን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። አናዶ ፡ አቋጭቶ ፡ ሥራ ፡ ለማሠራት ፡ ሎሌ ፡ ተልኮ ፡ ከሃደበት ፡ ሀገር ፡ አክብረው ፡ ያልተቀበሉት ፡ እንደ፡ ሆነ፡ ጌታውን ፡ ያንተን ፡ ስም ፡ ጠርቼ ፡ ብሄድ ፡ አዋርደው ፡ ሰደዱኝ ፡ እኔማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎብኝ ፡ የለምን ፡ ያንተ ፡ ስም ፡ መዋረዱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚቄጨኝ ፡ ይለዋል ፤ አናዶ ፡ ሥራ ፡ ለማሠራት ።

በምሕረትክ ፡ ወበጽድቅክ ።
በይቅርታህ ፡ በቸርነትህም ።

፲ ፤ ከመ ፡ ኢይበሉን ፡ አሕዛብ ፡ አይቱ ፡ ውእቱ ፡ አምላኮሙ ።
ትሩፋን ፡ ፈጣሪ ፡ አለን ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪ ፡ ካላቸው ፡ ለመቼ ፡ ይሆናቸዋል ፡ አያድናቸውምን ፡ እንዳይሉን ፡ አሕዛብ ።

፲፩ ፡ አምላክነሰ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ላዕለ ።
እሳቸው ፡ ባያውቁ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ የኛስ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ከሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በጽርሐ ፡ አርያም ፡ አለ ።

በሰማይኒ ፡ ወበምድርኒ ።
በሰማይም ፡ አለ ፤ በሰማይ ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በምድርም ፡ አለ ። ዙሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ማንሻ ፤ አንድም ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡

ዙሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ፡ ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፩ ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፳፩ - ፲፱ ።

፲፪ ፡ አማልክቲሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዘወርቅ ወዘብሩር ።
የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ግን እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የወደዱትን ፡ እንዳይፈጥሩ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ ናቸው ። አንድም ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።
የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

፲፫ ፡ ገ ፡ ፍኖ ። አፉ ፡ ፲ - ፲፭ ።

፲፫ ፡ አፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይነቡ ።
ሰው ፡ ሠራሽ ፡ የሚሆኑ ፡ እሊህ ፡ አፍ ፡ አላቸው ፤ አይናገሩም ። አንድም ፡ አፍ ፡ ሳላቸው ፡ አይናገሩም ።

ዐይን ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሬእዩ ።
ዐይን ፡ አላቸው ፡ አያዩም ፡ አንድም ፡ ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ አያዩም ።

፲፬ ፤ ዕዝን ፡ ቦሙ ፡ ወኢይሰምዑ ።
ጆሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙም ። አንድም ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ አይሰሙም ።

አንፍ ፡ ቦሙ ፡ ወኢያጸንዉ ።
አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱም ። አንድም ፡ አፍንጫ ፡ ሳላቸው ፡ አያሸቱም ። ኢሳ ፡ ፶፮ ፡ ፯ ። ሕዝ ፡ ፲፮ ፡ ፪ - ፲ ።

፲፭ ፡ እድ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይገሡ ።
እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳስሱም ። አንድም ፡ እጅ ፡ ሳላቸው ፡ አይዳስሱም ።

እግር ፡ ቦሙ ፡ ወኢየሐውሩ ።
እግር ፡ አላቸው ፡ አይሄዱም ። አንድም ፡ እግር ፡ ሳላቸው ፡ አይሄዱም ።

ወኢይነብ ፡ በጕራዔሁ ። ።

ባንደበታቸው ፡ አይናገሩም ።

ወአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ። ።

ባንደበታቸው ፡ ቃል ፡ እስትን ፋስ ፡ የለም ፤ ይህ ፡ ብቻ ፡ ይቀር ባቸዋል ።

፲፯ ፡ ከ ማሆሙ ፡ ለይኩኑ ፡ ኵሎሙ አለ ፡ ገ ብ ር ም ሙ ። ።

እሳቸውማ ፡ ምን ፡ ባይ ፡ የወርቅ ፡ የብር ፡ አይደሉምን ፡ ብሎ ፡ የሠሯቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይሁኑ ፡ ማለት ፤ አፍ ፡ ሳላቸው ፡ የማይናገሩ ፡ ዐይን ፡ ሳላቸው ፡ የማያዩ ፡ ጆሮ ፡ ሳላቸው ፡ የማይሰሙ ፡ አፍንጫ ፡ ሳላቸው ፡ የማያሽቱ ፡ እጅ ፡ ሳላቸው ፡ የማይዳስሱ ፡ እግር ፡ ሳላቸው ፡ የማይሄዱ ፡ ይሁኑ ።

ወኮሎሙ ፡ አለ ፡ ይትዌከሉ ፡ በሙ ። ።

አለ ፡ ይትዌከልዎሙም ፡ ይላል ፤ ስንኳን ፡ የሠሯቸው ፡ ያድኑናል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑባቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደሳቸው ፡ ይሁኑ ፡ ኢሳ ፡ ፪ ፡ ፳ ።

፲፱ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

የእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ጭዎች ፡ ይህ ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመንክሙ ። ።

ረዳኢክሙ ፡ ወምእመንክሙ ፡ ይላል ፤ የታመነ ፡ ረዳታችሁ ፡ የታመነ ፡ ወዳጃችሁ ፡ ነውና ።

፲፪ ፡ ቤተ ፡ አሮን ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

የአሮን ፡ ወገኖች ፡ ካህናት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመኖሙ ። ።

ረዳኢክሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመንክሙ ፤ የታመነ ፡ ረዳታችሁ ፡ የታመነ ፡ ወዳጃችሁ ፡ ነውና ።

፲፫ ፡ እለ ፡ ትፈርሀዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

ነጣጣለትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትፈሩት ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፤ አንድም ፡ መላችሁ ፡ እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ።

ረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ወምእመኖሙ ። ።

ረዳኢክሙ ፡ ወምእመንክሙ ፤ የታመነ ፡ ረዳታችሁ ፡ የታመነ ፡ ወዳጃችሁ ፡ ነውና ።

፲፬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዘከረነ ፡ ወባርከነ ።

እግዚአብሔር ፡ አንሰናልና ፡ አብዛን ፤ ተዋርደናልና ፡ አክብረን ። አንድም ፡ ተዘከረነ ፡ ወባርከነ ፡ ተዋርደን ፡ ነበርና ፡ አክብረን ፡ አንሰን ፡ ነበረና ፡ አብዛን ።

ባርከ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ።

የእስራኤልን ፡ ወገኖች ፡ ጭዎችን ፡ አክብር ፤ አብዛ ።

ወ ባ ር ክ ፡ ቤ ተ ፡ አ ሮ ን ።

የአሮን ፡ ወገኖች ፡ ካህናትን ፡ አክብር ፤ አብዛ ።

፲፩ ፤ ባርኩመ ፡ ለሆሎሙ ፡ ይፈርህም ፡ ለእግዚአብሔር ።

ነሣሣለትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በ ሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የሚፈሩትን ፡ ሁሉ ፡ አክብራቸው ፤ አብዛቸው ።

ለንኡሶሙ ፡ ወለዐቢዮሙ ።

ታላቁንም ፡ ታናሹንም ፡ አክብራቸው ፤ አብዛቸው ። አንድም ፡ ለንኡስክሙ ፡ ወለዐቢይክሙ ፡ ይላል ፤ ከላንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ ታናናሾቻችሁን ፡ ታላላቆቻችሁን፡ ያክብር ፤ ያብዛ ። ንኡስ ፡ ዐቢይ ፡ የዕድሜ ፡ የመዓርግ ፡ ነው ።

፲፬ ፡ ይዌስክ ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌክሙ፡ እግዚአብሔር በላንት ፡ ላይ ፡ ልጆችን ፡ ይጨምር ።

ላዕሌክሙ ፡ ወላዕለ ፡ ውሉድክሙ ።

በላንት ፡ ላይ ፡ ልጆችን ፡ በልጆቻችሁ፡ ላይ፡ የልጅ፡ ልጆችን፡ ይጨምር ።

፲፭ ፡ ቡሩካኑ ፡ አንትሙ ፡ ለእግዚአብሔር ። ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ።

ሰማይን፡ ምድርን፡ የፈጠረ፡ የእግዚአብሔር ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ፍጥረት ፡ ናችሁ ።

፲፮ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ለእግዚአብሔር። ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ የእግዚአብሔር ማደሪያ ፡ ናቸው ።

ምድረሰ ፡ ወሀበ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ምድርን ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ማደሪያ ፡ ሊሆን ፡ ፈጥሮ ፡ ሰጠ ፡ ማለት ፤ አርሶ ፡ ቄፍሮ ፡ ሊመገብ ። አንድም ፡ (ሰማየ ፡ ሰማያት) ፡ ልዕልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገን ዘብ ፡ ነው ። (ምድረሰ) ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ግን ፡ ትሕትና ፡ ነው ፤ ትሕትና ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ዘአኮ ፡ ሙታን ፡ ይሴብሑከ ፡ እግዚአ ።

አቤቱ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አያመሰግኑህምና ።

ወኢሶሎሙ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ።

ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ የወረዱ ፡ ሁሉ ፡ ልብስ ፡ ቀለብ ፡ ስጠን ፡ ብለው ፡ አያመሰግኑህምና ።

፲፰ ፡ ንህነ ፡ ሕያዋን ፡ ንባርኮ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ እኛ ፡ ሕያዋኑ ፡ እናመሰግነዋለን ፡ እንጂ ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ የሚልህ ፡ የለምና ፡ እኛ ፡ ሕያዋኑ ፡ ኑረን ፡ እናመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡ መኖሩን ፡ ስጠን ።

እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ።

ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘላለሙ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፱ ።

፩ ፤ አፍቀርኩ ፡ አስመ ፡ ሰምዐኒ ፡ እግዚ ብሔር ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፤ ስመ ፡ እግዚአ ብ ሔ ር ን ፡ መጥራት ፡ ወድጃለሁና ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰማኝ ። አንድም ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቶኛልና ፡ ስመ ፡ እግዚአብ ሔ ር ን ፡ መጥራት ፡ ወደድሁ ።

፪ ፤ ወአጽምዐ ፡ ዕዝኖ ፡ ኀቢየ ።

እዝነ ፡ ፈቃዱን ፡ ወደኔ ፡ መልሶ ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቷልና ።

ወአዋዕከዎ ፡ በመዋዕልየ ።

ባለ ፡ ዘመኔ ፡ ለምኜዋለሁና ፤ አፍዝዞታል ፡ ይግለጸው ።

፫ ፤ አኀዘኒ ፡ ጸዕረ ፡ ሞት ።

ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አግኝቶኛልና ።

ወረከበኒ ፡ ሕማመ ፡ ሲኦል ።

ለመቃብር ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ አግኝቶኛልና ።

ረከባኒ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፤ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ አግኝተውኛልና ።

፬ ፤ ጸዋዕኩ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፤ የ እ ግ ዚአ ብሔርን ፡ ስም ፡ በምስጋና ፡ ጸራሁ ፤ ገለጸው ።

እግዚኦ ፡ ባልሐ ፡ ለፍኑስየ ።

ወውእቱ ፡ ባልሐ ፡ ይላል ፡ እሱም ፡ ሰውነቴን ፡ ካገኛት ፡ መከራ ፡ አዳናት ። አንድም ፡ አቤቱ ፡ ሰውነቴን ፡ ካገኛት ፡ መከራ ፡ አድናት ።

፭ ፤ መሐሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጻድቅ ፡ ወአምላክነኒ ፡ መስተሣህል ።

መሐሪ ፡ ወጻድቅ ፡ ወመስተሣህል ፡ እ ግ ዚ አ ብሔር ፡ አምላክነ ፤ ፈጣሪያችን ፡ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ፡ ቸር ፡ ነው ፤ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፮ ፤ የዐቅብ ፡ ሕፃናተ ፡ እግዚአብሔር ።

እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ፡ ሕፃናትን ፡ በናታቸው ፡ ማሕፀን ፡ ሳሉ ፡ ይጠብቃል ፤ የበላችው ፡ ተጭኖ ፡ የጠጣችው ፡ አንዝዞ ፡ እንዳይገድላቸው ። አንድም ፡ ሕፃናተ ፡ ሥጋን ፡ ይጠብቃል ፤ ከገደል ፡ እንዳይወድቁ ፡ ከባሕር ፡ እንዳይጠልቁ ። አንድም ፡ ሕፃናተ ፡ ነፍስን ፡ ይጠብቃል ።

ተመንደብኩ ፡ ወአድኀነኒ ።

መከራ ፡ አገኘኝ ፤ ካገኘኝ ፡ መከራ ፡ አዳነኝ ።

፯ ፤ ግብኒ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትኪ ፡ ሰውነቴ ፡ ወደ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ተመለሽ ።

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳኢኪ ።

ረድአኪ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እግዚአ ብሔር ፡ ረድቶሻልና ።

፰ ፡ እስመ ፡ አድኃና ፡ ለነፍስየ ፡ እሞት።

ሰውነቴን ፡ ከሞተ ፡ ሥጋ ፡ አድ ኗታልና ።

ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአንብዕ ።

አዕይንተ ፡ ሥጋዬንም ፡ ከአን ብዐ ፡ ሥጋ ፡ አድኗቸዋልና ።

ወለእገርየኒ ፡ እምዳኅፅ ።

አእጋረ ፡ ሥጋዬንም ፡ ከዳኅፀ ፡ ሥጋ ፡ አድኗቸዋልና ።

፱ ፡ ኪመ ፡ አሥምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ሕያዋን ።

እግዚአብሔርን ፡ የአብርሃም ፡ የይ ስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ሀገር ፡ በም ትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ (ግ ብኢ) ፡ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ተመ ለሽ ። (እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡) ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከሁለት ፡ ባሕ ርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሁኖ ፡ ረድቶሻልና ። አንድም ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳት ፡ ሆኖሻ ልና ። (እስመ ፡ አድኅና) ፡ ነፍ ሴን ፡ ከሞተ ፡ ነፍስ ፡ አድኗታ ልና ። (ወለአዕይንትየኒ ፡ እምአን ብዕ) ፡ አዕይንተ ፡ ነፍሴን ፡ ከአ ንብዐ ፡ ነፍስ ፡ አድኗታልና ፤ አሁን ! በነፍስ ፡ ልቅሶ ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ፤ የመከራውን ፡ ጽናት ፡ መናገር ፡ ነው ። (ወለእገርየኒ) ፡ አእጋረ ፡ ነፍሴንም ፡ ከዳኅፀ ፡ ነፍስ ፡ አድኗቸዋልና ።

(ኪመ ፡ አሥምሮ) ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጻድቃን ፡ በሰማዕታት ፡ በመላእክት ፡ ሀገር ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደስ ፡ አሰኘው ፡ ዘንድ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፱ ።

፩ ፡ አመ፫ኩ ፡ በዘነበብኩ ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፤ ሕዝቅያስ ፡ ነቢያተ ፡ ሐሰት ፡ ወልድ ፡ የተባልህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ በቀኝ ፡ እጅህ ፡ ሳትወረውር ፡ በግራ ፡ እጅህ ፡ ሳትመክት ፡ ጠ ላት ፡ የጠፋልህ ፤ ድንግል ፡ የተ ባለች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ፡ የአ ሕዛብ ፡ አለንጋ ፡ ያልጮኸባት ፡ እንግዳ ፡ ፈረስ ፡ ያልረገጣት ፡ እሆን ፡ ይሆናላ ፡ እሆን ፡ እሆና ለሁ ፡ ብትል ፡ አይደለም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የመጣብህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፤ አዎን ፡ ይህ ፡ መከራ ፡ ያገኘኝ ፡ ይህን ፡ በተና ገርሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዐወቅሁ ፤ በተ ናገርሁት ፡ ነገር ፡ አመንሁ ።

ወአንሰ ፥ ብዙኀ ፥ ሐመምኩ ።

አንሰ ፥ ዋዜ ፥ ነው ፤ እንዲህ ፥ ብዬ ፥ በተናገርሁት ፥ ነገር ፥ ብዙ ፥ መከራ ፥ አገኘኝ ። አንድም ፥ ፈጽሜ ፥ ባለመከራ ፥ ሆንሁ ። ሮሜ ፥ ፫ ፤ ፪ ፥ ቆሮ ፥ ፬ ፥ ፲፫ ።

፪ ፤ አንሰ ፥ ዕቤ ፥ እምግዕዝየ ፥ ኵሉ ፥ ሰብእ ፥ ሐሳዊ ፥ ውእቱ ።

እኔ ፥ ከራሴ ፥ ጀምሮ ፥ ሰው ፥ ሁሉ ፥ ሐሰተኛ ፥ ነው ፥ አልሁ ፤ በዚህም ፥ ሐዊ ፥ አመሰግኖታል ፤ አንሰ ፥ እቤ ፥ በተድላየ ፥ ኢይት ሀወክ ፥ ለዓለም ፥ ባለው ፥ ግን ፥ ነቅፎታል። ዮሐ ፥ ፬ ፥ ፴፫።ሮሜ ፥ ፫ ፥ ፬።

፫ ፤ ምንተኑ ፥ አዐሰየ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ በእንተ ፥ ኵሉ ፥ ዘገብረ ፥ ሊተ ።

ይህን ፥ ስላደረገልኝ ፥ ፈንታ ፥ ለእግዚአብሔር ፥ ምን ፥ ወረታ ፥ እከፍለዋለሁ ።

፬ ፤ ጽዋዐ ፥ ሕይወት ፥ እትሜጠ ።

ድኅነትን ፥ አግኝቻለሁ ፤ (ትች) ፥ አንድም ፥ ድኅነትን ፥ አገኛለሁ ፥ እንጂ ፥ ምንተኑ ፥ አዐስየ ።

ወስመ ፥ እግዚአብሔር ፥ እጼውዕ ።

የእግዚአብሔርንም ፥ ስም ፥ እጠራለሁ ፥ እንጂ ፥ ምንተኑ ፥ አዐስየ ።

፭ ፤ ክቡር ፥ ሞቱ ፥ ለጻድቅ ፥ በቅድመ ፥ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፥ ባወቀው ፥ ነገር ፥ በእግዚአብሔር ፥ በኵርነት ፥ የጸድቅ ፥ ሰው ፥ ሞት ፥ ልዩ ፥ ነው ። ሐተታ ፥ እንዳለፈው ።

፮ ፤ እግዚኦ ፥ አነ ፥ ገብርከ ።

አቤቱ ፥ እኔ ፥ አገልጋይህ ፥ ተገዥህ ፥ ነኝ ።

ገብርከ ፥ ወልደ ፥ አመትከ ።

ያውም ፥ የሴት ፥ ባሪያህ ፥ ልጅ ፥ የምሆን ፥ ባሪያህ ፥ ነኝ ፤ ከወንድ ፥ ባሪያ ፥ ልጅ ፥ የሴት ፥ ባሪያ ፥ ልጅ ፥ ይታመናልና ። የወንድ ፥ ባሪያ ፥ ልጅ ፥ ይጠረጠራል ፤ አሁን ፥ ይህ ፥ ልጅ ፥ የእገሌ ፥ ልጅ ፥ ሁኖ ፥ ነውን ፥ እንዲያው ፥ ነው ፥ እንጂ ፥ ተብሎ ። ሴት ፥ ግን ፥ ባደባባይ ፥ ትወልደዋለች ፥ ታሳድገዋለችና ፥ አይጠረጠርም ። እኔም ፥ በገቢረ ፥ ኀጢአት ፥ በአምልኮ ፥ ጣዖት ፥ የማይጠረጠሩ ፥ የጥንተ ፥ ተገዦችህ ፥ የአብርሃም ፥ የይስሐቅ ፥ የያዕቆብ ፥ ልጅ ፥ ተገዥህ ፥ ነኝ ።

፯ ፥ ወሠበርከ ፥ መዋቅሕየ ።

እስራቴን ፥ አንድም ፥ መከራዬን ፥ አጠፋኽልኝ ።

ለከ ፥ እሠውዕ ፥ መሥዋዕተ ፥ ስብሐት ።

እሠውዕ ፥ ካልሁ ፥ ብሎ ፥ መሥዋዕት ፥ ብሏል ፥ እንጂ ፥ ለጌትነትህ ፥ ምስጋና ፥ አቀርባለሁ ፤ ጌትነትህን ፥ አመሰግናለሁ ።

፰ ፤ ወእሁብ ፡ ብዕዐትየ፡ለእግዚአብሔር በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ።
ይህን ፡ ብታደርግልኝ ፡ ይህን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብዬ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ የተሳልሁትን ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ስለቴን ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጣለሁ ፤

በሰው ፡ ፊት ፡ መሳል ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ መስጠት ፡ ይገባልና ።

፱ ፤ በዐጸደ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በምትሆን ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ።

በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ።
ወበማዕከሌኪ ፡ ኢየሩሳሌም ።

መዝሙር ፡ ፻፲፯ ።

፩ ፤ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር፡ኵልክሙ፡ አሕዛብ ።
ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ የምእመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ። ዐሥሩ ፡ ነገድ ፡ መላችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።
ወያሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ።

ይኸውም ፡ እላንት ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፤ ሁለቱ ፡ ነገድም ፡ ያመሰግኑታል ። ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፲፩ ።

፪ ፤ እስመ ፡ ጸንዐት ፡ ምሕረቱ ፡ ላዕሌነ።
ለነ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሚጠቱ ፡ ለኛ ፡ ጸንታ ፡ ተደርጋልናለችና ።
ወጽድቁሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓለም ።
ወጽድቁኒ ፡ ይላል ፤ ቸርነቱም ፡ ለዘላለም ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራልና ።
ስቄ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ። ማር ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ።

አንድም ፡ ይህን ፡ ሊቁ ፡ በሥርዐተ ፡ ቅዳሴ ፡ ሐዲስ ፡ አድርጎ ፡ ወስዶታል ።

(ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኵልክሙ ፡ አሕዛብ) ፡ ምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

(ወይሴብሕዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ) ። ምእመናን ፡ እስራኤል ፡ ያመሰግኑታልና ።

(እስመ ፡ ጸንዐት ፡ ምሕረቱ ፡ ላዕሌነ) ። ልጅነት ፡ ለኛ ፡ ጸንታ ፡ ተደርጋልናለችና ። (ወጽድቁሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሄሉ ፡ ለዓለም) ። የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራልና ። አንድም ፡ ልጅነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

መዝሙር ፡ ፻፲፯ ።

፩ ፡ ግኑዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ፡ኄር ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ቸር ነውና ፡ ቸር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለእግዚ አ ብ ሔ ር ፡ ተገዙ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ሆነ ።

፪ ፡ ንግሩ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከመ፡ኄር የእስራኤል ፡ ወገን ፡ የምትሆኑ ፡ ጭዎች ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ።

፫ ፡ ንግሩ ፡ ቤተ ፡ አሮን ፡ ከመ ፡ ኄር ።

የአሮን ፡ ወገን ፡ ካህናት ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡

፬ ፡ ንግሩ ፡ ዝክለከሙ ፡ እለ ፡ ትፈርሀዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኄር ።

እ ግ ዚ አ ብ ሔ ርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ የምትፈሩት ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፤ አንድም ፡ መላችሁ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንገሩ ፤ አስተምሩ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለዘላለም ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

፭ ፡ ሶበ ፡ ተመንደብኩ ፡ ጸዋዕኩዎ ፡ ለእ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ።

ትሩፍ ፡ እንዲህ ፡ የምትል ፡ ምን ፡ አድርጎልኻል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እ ግ ዚ አብሔርን ፡ መከራ ፡ ባጋኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ለመንሁት ።

ሰምዐኒ ፡ ወአርኃበ ፡ ሊተ ።

ልመናዬን ፡ ሰምቶ ፡ ተድላ ፡ ደስታዬን ፡ አበዛልኝ ፤ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ አለ ።

፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ፡ አይፈርሀ ፡ ዕጓለ፡እመሕያው፡ምንተ፡ ይገብረኒ

እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ፡ ይረዳኛል ፤ አልፈራም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ። አንድም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብዬ ፡ አልፈራም ። ዘኍ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፩ ።

፯ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ፡ ወአነ ፡ እሬእዮሙ ፡ ለጸላእትየ ።

እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ፡ ይረዳኛል ፤ እኔም ፡ ጠላቶቼን ፡ ንቄ ፡ አጥቅቼ ፡ አያቸዋለሁ ።

፰ ፡ ይኄይስ ፡ ተአምኖ፡በእግዚአብሔር እምተአምኖ ፡ በዕጓለ ፡ እመሕያው ።
በሰራዊቱ ፡ ከማመን ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ።

፱ ፡ ይኄይስ ፡ ተሰፍዎ ፡ በእግዚአብሔር እምተሰፍዎ ፡ በመላእክት ።
በነሰኅል ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ ከማ መን ፡ በ እግ ዚ አብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። አንድም ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ በተሠራ ፡ ጣያት ፡ ከማ መን ፡ በ እግ ዚ አብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። (ይኄይስ) ፡ በአጋን ንት ፡ ከማመን ፡ በ እግ ዚ አብሔር ፡ ማመን ፡ ይበልጣል ። ኢሳ፡፳፡ ፮ ።

፲ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ዐገቱኒ ።
አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከበቡኝ ።

ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሞዕክዎሙ ።
እኔ ፡ ግን ፡ ስመ ፡እግዚዚአብሔርን፡ ጠርቼ ፡ ድል ፡ ነሣኋቸው ።

፲፩ ፡ ዐጊተሰ ፡ ዐገቱኒ ።
መክበብን ፡ ከበቡኝ ።

፲፪ ፡ ዐገቱኒ ፡ ከመ ፡ ንህብ ፡ መዓረ ።
ሲከቡኝም ፡ ንህብ ፡ መዓርን ፡ እንደሚከበው ፡ ከበቡኝ ።

ወነዱ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ አሥዋክ
እሳት ፡ ሥብ ፡ ነው ፤ ሥብ ፡ በእሳት ፡ እንዲቀልጥ ፡ ጠፉ ፤ ዐረብ ፡ እሳት ፡ ሲል ፡ ሥብ ፡ እንዲል ። አን

ድም ፡ ከመ ፡ አሥዋክ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ እሾኽ ፡ በእሳት ፡ ጧ ፡ ጧ ፡ ብሎ ፡ እንዲያልቅ ፡ አለቁ ።

ወበስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሞዕክዎሙ ።
እኔ ፡ ግን ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠርቼ ፡ ድል ፡ ነሣኋቸው ። ኢሳ፡ ፴፫ ። ፲፬ ። ዘፀ ፡ ፳፪ ። ፮ ።

፲፫ ፡ ተንተንኩ ፡ ለወዲቅ ፡ ወእግዚአብ ሔር ፡ አ ን ሥ አ ኒ ።
በመከራው ፡ ልያዝ ፡ ቀረብሁ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከመከራው ፡ አ ዳነኝ ።

፲፬ ፡ ኃይልየኒ፡ወዝክርየኒ፡እግዚአብሔር እግዚአብሔር ፡ ብዋጋ ፡ ኀይሉ ፡ ስም ፡ አጸራሬ ፡ ነው ።

ወውእቱ ፡ ኮነኒ ፡ መድኃኒየ ።
እሱም ፡ ድኅነት ፡ ሆነኝ ። ዘፀ ፡ ፲፭፡ ፪ ። ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፪ ።

፲፭ ፡ ቃለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ውስተ ፡ አብያ ተ፡ጽድቃን ፡ ለጻድቃን ።
በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ጉባኤ ፡ ሚጠት ፡ ይደረጋል ፡ የሚል ፡ የደ ስታ ፡ ቃል ፡ ተሰማ ። አንድም ፡ በጻድቃን ፡ አገር ፡ በገነት ፡ በመ ንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደስ ፡ የሚ ያሰኝ ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ ተሰማ ።

የማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረት ፡ ኀይል ሠልጣነ ፡ እግ ዚ አ ብ ሔ ር ፡ ኀይ ልን ፡ አደረገች ። ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ።

፲፯ ፤ የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ አልዐለተኒ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገችኝ ።

የማን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብረት ፡ ነይለ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይል ን ፡ አደረገች ። ሦስት ፡ መሆኑ ፡ የሦስትነት ፤ ቃሉ ፡ ያለመለወጡ ፡ ያንድነት ፡ ምሳሌ ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፮ ።

፲፯ ፤ ኢይመውት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአሐዩ ።

እድናለሁ ፡ እንጂ ፡ አልሞትም ።

ወእነግር ፡ ግብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

የ እግዚአብሔርንም ፡ ሥራውን ፡ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

፲፰ ፤ ገሥጾሰ ፡ ገሠፀኒ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ መገሠጽን ፡ ገሠጸኝ ።

ወለሞትሰ ፡ ባሕቱ ፡ ኢመጠወኒ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠኝም ። ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፲፯ ። ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፲፰ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፯ - ፱ ።

፲፱ ፡ አርኀዉ ፡ ሊተ ፡ አናቅጸ ፡ ጽድቅ ።

የቤተ ፡ መቅደስን ፡ በር ፡ ክፈቱልኝ ።

እባእ ፡ ውስቴቶን ፡ ወእግነይ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ከዚያ ፡ ገብቼ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እገዛ ፡ አገለግል ፡ ዘንድ ።

ጽ ፤ ዛ ፡ አንቀጽ ፡ እንተ ፡ እግዚአብሔር

ይህች ፡ ኢየሩሳሌም ፤ አንድም ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ በር ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰባ ፡ ዘመን ፡ ለትሩፋን ፡ የሰጣት ፡ ያወጣት ፡ ናት ።

ጻድቃን ፡ ይበውኡ ፡ ውስቴታ ።

ትሩፋን ፡ ይገቡባታል ። አንድም ፡ (አርኀዉ ፡ ሊተ ፡ አናቅጸ ፡ ጽድቅ) ፡ የገነትን ፡ በር ፡ ክፈቱልኝ ። ወአግሐሥ ፡ ለሱራፌ ፡ ዘውስተ ፡ እዴሁ ፡ ሰይፈ ፡ እሳት ፡ እንዲል ። (እባእ) ፡ ከዚያ ፡ ገብቼ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እገዛ ፡ ዘንድ ። (ዛ ፡ አንቀጽ) ፡ ይህች ፡ ገነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጻድቃን ፡ በደሙ ፡ ዐልሎ ፡ ጐልቶ ፡ የሠራት ፡ ናት ። (ጻድቃን) ፡ በቁሙ ፡ ጻድቃን ፡ ይገቡባታል ።

፳፩ ፤ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ሰማዕከኒ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተኸኛል ፡ እገዛልኻለሁ ።

ወኮንከኒ ፡ መድኃኒየ ።

ድኀነትም ፡ ሆነኸኛልና ።

፳፪ ፤ ዕብን ፡ ዘመነንዋ ፡ ነደቅት ።

አናጢች ፡ የናቋት ፡ እብነ ፡ ሙሴ ፡ ወይእዜ ፡ ኮነት ፡ ውስተ ፡ርእሰ ፡ማዕዘንት

አስተጋባኢተ ፡ ሕንጻ ፡ ሆነች ። ዘቦ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አንቅዕት ፡ አዕይንትም ፡ ይላል ፤ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ምንጭ ፡ አላት ፤ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ በየ

ነገዳቸው ፡ ይጠጣሉ ። ይህችም ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ረግረግ ፡ ሁና ፡ ታሰጥምላቸዋለች ፡ ተከትላ ፡ ሄዳለች ፤ ዘሩባቤል ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ መቃን ፡ ቢያደርጋት ፡ አጠረች ፤ ጕበን ፡ ቢያደርጋት ፡ ረዘመች ፤ ወድቃ ፡ ትኖራለች ። ሕንጻው ፡ ተፈጽሞ ፡ አንድ ፡ መአዝን ፡ መግ ጠሚያ ፡ ሲቀር ፡ በፈቃደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ ገጥ ማ ፡ ተገኝታለችና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፲፬።ዳን ፡ ፪ ፡ ፵፬። ማቴ ፡ ፳፭ ፵፪ ። ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ። ፳ ፡ ፲፯ ። ማብ ፡ ፬ ፲፭ ። ሮሜ ፡ ፱ ፡ ፴፫ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፬ ፡ ፯ ፡

፳፫ ፤ እምነበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነት ፡ ዛቲ የመአዝን ፡ መሰብሰቢያ ፡ መሆኗ ፡ መናቂያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ።

ወነካር ፡ ይእቲ ፡ ለአዕይንቲነ ።

ይህችውም ፡ ላይነ ፡ ሥጋችን ፡ ድንቅ ፡ ናት ። አንድም ፡ (እብን) ፡ አሕዛብ ፡ የናቁት ፡ ዘሩባቤል ፡ (ወይእቲ) ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ። (እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡) መናቁም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። (ወነካር) ፡ ይኸውም ፡ ላይነ ፡ ሥጋችን ፡ ድንቅ ፡ ነው ። አንድም ፡ (እብን) ፡ አይሁድ ፡ የናቁት ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ወይእቲ) ፡ በሰረ ፡ ምእመናን ፡ ሆነ ፡ (እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡) ፡ መናቁም ፡ በሰረ ፡ ምእመናን ፡ መሆኑም ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። (ወነካር) ፡ ይኸውም ፡ ላይነ ፡ ነፍሳችን ፡ ድንቅ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፵፪ ። ማር ፡ ፲ ፡ ፪ ።

፳፬ ፤ ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡

ይህች ፡ ዕለተ ፡ ሚጠት ፡ እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፡ ትሩፋንን ፡ አውጥቶ ፡ ሥራውን ፡ የሠራባት ፡ ናት ። አንድም ፡ ይህች ፡ ዕለተ ፡ ዐርብ ፡ እግዚአብሔር ፡ አጋንንትን ፡ አጥፍቶ ፡ ነፍሳትን ፡ አውጥቶ ፡ ሥራውን ፡ የሠራባት ፡ ዕለት ፡ ናት ።

ንትፈሣሕ ፡ ወንትሐሠይ ፡ ባቲ ። ራእ ፡ ፲፱ ፡ ፯ ።

በሷ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ደስ ፡ ይበለን ።

፳፭ ፤ አ ፡ እግዚአ ፡ አድኅንሰ ።

አቤቱ ፡ አድነና ፤ አንድም ፡ አድነን ፡ አቤቱ ፡ አድነነ ።

አ ፡ እግዚአ ፡ ሠርሐሰ ።

አቤቱ ፡ ጐዳናችነን ፡ አቅና ፤ አንድም ፡ ሠርሕ ፡ ፍኖተነ ፤ መንገዳችነን ፡ አቅናልና ።

፳፮ ፤ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠርቶ ፡ የሚመጣ ፡ ዘሩባቤል ፡ ንኡድ ፡

ክቡር ፡ ነው ። አንድም ፡ እግዚ አብሔር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ባወጣለት ፡ ስም ፤ በስ ምዐ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እግዚአ ብሔር ፡ መስክሮለት ፡ የመጣ ፡ ጌታ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

ባረክናክሙ ፡ እምቤተ ፡ እግዚአብሔር

ከቤተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ተወግዕ ተን ፡ አከበርናችሁ ፡ ይላሉ ፡ ነ ቢያት ፡ ካህናት ፤ አንድም ፡ ሐዋር ያት ፡ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፱ ። ማር ፡ ፲፩ ፡ ፱ ።

፳፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ እግዚአ ፡ አስተር አየ ፡ ለነ ።

በምልአት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረድኤት ፡ ተገለጸ ፤ አንድም ፡ በሥጋ ፡ ተገለጸ ።

ግበሩ ፡ በዓለ ፡ በትፍሥሕት ፡ በጎበ ፡ እለ ፡ ያስተሐምምዎ ።

እምጎበ ፡ እለ ፡ ያስተምሙ ፡ ሎቱ ፡ ይላል ፤ ለሱ ፡ ከሚያስተነትኑ ፡ በሱ ፡ ስም ፡ ከሚያስተምሩ ፡ ከነ ቢያት ፡ ከካህናት ፡ አብነት ፡ ነሥታችሁ ፡ የብሉዩን ፡ በዓል ፡ አክብሩ ። አንድም ፡ በሱ ፡ ስም ፡ ከሚያስተምሩ ፡ ከሐዋርያት ፡ አብ ነት ፡ ነሥታችሁ ፡ የሐዲሱን ፡ በዓል ፡ አክብሩ ፤ አንድም ፡ ከሰ ማዕታት ፡ አብነት ፡ ነሥታችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ። አንድም ፡ ምግባር ፡ ሠርታችሁ ፡ ዕረፍተ ፡ ነፍስ ፡ አግኙ ። በዓሎሙ ፡ ለአ እዳግ ፡ ገዳም ፡ እንዲል ።

እስከ ፡ አቅርንቲሁ ፡ ለምሥዋዕ ።

አቅርንተ ፡ ምሥዋዑን ፡ ሥብ ፡ እስከ ፡ መምላት ፡ ደርሳችሁ ። አንድም ፡ አቅርንተ ፡ ምሥዋዑን ፡ እስከ ፡ መያዝ ፡ ደርሳችሁ ። አንድም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እስከ ፡ መምላት ፡ ደርሳችሁ ፡ አንድም ፡ መስቀል ፡ ቀኖት ፡ እስከ ፡ መቀበል ፡ ደርሳችሁ ።

፳፰ ፤ አምላኪየ ፡ አንተ ፡ እገኒ ፡ ለከ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነኽና ፡ እገዛ ልኻለሁ ።

አምላኪየ ፡ አንተ ፡ መአሌዕለከ ።

ፈጣሪዬ ፡ አንተ ፡ ነኽና ፡ ልዑል ፡ እያልሁ ፡ አመሰግንኻለሁ ።

እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ሰማዕከኒ ።

ልመናዬን ፡ ሰምተኽኛልና ፡ እገ ዛልኻለሁ ።

መኮንከኒ ፡ መድኀኒየ ።

ድኅነትም ፡ ሁነኽኛልና ።

፳፱ ፤ ግነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ኄር

ቸር ፡ ነውና ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ተገዙ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ምሕረቱ ።

ቸርነቱ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፤ ስለ ፡ ሆነ ።

መዝሙር ፡ ፻፲፭ ።

ክፍል ፡ ፩ ፤ አሌፍ ፡ ብሂል ፡ አሐዱ ፡ እግዚአ ብሔር ።

አሌፍ ፡ ማለት ፡ ፩ዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው።ይህንም ፡ አሌፋት ፡ አዳም ፡ በገነት ፡ ሳለ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሲጸልየው ፡ ኑሯል ። ኋላ ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በላ ፡ ሳተ ፤ ተሰውሮታል ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተነሡ ፡ አበው ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ ያስጥመን ፡ እያሉ ፡ የሚያምኑ ፡ ሁነዋል ። ጌታ ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ደም ፡ አይማሉ ፡ ብሎ ፡ ለሔኖክ ፡ በጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ ጽፎ ፡ አሳየው ፤ በብርት ፡ ቀርጾ ፡ አኑሮታል ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚምሉ ፡ ሁነዋል ። ነቢያትም ፡ በየመጻፋቸው ፡ እየወሰዱ ፡ ጽፈውታል ። ኤርምያስም ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ተናግሮታል ፤ ዳዊትም ፡ ባሥረኛው ፡ አርእስት ፡ ተናግሮታል ። ይኸውም ፡ ዐሥሩ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ። ዘጠኙን ፡ ትእዛዘከ ፡ ፍኖተከ ፡ ኵነኔከ ፤ ኢታምልክን ፡ ሰምዐከ ፡ እያላቸው ፡ ይሄዳል ። ስምዕከ ፡ አለ ፡ መስክሮ ፡ ሠርቶታልና ። ቃልከ ፡ አለ ፡ ተናግሮ ፡ ሠርቶታልና ። ፍናዊከ ፡ አለ ፡ በመንገድ ፡ እንዲሄዱበት ፡ ሰውም ፡ በሕጉ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ። ኵነኔከ ፡ አለ ፡ ይፈርድበታልና ፤ ትእዛዝከ ፡ አለ ፡ እዝዞ ፡ ሠርቶታልና ። አንድም ፡ ይህንኑ ፡ ቅሉ ፡ የሚያዘዋውረው ፡ አለ ።

፩ ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ንጹሓን ፡ በፍኖቶሙ በሃይማኖት ፡ ከክሕደት ፡ ንጹሓን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወእለ ፡ የሐውሩ ፡ በሕገ ፡ እግዚአብሔር እግዚአ ብሔር ፡ በሠራቸው ፡ በዘጠኙ ፡ ሕገጋት ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። አንድም ፡ በምግባር ፡ ከኀጢአት ፡ ንጹሓን ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ። (ወእለ ፡ የሐውሩ) ፡ በማናቸውም ፡ ሕገ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

፪ ፡ ብፁዓ ን ፡ እለ ፡ የኀሡ ፡ ስምዖ ። አምልኮቱን ፡ የሚሹ ፡ ማለት ፡ በኢታምልክ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ወበኵሉ ፡ ልቦሙ ፡ የኀሥሥዎ ። በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ የሚሹት ፡ ሰዎች ፡ ንኡዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

፫ ፤ እለሰ ፡ ይገብሩ ፡ ዐመፃ ፡ ፍኖቱ ፡ ዚአሁ ፡ አ ሐ ሩ ።

በአወራረድ ፡ ተረጐመው ፤ የሚ ቀድመው ፡ አለ ።

፬ ፤ አንተ ፡ አዘዝከ ፡ ይዕቀቡ ፡ ትእዛዘከ ፡ ፈ ድ ፋ ደ ።

አንተ ፡ ትእዛዝህን ፡ ሕግህን ፡ ፈጽመው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ አዝዘህ ፡ ነበር ። ዐመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በሕግህ ፡ በትእዛዝህ ፡ ጸንተው ፡ አልኖሩም ። አንድም ፡ እሱ ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ ፈጽ መው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብ ቁ ፡ ብሎ ፡ ሥራት ፡ ሠርቶ ፡ ነበር ፤ ዐመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ እለሱ ፡ ግን ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ አልጠበቁም ፤ በሕጉ ፡ በትእዛዙ ፡ ጸንተው ፡ አልኖሩም ።

፭ ፤ ይረትዕሰ ፡ ይርታዕ ፡ ፍኖትየ ።

እንዲህስ ፡ የሚቀና ፡ ከሆነ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገዴ ፡ ይቅ ናልኝ ።

ከመ ፡ እዕቀብ ፡ ሥነ፟ሬከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፮ ፤ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ኢይትኀፈር ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕጉን ፡ በጠ በቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ መጥቶብኝ ፡ መከራውን ፡ አላ ፍርም ።

በርእየ ፡ ኵሉ ፡ ትእዛዝከ ።

ሕግህን ፡ በመስማት ፡ በመጠበቅ ።

፯ ፤ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በልብ ፡ ርቱዕ

አቤቱ ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እገዛል ኻለሁ ።

ዕለ ፡ ተመሀርኩ ፡ ሥነ፟ፊ ፡ ጽድቅከ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደ ሆነ ፡ እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ በተማርሁ ፡ ጊዜ ።

፰ ፡ ወአዐቅብ ፡ ሥነ፟ፊከ ።

ሕግህን ፡ እጠብቃለሁ ።

ወኢትግድፈኒ ፡ ለዝኩሉ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ፈጽመህ ፡ በመ ከራው ፡ አትጣለኝ ።

ክፍል ፡ ፱ ፡ ቤት ፡ ብሂል ፡ ባዕል ፡ እግዚ አ ብ ሔ ር ።

ቤት ፡ ማለት ፡ ባዕል ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ። ቢገኙኝ ፡ አ ፡ አብ ።

፱ ፤ በምንት ፡ ያረትዕ ፡ ወፈላ ፡ ፍኖቱ ።

ወፈላ ፡ ትሩፍ ፡ ግብሩን ፡ ጕዳ ናውን ፡ በምን ፡ ያቀናል ፡ ብትል ፡ በ ዐ ቂ በ ፡ ነ ቢ ብ ከ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ ነዋ ። አን ድም ፡ እንዲህ ፡ ቢሉ ፡ ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ አይደለምን ።

፲ ፡ ወበዙሉ ፡ ልብየ ፡ ጎሠሥኩከ ።

በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ሻሁህ ።

ኢታርኅቀኒ ፡ እምትእዛዝከ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ከሕግህ ፡ አታውጣኝ ፤ አትለየኝ ።

፲፩ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ኀባእኩ ፡ ነቢብከ።

ሃይማኖትህን ፡ በልቡናዬ ፡ ሰወርሁ ።

ከመ ፡ ኢየአብስ ፡ ለከ ።

ኪያከ ፡ አንተን ፡ እንዳልክድ ፡ አንተን ፡ ሕግህን ፡ በልቡናዬ ፡ ሰወርሁ ፤ አንተን ፡ እንዳልበድል ።

፲፪ ፡ ቡሩክ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ ክቡር ፡ ምስጉንም ፡ ነኽ ።

መምህረኒ ፡ ሕንፅከ ።

መህረኒ ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ።

፲፫ ፡ በከናፍርየ ፡ ነገርኩ ፡ ኵሎ ፡ ሕንፅ ፡ አፉከ ።

ባንደበትህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህን ፡ ባንደበቴ ፡ ነገርሁ ፤ አስተማርሁ ።

፲፬ ፡ በፍኖተ ፡ ስምዕከ ፡ ተፈሣሕኩ ።

በአምልኮትህ ፡ ጐዳና ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡ ማለት ፤ አምልኮትህን ፡ በመጠበቅ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

ከመ ፡ ዘበዙሉ ፡ ብዕል ።

ፍጹም ፡ ብዕል ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ። ወርቅ ፡ ብር ፡ አግኝቶ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ ያጣ ፡ እንደ፡ሆነ፡ ያዝናል ፤ ፈረስ ፡ በቅሎም ፡ አግኝቶ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ያጣም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያዝናል ። ሁሉንም ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋልና ።

፲፭ ፡ ወእዛዋዕ ፡ በትእዛዝከ ።

ሕግህን ፡ ተግባር ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ።

ወአኀሥሥ ፡ ፍናዊከ ።

ሕግህን ፡ ለራሴ ፡ እሻለሁ ።

፲፮ ፡ ወአነብብ ፡ ትእዛዛቲከ ።

አዝዘህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህንም ፡ ለሌላው ፡ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

ወኢይረስዕ ፡ ቃለከ ።

ተናግረህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህንም ፡ አልዘነጋም ።

ከፍል ፡ ፲ ፤ ጋማል ፡ ብሂል ፡ ግሩም ፡ እግዚአብሔር ።

ጋሜል ፡ ማለት ፡ ግሩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፯ ፡ ዕስዮ ፡ ለገብርከ ።

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ሚጠትን ፡ ሕሜተ ፡ ንስሓን ፡ ስጠው ።

ከመ ፡ እሕያው ፡ ወእዕቀብ ፡ ነቢብከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ከመከራ ፡

ው ፥ ዐርፍ ፥ ዘንድ ፥ ሕግህንም ፥ በመጠበቅ ፥ ጸንቼ ፥ እኖር ፥ ዘንድ ።

፻፳ ፥ ክሥቶን ፥ ለአዕይንትየ ፥ ወእርአይ ዐይኖቼን ፥ አብራቸው ። አንድም ፥ ዐይነ ፥ ልቡናዬን ፥ ግለጽልኝ ፥ ምስጢር ፥ አይ ፥ ዘንድ ፤ እንዳይ ፥ ልሁን ።

መድምምከ ፥ እምሕግከ ።

ሕግህን ፥ ካለመጠበቄ ፥ የተነሣ ፥ መድምም ፥ ፂዋዌህ ፥ ተደረገ ብኝ ። አንድም ፥ ሕግህን ፥ ከመ ጠበቄ ፥ የተነሣ ፥ ግሩም ፥ ድንቅ ፥ የሚሆን ፥ ሚጠትህ ፥ ይደረግል ኛል ።

፻፳፩ ፥ ፈላሲ ፥ አነ ፥ ውስተ ፥ ምድር ።

እኔ ፥ በባቢሎን ፥ ስደተኛ ፥ መጻተኛ ፥ ነኝ ።

አትግኅእ ፥ እምኔየ ፥ ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፥ ከኔ ፥ አትሰውረው ፤ ስደተኛ ፥ ለማን ፥ ይነገራል ፥ ብለው ፥ ምስጢር ፥ ይሰውሩታል ።

፻፳፪ ፥ አፍቀረት ፥ ነፍስየ ፥ መፈተውት ።

ሰውነቴ ፥ ፈጽማ ፥ ወዳለችና ።

ዅነኔከ ፥ በዅሉ ፥ ጊዜ ።

ሁል ፥ ጊዜ ፥ ሕግህን ።

፻፳፫ ፥ ገሠጽኮሙ ፥ ለዕቡያን ።

ትዕቢተኞች ፥ ባቢሎናውያንን ፥ ሠራኻቸው ፤ ቀጻኻቸው ። አንድም ፥ ገሠጽኮሙ ፥ ለዕቡያን ።

ርጉማን ፥ እለ ፥ ይትገኅሡ ፥ እምትእዛዝከ

ትዕቢተኞች ፥ ርጉማን ፥ የሚሆኑ ፥ ከሕግህ ፥ የወጡ ፥ ባቢሎናውያንን ፤ አንድም ፥ ኤኮንያን ፥ ሴዴቅያስን ፥ ሠራኻቸው ፤ ቀጻኻቸው ።

፻፳፬ ፥ አዕትት ፥ እምኔየ ፥ ጽዕለተ ፥ ውኅጎረ

ስድቤን ፥ ተዋርዶውን ፥ ከኔ ፥ አርቅልኝ ፥ ገብሮ ፥ ገዶ ፥ አመፉ ፥ ወለቶ ፥ እያሉ ፥ ይሰድቧቸዋልና ።

እስመ ፥ ትእዛዘከ ፥ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፥ ሽቻለሁና ።

፻፳፭ ፥ እስመ ፥ ነበሩ ፥ መላእክት ፥ ወኪ ያ ያ ፥ ሐ መ ዩ ።

የባቢሎናውያን ፥ አለቆች ፥ ባደ ባባይ ፥ ተቀምጠው ፥ ሲባባ ፥ ገደል ፥ ገባ ፥ እያሉ ፥ በኔ ፥ ይዘ ፍናሉ ፤ እኔን ፥ ያማሉ ።

መገብርከሰ ፥ ይዛዋዕ ፥ በዅነኔከ ።

እኔ ፥ ባሪያህ ፥ ግን ፥ ሰው ፥ ምን ፥ ቁም ፥ ነገር ፥ ነው ፥ ብዬ ፥ ሕግ ህን ፥ ተግባር ፥ አድርጌ ፥ እኖራ ለሁ ።

፻፳፮ ፤ እስመ ፥ ስምዕከ ፥ ተምህርየ ፥ ውእቱ

ሕግህ ፥ መማሬ ፥ ትምርቴ ፥ ነውና ።

መምክርየኒ ፥ ዅነኔ ፥ ዚአከ ።

ዘጠኙም ፥ ሕገጋት ፥ ትምርቴ ፥ ናቸው ።

ክፍል ፡ ፱ ፤ ዳሌጥ ፡ ብሂል ፡ ድልው ፡ እግዚአብሔር ።

ዳሌጥ ፡ ማለት ፡ ድልው ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ። ቢገናኝ ፡ ጋዳ ።

፹፩ ፤ ጠግዐት ፡ ነፍስየ ፡ በምድር ።

ሰውነቴ ፡ በባቢሎን ፡ ተዋረደች ፤ ድንኒ ፡ ወንትዓዶ ፡ ብኪ ፡ እያሉ ፡ ፈረፈር ፡ ይሻገሩባቸዋል ። ኮር ፡ ይወጡባቸዋልና ። አንድም ፡ በቀጠና ፡ በስልት ፡ ከምድር ፡ ተጣበቀች ፤ ቀጠና ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ አይሆንለትምና ።

ወአሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ በተናገርከው ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ በመጠበቄ ፡ አድነኝ ።

፹፪ ፤ ነገርኩ ፡ ፍናዊከ ፡ ወሰምዓከኒ ።

ዘጠኙን ፡ ኢታምልክንም ፡ ነገርሁ ፤ አስተማርሁ ።

ወምህረኒ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ።

፹፫ ፤ ፍኖተ ፡ ጽድቅከ ፡ አለብወኒ ።

እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ።

ወእዛዋዕ ፡ በመንክርከ ።

ድንቅ ፡ የሚሆን ፡ ሥራህን ፡ ተግባር ፡ አድርጌ ፡ እኖራለሁ ።

፹፬ ፤ ደቀሰት ፡ ነፍስየ ፡ እምኀዘን ።

ሰውነቴ ፡ ከማዘኗ ፡ የተነሣ ፡ አንቀላፋች ፤ ሐዘን ፡ እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ ይላልና ። አንድም ፡ ሰውነቴ ፡ ከብዙ ፡ መከራ ፡ የተነሣ ፡ የሞት ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፋች ።

አጽንዓኒ ፡ በነቢብከ ።

በሕግህ ፡ አንድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ጎሊቆን ፡ ባልከው ፡ አጽናኝ ።

፹፭ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ አርኀቅ ፡ እምኔየ ።

የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ከኔ ፡ አርቅ ። አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፡ ይላል ፤ የባቢሎናውያንን ፤ አንድም ፡ የኤኮንያንን ፡ የሴዴቅያስን ፡ ግብር ፡ ከኔ ፡ አርቅ ።

ወበሕግከ ፡ ተማሃለኒ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቄ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፹፮ ፤ ፍኖተ ፡ ጽድቅከ ፡ አብደርኩ ።

እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ ወድጃለሁና ።

ወኮነኔከሰ ፡ ኢረሳዕኩ ።

ሕግህንም ፡ አልዘነጋሁም ።

፹፯ ፤ ተለውኩ ፡ ስምዓከ ፡ እግዚኦ ፡ ኢታስተንፍረኒ ።

አቤቱ ፡ አምልኮትህን ፡ ጠበቅሁ ፡

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ አንተም ፡ በመከራው ፡ አታሳፍረኝ ። አን ድም ፡ በመከራው ፡ እንዳታሳ ፍረኝ ፡ ባንተ ፡ አመንሁ ። አን ድም ፡ አቤቱ ፡ ባንተ ፡ አምኖለሁና፡ በመከራው ፡ አታሳፍረኝ ።

ፀፀ ፡ ፍኖተ ፡ ትእዛዝከ ፡ ሮጽኩ ።

አዝዘህ ፡ በሠራኻቸው ፡ በዘጠ ኙ ፡ ሕገጋትም ፡ ጸናሁ ። አን ም ፡ ጸንቼ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወረድሁ ።

ዖበ ፡ አርኃብኮ ፡ ለልብየ ።

ልቡናዬን ፡ በዕውቀት ፡ ባሰፋኸ ው ፡ ጊዜ ።

ክፍል ፡ ፩ ፤ ሄ ፡ ብሂል ፡ ሀልው ፡ እግዚ አብሔር ።

ሄ ፡ ማለት ፡ ሀልው ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ፀፀ፫ ፡ ምህረኒ ፡ እግዚኦ ፡ ፍኖተ፡ጽድቅከ

አቤቱ ፡ እውነተኛውን ፡ ሕግ ህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

መእኀሥሣ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

ፀፀ፬ ፡ አለብወኒ ፡ መእኀሥሥ ፡ ሕገከ ።

ሕግህን ፡ እሻ ፡ ዘንድ ፡ ዕውቀት ፡ ግለጽልኝ ።

መአዕቀቦ ፡ በኵሉ ፡ ልብየ ።

በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ልጠብቀው ።

ፀፀ፭ ፡ ምርሐኒ ፡ ፍኖተ ፡ ትእዛዝከ ።

አዝዘህ ፡ የሠራኸው ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፡ አስተምረኝ ።

አስመ ፡ ኪያሃ ፡ ፈቀድኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

ፀፀ፮ ፡ ሚጥ ፡ ልብየ ፡ ውስተ ፡ ስምዕከ ።

ልቡናዬን ፡ ወደ ፡ አምልኮትህ ፡ መልሰው ።

ወአኮ ፡ ውስተ ፡ ትዕግልት ።

ወደ ፡ ጣዖት ፡ ያይደለ ፤ ወይስትዩ ፡ ወይነ ፡ ትዕግልት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አምላኮሙ ፡ እንዲል ። አን ድም ፡ (ሚጥ) ፡ ልቡናዬን ፡ ወደ ፡ ሕግህ ፡ መልስ ። (ወአኮ) ፡ ወደ ፡ ቅሚያ ፡ ያይደለ ።

ፀፀ፯ ፡ ሚመን ፡ ለአዕይንትየ ፡ ከመ ፡ ኢ ይ ር አ ያ ፡ ከ ን ኖ ።

ከንቱ ፡ ነገርን ፡ እንዳያዩ ፡ ወይ ኖቼን ፡ መልሳቸው ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ እንዳያመልኩ ፡ ሰውነቶቼን ፡ ወደ ፡ አምልኮትህ ፡ መልሳቸው ።

መአሕይወኒ ፡ በፍኖትከ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቄ ፡ አድነኝ ።

ፀፀ፰ ፤ አቅም ፡ ለገብርከ ፡ ዘነበብከ ፡ ሙ ስ ተ ፡ ነ ቢ ብ ከ ።

አቅም ፡ ለገብርከ ፡ ዘነበብከ ፡ ለገብርከ ፡ ይላል ፤ እውነት ፡ በሚ ናገር ፡ ቃልህ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡

ነሊቆን ፡ ብለህ ፡ የተናገርኸው
ን ፡ ቃል ፡ ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡
አድርግለት ። አንብብ ፡ በውስተ ፡
ወንጌሉ ፡ ዘሠርዐ ፡ ክርስቶስ ፡
እንዲል ።

፴፱ ፤ አ እ ት ት ፡ እ ም ኔ የ ፡ ጽዕለ ት ፡
ዘ ተ ሐ ዘ ብ ኩ ።

የተጠራጠርሁትን ፡ ስድቡን ፡ ከ
ኔ ፡ አርቀው ። ባሮቻችን ፡ ናችሁ ፡
አትወጡም ፡ እያሉ ፡ ይሰድቧቸ
ዋል ፤ እውነት ፡ ባቢሎን ፡ ተማ
ርኮ ፡ ለመቅረት ፡ ነው ፡ የፈጠር
ከን ፡ እያሉ ፡ ያዝናሉና ።

እስመ ፡ ሠናይ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

፵ ፤ ናሁ ፡ ፈተውኩ ፡ ትእዛዘከ ።

እንሆ ፡ ሕግህን ፡ ወድጃለሁና ።

መአሕይወኒ ፡ በጽድቅከ ።

በቸርነትህ ፡ አድነኝ ።

ክፍል ፡ ፮ ፤ ዋው ፡ ብሂል ፡ ዋሕድ ፡ እግ
ዚ አ ብ ሔ ር ።

ዋው ፡ ማለት ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡
ሐው ። እምብዝኀ ፡ ትንታጉ ፡ ለ
ሐው ፡ ይበዝኀ ፡ ፍሕሙ ፡ እን
ዲል ። ሚራ ፡ ፲፭ ፡ ፴፪ ።

፵፭ ፤ ይ ም ጻ እ ፡ ላዕሌየ ፡ ምሕረትከ ፡
እ ግ ዚ አ ።

ሊተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ ቸር
ነትህ ፡ ይደረግልኝ ።

እግዚአ ፡ አድኅኖትከ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

አቤቱ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡
በተናገርኸው ፤ አንድም ፡ ሕግ
ህን ፡ በመጠበቄ ፡ ትድግናህን ፡
አድርግልኝ ።

፵፪ ፤ አወ ሥ አሙ ፡ ቃለ ፡ ለእለ ፡ ይጼዕሉኒ

እኔስ ፡ አልችልልህምና ፡ ለሚ
ሰድቡኝ ፡ ለባቢሎናውያን ፡ ቃል ፡
መልስላቸው ። ስጠኝ ፡ ፍጆታ ፡
ማለት ፡ አይደለም ፤ የግብር ፡
ሙግት ፡ ነው ።

እስመ ፡ ተወከልኩ ፡ በቃልከ ።

በሕግህ ፡ አምኛለሁና ።

፵፫ ፤ አ ታ አትት ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ እ ም
አ ፉ የ ፡ ለ ግ ሙ ራ ።

እውነተኛውን ፡ ሕግህን ፡ ካን
ደበቴ ፡ ፈጽመህ ፡ አታርቀው ።

እስመ ፡ ተወከልኩ ፡ በኵነኔከ ።

በሕግህ ፡ ጸንቻለሁ ፡ አምኛለ
ሁና ።

፵፬ ፤ ወአዐቅብ ፡ ሕግከ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሕግህን ፡ እጠብቃ
ለሁ ።

ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ለዘላለሙ ።

፵፮ ፤ ወአሐውር ፡ ስፋሐ ።

ስፋሐ ፡ አእምሮ ፡ ሁኜ ፡ እኖ
ራለሁ ።

እስመ ፥ ትእዛዘከ ፥ ኅሠሥኩ ።
ሕግህን ፥ ሽቻለሁና ።

፵፮ ፤ ወእነግር ፥ ስምዐከ ፥ በቅድመ ፥ ነገ
ሥት ፥ ወኢይትኀፈር ።
በነገሥታቱ ፥ ፊት ፥ ሕግህን ፥ አምልኮህን ፥ እናገራለሁ ፤ ስና ገርም ፥ አላፍርም ፤ እንዲህ ፥ የ ሚሉ ፥ ሠለስቱ ፥ ደቂቅ ፥ ናቸው ።

ግብ ፥ ፲፫ ፥ ፲፯ ። ሮሜ ፥ ፩ ፥ ፲፮ ።
፩ ፥ ቆሮ ፥ ፩ ፥ ፲፰ ፥ ገላ፩ ።

፵፯ ፤ ወአነብብ ፥ ትእዛዘከ ፥ ዘአፍቀርኩ ጥ ቀ ።
ፊጽሜ ፥ የወደድሁትን ፥ ሕግህን ፥ እነግራለሁ ፤ አስተምራለሁ ።

፵፰ ፤ ወአነሥእ ፥ እደውየ ፥ ኀበ ፥ ትእዛ ዝከ ፥ ዘአፍቀርኩ ።

እደ ፥ ቃሌን ፥ ለጸሎት ፥ እደ ፥ ሥጋ ዬን ፥ ለመሥዋዕት ፥ እደ ፥ ልቡ ናዉን ፥ ለአንክሮ ፥ ለተዘክሮ ፥ ወደ፡ ወደድሁት ፥ ሕግህ ፥ አነሣለሁ ።

ወእዛዋዕ ፥ በትእዛዝከ ።

ሕግህን ፥ ግብር ፥ አድርጌ ፥ እኖ ራለሁ ።

ክፍል ፥ ፯ ፤ ዛይ ፥ ብሂል ፥ ዝኩር ፥ እግ ዚ አ ብ ሔ ር ።

ዛያ ፥ ማለት ፥ ዝኩር ፥ እ ግ ዚ አ ብሔር ፥ ማለት ፥ ነው ።

፵፱ ፤ ተዘከር ፥ ቃለከ ፥ ዘአስፈውኮ ፥ ለግ ብ ር ከ ።
ለባሪያህ ፥ ለኤርምያስ ፥ ተስፋ ፥ ያደረግህለትን ፥ ሚጠትን ፥ አስ ብ ፤ አስበህ ፥ አውጣን ።

፶ ፤ ወይእቲ፡ አስተፍሥሓተኒ፡በሕማምየ ይህችውም ፥ ሚጠት ፥ በመከራዬ ፥ ጊዜ ፥ ደስ ፥ አሰኘችኝ ።

አስመ ፥ ቃልከ ፥ አሕየወኒ ።
በተናገርኸው ፥ ጊዜ ፤ አንድም ፥ ተናግረህ ፥ የሠራኸው ፥ ሕግህ ፥ አድ ኖኛልና ።

፶፩ ፤ ዕቡያን ፥ ዐመፁ ፥ ፈድሓደ ።

ዕቡያን ፥ ባቢሎናውያን ፤ አንድም ፥ ኤኮንያን ፥ ሴዴቅያስ ፥ ፈጽመው ፥ በደሉ ።

ወእመሕግከሰ ፥ ኢተግሕሥኩ ።

እኔ ፥ ግን ፥ ከሕግህ ፥ አልወጣሁም ።

፶፪ ፤ ተዘከርኩ ፥ ፍትሓከ ፥ ዘእምዓለም ።

ዓለም ፥ ከተፈጠረ ፥ ዠምሮ ፥ ሲነ ገር ፥ የሚኖር ፥ ፈርዶህ ፥ የሠራኽ ውን ፥ ሕግህን ፥ አሰብሁ ።

ወቶፈግሕኩ ፥ እግዚኦ ።

አቤቱ ፥ ደስ ፥ አለኝ ። ኢሳ ፥ ፵፯፡፱።

፶፫ ፤ ኀዘን ፥ አኀዘኒ ፥ እምኃጥኣን ፥ እለ ኅ ደ ጉ ፥ ሕ ገ ከ ።
ሕግህን ፥ ካፈረሱ ፥ ከኃጥኣን ፥ ከባ ቢሎናውያን ፥ የተነሣ ፤ አንድም ፥ ከባቢሎናውያን ፥ የመጣ ፥ መከራ ፥ አገኘኝ ።

፸፱ ፤ መዝሙረ ፡ ኮነኒ ፡ ሠናይከ ።

ሕግህ ፡ መጫወቻ ፡ ኾንኝ ።

በብሔር ፡ በጎበ ፡ ፈለስኩ ።

ተሰድጄ ፡ በሄድኩበት ፡ ሀገር ፡ በባ
ቢሎን ።

፸፩ ፤ ተዘከርኩ ፡ በሌሊት፡ስመከ፡እግዚአ

አቤቱ ፡ በቁሙ ፡ በሌሊት ፤ አንድ
ም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ የአምላክነ
ትህን ፡ ስም ፡ አሰብሁ ።

ወዐቀብኩ ፡ ሕገከ ።

ሕግህንም ፡ ጠበቅሁ ።

፸፪ ፤ ወይእቲ ፡ ኮነተኒ ።

ይህችውም ፡ ረባችኝ ፤ ጠቀመ
ችኝ ።

እስመ ፡ ሠናይከ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

ክፍል ፡ ፳ ፤ ሔት ፡ ብሂል ፡ ሕያው ፡
እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር ።

ሔት ፡ ማለት ፡ ሕያው ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገ
ናኝ ፡ ዛሀን ።

፸፫ ፤ ክፍልየ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡
ፅዋ ፡ ተርታዬ ፡ ነው ።

ወዕቤ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕገከ ።

ሕግህን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠ
ብቁ ፡ ብዬ ፡ አዘዝሁ ።

፸፬ ፤ ሰአልኩ ፡ ገጸከ ፡ እግዚአ ፡ በኩሉ፡
ልብየ ።

አቤቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡
ገጸ ፡ ምሕረትህን ፡ ገጸ ፡ ረድኤ
ትህን ፡ ሻሁ ።

ተሣሃለኒ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኃለቆን ፡ ብለህ ፡
በተናገርኸው ፤ አንድም ፡ ሕግ
ህን ፡ በመጠበቄ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

፸፭ ፤ ወኀለይኩ ፡ በእንተ ፡ ፍናዊከ ።

የሕግህን ፡ ነገር ፡ አሰብሁ ፡ ማ
ለት ፤ ሕግህን ፡ ጠበቅሁ ።

ሚጥኩ ፡ እግርየ ፡ ውስተ ፡ ስምዕከ ።

እግረ ፡ ኅሊናዬን ፡ ወደ ፡ አምል
ኮትህ ፡ መለስሁ ።

፸፮ ፤ አጥባዕኩ ፡ ወኢናፈቁ ፡ ለዐቂበ ፡
ት እ ዛ ዝ ከ ።

ሕግህን ፡ ለመጠበቅ ፡ ጨከንሁ ፤
ያድነኝን ፡ ይሆን ፡ አያድነኝ ፡
ብዬ ፡ አልተጠራጠርሁም ።

፸፯ ፤ ኣሕባለ ፡ ኃጥአን ፡ ተማፈራ፡ላዕሌየ
ኃጥኣን ፡ ባቢሎናውያን ፡ ገመድ ፡
ዘረገፉብኝ ፡ ማለት ፤ ምክር ፡ መከ
ሩብኝ ፡ ጦር ፡ ሸመቁብኝ ።

ወሕገከሰ ፡ ኢረሳዕኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሕግህን ፡ አልዘነጋ
ሁም ።

፸፰ ፤ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እትነሣእ ።

በመከራዬ ፡ ጊዜ ፤ አንድም ፡

በቁሙ ፥ በመንፈቀ ፥ ሌሊት ፥ እነሣለሁ ።

ከመ ፥ እግኒይ ፥ ለከ ፥ በእንተ ፥ ሥነጌ ፥ ጽ ድ ቅ ከ ።

ስለ ፥ እውነተኛው ፥ ሕግህ ፥ እገዛልህ ፥ ዘንድ ፥ እትነሣእ ።

ፀ፫ ፤ ከማሆሙ ፥ አነ ፥ ለኵሎሙ ፥ እለ ፥ ይ ፈ ር ሁ ከ ።

እንደሚፈሩህ፡ እንደሚያመልኩብህ እንደ ፥ ነቢያት ፥ እንደ ፥ ካህናት ፥ እትነሣእ ።

ወእለ ፥ የዐቅቡ ፥ ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፥ እንደሚጠብቁ ።

ፀ፬ ፤ ሣህልከ ፥ እግዚኦ ፥ መልዐ፡ ምድረ

አቤቱ ፥ ይቅርታህ ፥ ቸርነትህ ፥ ምድርን ፥ መላ ፥ ማለት ፤ ለሰው ፥ ሁሉ ፥ ተደረገ ። አንድም ፥ ትሑ ታኑን ፥ አንድም ፥ ደቂቀ ፥ አዳ ምን ፥ ፈጠረ ።

ወምህረኒ ፥ ሥነጌከ ።

ሕግህን ፥ ግለጽልኝ ፥ አስተምረኝ ።

ክፍል ፥ ፱ ፤ ጤት ፥ ብሂል ፥ ጠቢብ ፥ እግ ዚ አ ብ ሔ ር ።

ጤት ፥ ማለት ፥ ጠቢብ ፥ እ ግ ዚ አብሔር ። ማለት ፥ ነው ።

ፀ፭ ፤ ሠናይተ ፥ ገበርከ ፥ ላዕለ ፥ ገብርከ።

ሊተ ፥ ሲል ፥ ነው ፤ ለኔ ፥ ለባሪያህ ፥ ሚጠትን ፥ አደረግህልኝ ።

እግዚኦ ፥ በከመ ፥ ቃልከ ።

አቤቱ ፥ ሕግህን ፥ እንደ ፥ መጠ

በቄ ፤ እንድም ፥ ወሰብዓ ፥ ዓም ፥ ብለህ ፥ እንደ ፥ ተናገርህ ።

ፀ፮ ፤ ሠናይተ ፥ ምክረ ፥ ወጥበበ ፥ ምህረኒ

በጎ ፥ ምክር ፥ ጥበብን ፥ ግለጽ ልኝ ። አንድም ፥ ኢታምልክን ፥ ዘጠኑን ፥ ሕገጋት ፥ ግለጽልኝ ፥ አስተምረኝ ።

እስመ ፥ ተአመንኩ ፥ በትእዛዝከ ።

በሕግህ ፥ ጸንቻለሁና ።

ፀ፯ ፤ ወአንሰ፡ዘእንበለ፡እሕምም፡ኀሳሕኩ

ኀጢአት ፥ ሳልሠራ ፥ ተማርኬ ፥ ወደ ፥ ባቢሎን ፥ ወረድሁ ። አን ድም ፥ ጣዖት ፥ ሳላመልክ ፥ የሪያ ፥ ሥጋ ፥ ሳልበላ ፥ ከባቢሎን ፥ ወደ ፥ ኢየሩሳሌም ፥ ወጣሁ ።

በእንተዝ ፥ ዐቀብኩ ፥ ነቢበከ ።

ስለዚህ ፥ ሕግህን ፥ ጠበቅሁ ።

ፀ፰ ፤ ኄር፡ አንተ ፥ እግዚኦ ።

አቤቱ ፥ አንተ ፥ ቸር ፥ ነህ ።

ወበኂሩትከ ፥ ምህረኒ ፥ ሥነጌከ ።

በቸርነትህ ፥ ሕግህን ፥ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

ፀ፱ ፤ በዝኆ ፥ ላዕሌየ ፥ ዐመፃሆሙ ፥ ለዕ ቡ ያ ን ።

የባቢሎናውያን ፥ አንድም ፥ የኤ ኮንያን ፥ የሴዴቅያስ ፥ ነገር ፥ በዛብኝ ።

ለህ ፥ እንደ፡ ተናገርከው ፤ አንድም ፥ ሕግህን ፥ እንደ ፥ መጠበቄ ፥ ይደ ረግልኝ ።

ፅ፯ ፤ ይምጽአኒ ፥ ሣህልክ ፥ ወእሕየው።

ቸርነትህ ፥ ይደረግልኝ ፤ ወእሕየ ው ፤ እኔም ፥ ከመከራው ፥ ልዳን ።

እስመ ፥ ተምሀርየ ፥ ውእቱ ፥ ሕግከ ።

ሕግህ፥ መማሬ ፥ ትምርቴ ፥ ነውና ። አንድም ፥ መማሬ ፥ ትምርቴ ፥ ሕ ግህ ፥ ነውና ።

ፅ፰ ፤ ይትኃፈሩ ፥ ዕቡያን ፡እስመ ፥ ዐመፃ መከሩ ፥ ላዕሌየ ።

ባቢሎናውያን ፥ በኔ ፥ ዐመፃን ፥ መ ክረዋልና ፤ ይፈሩ ። አንድም፡ እለ ፥ ዐመፃ ፥ መከሩ ፥ በኔ ፥ ዐመፅን ፥ የ መከሩ ፥ ባቢሎናውያን ፤ አንድም ፥ ኤኮንያን ፥ ሴዴቅያስ ፥ ይፈሩ ፤ ይዋ ረዱ ።

ወአንሰ ፥ እዛዋዕ ፥ በትእዛዝከ ።

እኔ ፥ ግን ፥ ሰው ፥ ቢመክር ፥ ምን ፥ ያደርጋል ፥ ብዬ ፥ ሕግህን ፥ ተግ ግባር ፥ አድርጌ ፥ እኖራለሁ ።

ፅ፱ ፥ ይግበኡኒ ፥ እለ ፥ ይፈርሁከ ።

የኔስ ፥ የኔ ፥ ነውና ፤ የሚፈሩህ ፥ የሚ ያመልኩህ ፥ ነቢያት ፥ ካህናት ፥ ከባ ቢሎን ፥ ወደ ፥ ኢየሩሳሌም ፥ ይመለ ሱልኝ ። የኃጥኡ ፥ ዳፋ ፥ ጻድቁን ፥ ያዳፉ ፥ እንዲሉ ፥ የኔ ፥ ዳፋ ፥ ተርፍ ቸው ፥ በባቢሎን ፥ ኣይቅሩ ።

ወእለ ፥ የአምሩ ፥ ስመከ ።

ስምህን ፥ ዐውቀው ፥ የሚወዱ ።

ፅ፲ ፤ ለይኩን ፥ ልብየ ፥ ንጹሐ ፥ በሕጎኔከ ከመ ፥ ኢትኅፈር ።

በመከራው ፥ እንዳላፍር ፥ ልቡናዬ ፥ በሕግህ ፥ ከኀጢአት ፥ በሃይማኖት ፥ ከክሕደት ፥ ንጹሕ ፥ ይሁን ።

ክፍል ፥ ፲፩ ፥ ካፍ ፥ ብሂል ፥ ከሃሊ ፥ እግ ዚአብሔር ።

ካፍ ፥ ማለት ፥ ከሃሊ ፥ እግዚ አ ብ ሔር ፥ ማለት ፥ ነው ።

ፅ፩ ፤ ኀለፈት ፥ ነፍስየ ፥ ውስተ ፥ አድኅ ኖ ት ከ ።

ሰውነቴ ፥ ትድግናህን ፥ ናፈቀች ፤ ወደደች ።

ወተወከልኩ ፥ በቃልከ ።

ወሰብዓ ፥ ዓም ፥ ብለህ ፥ በተናገርከ ው ፤ አንድም ፥ በሕግህ ፥ አመንሁ ።

ፅ፪ ፥ ደክማ ፥ አዕይንትየ፡ ለመድኃኒትከ

ዐይኖቼ ፥ ትድግናህን ፥ በመሻት ፤ አንድም ፥ በመመልከት ፥ ደከሙ ። እንደ ፥ ባለቀጠሮ ፥ ካሁን ፥ ካሁን ፥ ይመጣል ፥ እያለ ፥ መንገድ ፥ መን ገዱን ፥ እንዲመለከት ።

እንዘ ፥ ይብላ ፥ ማዕዜ ፥ ታስተፌሥሐኒ

ታስተፌሥሐኒ ፥ ቢል ፥ ይቀናል ፥ ከባቢሎን ፥ ወደ ፥ ኢየሩሳሌም ፥ አ ውጥተህ ፥ መቼ ፥ ደስ ፥ ታሰኘን ፥ ይሆን ፥ እያሉ ።

፹፫ ፤ አ ስ መ ፡ ኪ ን ኩ ፡ ከመ ፡ ዝ ቅ ፡ ውስተ ፡ አስሐትያ ።

ከውርጭ ፡ እንዳደረ ፡ ራዋት ፡ ሁኛ ለሁና ፡ ማለት ፤ ተዋር ዲ ቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

ወሶነኔከስ ፡ ኢረሳዕኩ ።

እኔ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ጸናብኝ ፡ ብዬ ፡ ከሕግህ ፡ አልወጣሁም ።

፹፬ ፤ ኂመጠን ፡ እማንቱ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለ ገ ብ ር ከ ።

ባሪያህ ፡ ትሩፍ ፡ በባቢሎን ፡ የሚ ኖረው ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ብዬህ ፡ የለ ምን ፡ ቢለው ።

ማዕዜ ፡ ትፈትሕ ፡ ሊተ ፡ እምእለ ፡ ይሰዱኒ

ማርከው ፡ ከሚወስዱኝ ፡ ከባቢሎና ውያን ፡ መች ፡ ትፈርድልኛለህ ፡ ይላል ።

፹፭ ፤ ነገሩኒ ፡ ኃጥኣን ፡ ዛውዐ ።

ኃጥኣን ፡ ባቢሎናውያን ፡ ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ነገሩኝ ፡ ማለት ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛችኋለን ፡ አሉ ።

ወአኮሰ ፡ ከመ ፡ ሕግከ ፡ እግዚኦ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተና ገርከው ፡ ያይደለ ። አንድም ፡ (ነገ ሩኒ) ፡ ጣዖት ፡ አምልክ ፡ አሉኝ ። ወያማስን ፡ አውግረ ፡ ዛውዕ ፡ እን ዲል ። (ወአኮሰ) ፡ ኢ ፡ ምልክ ፡ ባዕ ደ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተናገርከው ፡ ያይደለ ።

፹፮ ፤ ኵሉ ፡ ትእዛዝከ ፡ ጽድቅ ።

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ።

በዐመፃ ፡ ሰደዱኒ ፡ ርድአኒ ።

በግፍ ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ ሰደ ውኛልና ፡ ርዳኝ ፤ አድነኝ ።

፹፯ ፤ ሕቀ ፡ ከመ ፡ ዘእምደምሰሱኒ ፡ ው ስ ተ ፡ ም ድ ር ።

ከባቢሎን ፡ ሊያጠፉኝ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቶኝ ፡ ነበረ ። አንድም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሊያወርዱኝ ፡ ጥ ቂት ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ቀርቶኝ ፡ ነበረ ።

ወአንሰ ፡ ኢኀደጉ ፡ ትእዛዘከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሕግህ ን ፡ አልተውሁም ፡ ማለት ፤ አላፈረስሁም ።

፹፰ ፤ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አሕይወኒ ።

እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ከመከራው ፡ አድነኝ ።

ወእዕቀብ ፡ ሰምዐ ፡ አፉከ ።

ባንደበትህ ፡ የሠራኸው ፡ አምልኮ ትህን ፡ ልጠብቅ ።

ክፍል ፡ ፲፱ ፤ ላሜድ ፡ ብሂል ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ።

ላሜድ ፡ ማለት ፡ ልዑል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በ ገናኝ ፡ ሁሉ ።

፻፲፱ ፤ እግዚአ ፡ ለዓለም ፡ ይ ነ ብ ር ፡ ቃልከ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

አቤቱ ፡ ለይኩን ፡ ብለህ ፡ የፈጠርከው ፡ ብርሃን ፤ አንድም ፡ ሕግህ ፡ ባለ ፣ ለፍ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

፯ ፤ ወለተ ፡ ውልደ ፡ ትውልድ ፡ ጽድቅከ ።

ቸርነትህም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ሲ ነ ገር ፡ ይኖራል ።

ፃረርካ ፡ ለምድር ፡ ወትነብር ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ ምድርን ፡ ፈጠርኻት ፤ ለዘላለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ።

፺፩ ፡ ወበትእዛዝከ ፡ ይቀውም ፡ ዕለት ።

የፈጠርኸው ፡ ፀሓይ ፡ ባንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። ስማ ፡ ለአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዲል ።

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ቀንይከ ።

ሁሉን ፡ ፈጥረኻልና ። አ ፡ አብ ፡ ኵሎ ፡ ቀነይከ ፡ እንዲል ።

፺፪ ፤ ሶበ ፡ አኮ ፡ ሕግከ ፡ ተምህርየ ፡ ውእቱ

ሕግህ ፡ መምሬ ፡ ትምርቴ ፡ ባይሆን ፡

ትካት ፡ እምተኃጕልኩ ፡ በኀሣርየ ።

በኀጢአት ፡ ሳለሁ ፡ አንድም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ በጠፋሁ ፡ ነበር ።

፺፫ ፤ ለዓለም ፡ ኢይረስዕ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ለዘላለም ፡ አልዘነጋም ።

አስመ ፡ ቦቱ ፡ አሕየውከኒ ።

ሕግህን ፡ በመጠበቅ ፡ ከመከራ ፡ አድነኸኛልና ።

፺፬ ፤ ዘዚአከ ፡ አነ ፡ አድኅንኒ ።

እኔ ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ነኝና ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ ኵነኔከ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፺፭ ፤ ኪያየ ፡ ይጸንሑ ፡ ኃጥኣን ፡ ይቅትሉኒ ።

ባቢሎናውያን ፡ ይገሉኝ ፡ ዘንድ ፡ ያደፍጡብኛል ፤ ይሸምቁብኛል ።

እስመ ፡ ስምዐከ ፡ ለበውኩ ።

አምልኮትህን ፡ ይጥለሁ ፤ ሕግህን ፡ ጠብቄ ፡ አለሁና ።

፺፮ ፤ ለኵሉ ፡ ግብር ፡ ርኢኩ ፡ ማኅለቅቶ ።

የሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ዐወቅሁ ፤ ቢገዙ ፡ ቢነዱ ፡ ያልፋል ።

ወትእዛዝከሰ ፡ ርኁብ ፡ ፈድፋደ ።

ሕግህ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ሰፊ ፡ ነው ፤ አያልፍም ።

ክፍል ፡ ፲፫ ፤ ሜም ፡ ብሂል ፡ ምዑዝ ፡ እግዚአብሔር ።

ሜም ፡ ማለት ፡ ምዑዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፺፯ ፤ ጥቀ ፡ አፍቀርኩ ፡ ሕገከ ፡ እግዚአ ።

አቤቱ ፡ ሕግህን ፡ ፈጽሜ ፡ ወደድሁ ፤ ናፈቅሁ ።

ፈቀሉ ፡ አሚረ ፡ ተምሀርየ ፡ ውእቱ ።

ዕለት፡ ዕለት፡ ሕግህ፡ መምሬ፡ ትምርቴ ፡ ነውና ።

፻፷ ፡ ወእምጸላዕትየ ፡ አጥበበኒ፡ትእዛዝኪ

ከጠላቶቼ ፡ ይልቅ ፡ ሕግህ ፡ አራቀቀኝ ።

እስመ ፡ ለዓለም ፡ ሊተ ፡ ውእቱ ።

ለዘላለም፡ መምሬ፡ትምርቴ፡ ነውና።

፻፸ ፡ ወእምኵሎሙ ፡ እለ ፡ መሀሩኒ ፡ ጠበብኩ ።

ከሚያስተምሩኝ ፡ ይልቅ ፡ ሕግህ ፡ አራቀቀኝ ።

እስመ ፡ ተምሀርየ ፡ ውእቱ ፡ ትእዛዝኪ ።

ሕግህ ፡ መምሬ፡ ትምርቴ ፡ ነውና ።

፻፸፩ ፡ ወእምአእሩግኒ ፡ ጠበብኩ ።

ከሽማግሌች ፡ ይልቅ ፡ ዐዋቂ ፡ ሆንሁ ፤ ይህ ፡ ዳንኤል ፡ ነው ። አብዳንኑ ፡ አንትሙ ፡ ዘትኴንኑ ፡ ወለተ ፡ እስራኤል ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕትቱ ፡ ወ ትጠይቁ ፡ ብሏቸዋል ።

እስመ ፡ ትእዛዝኪ ፡ ኀሠሥኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፻፸፪ ፡ እምኵሉ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ ከላዕኩ እግርየ ።

ከዐመፅ ፡ ሥራ፡ ሁሉ ፡ እግረ ፡ ልቡናዬን ፡ ለየሁ ። አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፡ ከባቢሎናውያን ፤ አንድም ፡ ከኤኮንያን ፡ ከሴዴቅያስ ፡ ግብር ፡ እግረ ፡ ልቡናዬን ፡ ከለከልሁ ።

ከመ ፡ እዕቀብ ፡ ነቢበከ ።

ተናግረህ ፡ የሠራኸውን ፡ ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፻፸፫ ፡ ወኢተግሣኩ ፡ እምኵነኔከ ።

ከሕግህም ፡ አልወጣሁም ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ምህርከኒ ።

አንተ ፡ ገልጸኸልኛል ፡ አስተምረኸኛልና ።

፻፸፬ ፡ ጥዑም ፡ ለጕርዔየ ፡ ነቢብከ ።

ሕግህ ፡ ለሰውነቴ ፡ የተስማማ ፡ ነው ።

እመዓር ፡ ወምከር ፡ ጥዕመኒ ፡ ለአፋየ ።

ከመዓር ፡ ከሸንኮር ፡ ይልቅ ፡ ላንደበቴ ፡ የጣፈጠ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ የተስማማ ፡ ነው ።

፻፸፭ ፡ ወእምትእዛዝከ ፡ ለበውከ ።

ሕግህን፡ ከመጠበቄ፡ የተነሣ፡ ቢጠብቁት ፡ እንዲያድን ፡ ባይጠብቁት ፡ እንዲያጠፋ ፡ ዐወቅሁ ።

በእንተዝ ፡ ኵሉ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ፡ጸላዕኩ

ስለዚህ ፡ የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ጸላሁ ። አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፡ የባቢሎናውያንን ፤ አንድም ፡ የኤኮንያንን፡ የሴዴቅያስን ፡ ግብር ፡ ተውሁ ፤ ጸላሁ ።

ክፍል ፣ ፲፬ ፣ ኖን ፣ ብሂል ፣ ንጉሥ ፣ እግዚአብሔር ።

ኖን ፣ ማለት ፣ ንጉሥ ፣ እግዚአብሔር ፣ ማለት፣ ነው፤ ቢገናኝ ፣ መና ።

፻፳ ፤ ማኅቶት ፣ ለእግርየ ፣ ሕግከ ።

ለእገርየም ፣ ይላል ፤ ሕግህ ፣ ለሰው ነቴ ፣ ፋና ፣ ነው ።

ብርሃን ፣ ለፍኖትየ ።

ኢታምልክም ፣ ለሥራዬ ፣ ፀሐይ ፣ ነው ። ከፋና ፣ ብርሃን፣ የፀሐይ ፣ ብርሃን ፣ እንዲበልጥ ፣ ከዘጠኙም፣ ኢታምልክ ፣ ትበልጣለችና ። ፻ ፣ ቆሮ፣ ፲፫ ። ፻፡ ጴጥ ፣ ፩ ፣ ፲፱ ።

፻፲ ፣ መሐልኩ ፣ ወአጥባዕኩ ፣ ከመ ፣ አዕቀብ ፣ ሕጎኔ ፣ ጽድቅከ ።

እውነተኛውን ፣ ሕግህን ፣ እጠብቅ፣ ዘንድ ፣ ጨክኜ ፣ ማልሁ ።

፻፲፩ ፣ ወሐመምኩ ፣ ፈድፋደ ።

ፈጽሜ ፣ ባለመከራ ፣ ሁኛለሁና ።

እግዚኦ ፣ እሕይወኒ ፣ በከመ ፣ ነቢብከ ።

አቤቱ ፣ በሕግህ ፤ አንድም ፣ ወሰብዓ ፣ ዓም ፣ ብለህ ፣ በተናገርከው ፣ አድነኝ ።

፻፲፪ ፣ ሥመር ፣ እግዚኦ ፣ ቃለ ፣ አፉየ ።

አቤቱ ፣ ልመናዬን ፣ ወደህ ፣ ተቀበል ።

ወምህረኒ ፣ ሕጎከ ።

ሕግህን ፣ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፲፫ ፣ ነፍስየ ፣ ውስተ ፣ እዴከ ፣ በዕለ ፣ ኵሉ ፣ ጊዜ

ሁል ፣ ጊዜ ፣ ሰውነቴን ፣ ባንተ ፣ እጅ ፣ ሥልጣን ፣ አስጠብቃለሁ ።

ወኢረሳዕኩ ፣ ሕገከ ።

ሕግህንም ፣ አልዘነጋሁም ።

፻፲፬ ፣ ሠርዉ ፣ ሊተ ፣ ኃጥኣን ፣ መሥገርተ ።

ባቢሎናውያን ፣ ምክር ፣ መከሩብኝ፤ ጦር ፣ ሸመቁብኝ ።

ወኢስሕትኩ ፣ እምትእዛዝከ ።

እኔ ፣ ግን ፣ ሰው ፣ ቢመክር ፣ ምን ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ነው ፣ ብዬ ፣ ከሕግህ ፣ አልወጣሁም ።

፻፲፭ ፣ ወወረስኩ ፣ ስምዐከ ፣ ለዓለም ።

አምልኮትህን ፣ ለዘላለም ፣ ገንዘብ ፣ አደረግሁ ፤ አደረግሁ ፣ እንጂ ፤ ኢረሳዕኩ ።

እስመ ፣ ሐሤቱ ፣ ለልብየ ፣ ውእቱ ።

አምልኮትህ ፣ ለልቡናዬ፣ ተስፋው ፣ ነውና ። ኤር ፣ ፲፭ ፣ ፲፯ ።

፻፲፮ ፣ ሜጥኩ ፣ ልብየ ፣ ከመ ፣ እግበር ፣ ትእዛዘ ከ ።

ሕግህን ፣ እጠብቅ ፣ ዘንድ ፣ ልቡናዬን ፣ ወደ ፣ አምልኮትህ ፣ መለስሁ ።

ለዓለም ፣ ዘእንበለ ፣ ሐሰ ።

እግበር ፣ ዘእንበለ ፣ ሐሰ ፣ ሜጥኩ ፣ ዘእንበለ ፣ ሐሰ ፣ በል ፤ ለዘላለሙ ፣ ያለነውር ፣ ያለነቀፋ ።

ዳልሆን ፡ አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ ወደድሁ ።

፻፳ ፡ አውድድ ፡ ውስተ ፡ ሥጋየ ፡ ፈሪሆተከ

ቅኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ በሰውነቴ ፡ አስማማ ።

አስመ ፡ ፈራህኩ ፡ እምኵነኔከ ።

ከሕግህ ፡ የተነሣ ፡ ፈርቻለሁና ።

ክፍል ፡ ፲፮ ፡ ዓ ፡ ብሂል ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአ ብ ሔ ር ።

ዓ ፡ ማለት ፡ ዐቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ አ ፡ አብ ፡ ሁሉ ፡ ሰዓታት ፡ ጋዳ ፡ ለከ ።

፻፳፩ ፡ ገበርከ ፡ ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ።

ፍትሕንና ፡ ጽድቅን ፡ አንድ ፡ ወ ገን ፡ አድርገህ ፡ ለባሪያህ ፡ ለትሩ ፍ ፡ ሚጠትን ፡ አደረግህለት ።

ኢትመዋዕኒ ፡ ለእለ ፡ ይሣቅዩኒ ።

ሥቃይ ፡ ለሚያጸኑብኝ ፡ ለባቢሎና ውያን ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠኝ ።

፻፳፪ ፡ ጸንሐ ፡ ለገብርከ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ በበጎ ፡ ወረታ ፡ በበጎ ፡ ረድኤት ፡ በበጎ ፡ ሚጠት ፡ ቁየው ።

ወኢይትዐገሉኒ ፡ ዕቡያን ።

ባቢሎናውያን ፡ እንዳይቀሙኝ ፡ ለጊዜውማ ፡ ቀምተውት ፡ የለምን ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ቀሙኝ ፡ እንዳይቀሩ ።

፻፳፫ ፡ ደክማ ፡ አዕይንትየ ፡ ለእድኅኖትከ

ዐይኖቼ ፡ ትድግናህን ፡ በመጠበቅ ፡ ደከሙ ።

ወለቃለ ፡ ጽድቅከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ጎሊቆን ፡ ያልከው ንም ፡ በመሻት ።

፻፳፬ ፡ ግበር ፡ ለገብርከ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ

ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ እንደ ፡ ቸርነ ትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ሚጠትን ፡ አድርግለት ።

ወምህረኒ ፡ ኵነኔከ ።

ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፳፭ ፡ ገብርከ ፡ እነ ፡ አለብወኒ ።

እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ነኝና ፡ ዕውቀትን ፡ ግለጽልኝ ።

ወአእምር ፡ ስምዐከ ።

አምልኮትህን ፡ ሕግህን ፡ ልወቅ ፡ ልጠብቅ ።

፻፳፮ ፡ ጊዜ ፡ ገቢር ፡ ለእግዚአብሔር ።

ለእግዚአ ብሔር ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ በት ፡ ጊዜ ፡ አለው ። አንድም ፡ ለገ ቢር ፡ ለእግዚአ ብ ሔ ር ፡ ለእግዚአ ብ ሔ ር ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለገቢር ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ።

ወ ዐ ለ ዉ ፡ ሕ ገ ከ ።

ባቢሎናውያን ፡ ግን ፡ ሕግህን ፡ አፈ ረሱ ።

፻፳፯ ፡ በእንተዝ ፡ አፍቀርኩ ፡ ትእዛዘከ

እነሱ ፡ እንዳፈረሱ ፡ እኔም ፡ እንዳ ላፈርስ ፡ ሕግህን ፡ ወደድሁ ።

አምወርቅ ፡ ወአምጳዝዮን ።

ከወርቅ ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ ሕግ ህን ፡ ወደድሁ ። አሥ ፡ ፳፫ ፡ ፲፱ ።

፻፸፮ ፡ በእንተዝ ፡ አርታዕኩ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ት እ ዛ ዝ ከ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ማለት ፤ ዐላዋቂ ፡ እንዳልባል ፡ እግረ ፡ ጎሊናዬን ፡ ወደ ፡ ሕግህ ፡ አቀናለሁ ።

ኵሎ ፡ ፍኖተ ፡ ዐመፃ ፡ ጸላዕኩ ።

የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፤ አንድም ፡ ፍኖተ ፡ ዐማፅያን ፤ የባቢሎናውያ ንን ፤ አንድም ፡ የኤኮንያንን ፡ የሴዶ ቅያስን ፡ ግብር ፡ ጸላሁ ።

ክፍል ፡ ፲፯ ፡ ፈ ፡ ብሂል ፡ ፍቁር ፡ እግ ዚ አ ብ ሔ ር ።

ፈ ፡ ማለት ፡ ፍቁር ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ።

፻፸፱ ፡ መንክር ፡ ስምዕከ ።

አምልኮትህ ፡ ሕግህ ፡ ድንቅ ፡ ነው።

በእንተዝ ፡ ኀሠሦ ፡ ነፍስየ ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሰውነቴ ፡ ናፈቀ ችው ፤ ወደደችው ።

፻፸ ፡ ነገረ ፡ ቃልከ ፡ ያበርህ ፡ ወያጠብብ ሕ ፃ ና ን ።

ለይኩን ፡ ብለህ ፡ የፈጠርኸው ፡ ፀ ሓይ ፡ ሕፃናት ፡ ሥጋን ፡ ፈጽሞ ፡ ያራቅቃል ። አንድም ፡ ተናግረህ ፡ የሠራኸው ፡ ሕግህ ፡ ሕፃናተ ፡ ነፍ ስን ፡ ያራቅቃል ።

፻፸፩ ፡ አፋየ ፡ ከሠትኩ ፡ ወነፍስየ ፡ አናኅኩ

አፌን ፡ ከፈትሁ ፡ ልቡናዬንም ፡ አሰፋሁ ፤ የወደዱትን ፡ ምግብ ፡ ኡፍን ፡ ከፍተው ፡ ሆድን ፡ አስፍ ተው ፡ እንዲመገቡት ፡ ባፌም ፡ በል ቤም ፡ ወድጄ ፡ ተቀበልሁ ።

አስመ ፡ ትእዛዘከ ፡ አፍቀርኩ ።

ሕግህን ፡ ሽቻለሁና ።

፻፸፪ ፡ ነጽር ፡ ላዕሌየ ፡ ወተሣሃለኒ ።

ኪያየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ እኔን ፡ በዐይነ ፡ ምሕረት ፡ እየኝ ፡ ተመልከተኝ ፤ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመልክተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

በከመ ፡ ፍት ሐ ሙ ፡ ለእለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስ መ ከ ።

ስምህን ፡ ለሚወዱ ፡ ለነቢያት ፡ ለካህናት ፡ እንድትፈርድላቸው ፡ መጠን ።

፻፸፫ ፡ አርትዕ ፡ ፍኖትየ ፡ ወሐረትየ ፡ በከመ ፡ ነቢብከ ።

ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፤ አን ድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ጎሊቆን ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መንገዴን ፡ አቅናልኝ ፡

ወኢይማዓኒ ፡ ኵሉ ፡ ኃጢአት ።

ባቢሎናዊ ፤ አንድም ፡ በቁሙ ፡ ኀጢአት ፡ ድል ፡ እንዳይነሣኝ ።

ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፮ ። ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።

፻፸፬ ፡ አድኅነኒ ፡ እምትዕግልተ ፡ ዕጓለ እ መ ሕ ያ ው ።

ከሰው ፡ ቅማያ ፡ አድነኝ ። አን

ድም ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ጣዖት ፡ ከማምለክ ፡ አድነኝ ። ወይሰትዩ ፡ ወይነ ፡ ትዕግልት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አምላኮሙ ፡ እንዲል ፡

መእዕቀብ ፡ ትእዛዘከ ።

ሕግህን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ።

፻፻፭ ፡ አብርህ ፡ ገጸከ ፡ ላዕለ ፡ ገብርከ።

ለገብርከ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለባሪያህ ፡ ለትሩፍ ፡ ብርሃነ ፡ ረድኤትህን ፡ አብራለት ። አንድም ፡ አብርተህ ፡ ደስ ፡ አሰኘው ።

መምህረኒ ፡ ኵነኔከ ።

መህረኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሕግህንም ፡ ግለጽልኝ ፤ አስተምረኝ ።

፻፻፮ ፤ ሙታዘ ፡ ማይ ፡ ወረደ ፡ እምአዕ ይ ን ት የ ።

የእንብ ፡ ጕርፍ ፡ ካይኔ ፡ በዝቶ ፡ ፈሰሰ ፤ የብጽብጽ ፡ ነው ።

መእመ ፡ አኮሰ ፡ እምኢዐቀብኩ ፡ ሕገከ።

እምዐቀብኩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የብጽብጽስ ፡ ባይሆን ፡ ሕግህን ፡ በጠበቅሁ ፡ ነበር ። አንድም ፡ (እምኢዐቀብኩ ፡ መከራስ ፡ ባታመጣብኝ ፡ ሕግህን ፡ ባልጠበቅሁም ፡ ነበር ፤ መከራ ፡ ብታመጣብኝ ፡ ጠበቅሁ ፡ እንጂ ። አንድም ፡ (ሙሓዘ ፡ ማይ) ፡ የእንብ ፡ ጕርፍ ፡ ካይኔ ፡ በዝቶ ፡ ፈሰሰ ፡ ማለት ፤ የንስሓ ፡ ነው ። (ወእመ ፡ አኮሰ) ፡ የንስሓ ፡ ባይሆን ፡ ሕግህን ፡ ባልጠበቅሁም ፡ ነበር ፤ የንስሓ ፡ ቢሆን ፡ ጠበቅሁት ፡ እንጂ ። አንድም ፡ መከራ ፡ እየተቀበልሁ ፡ እኔን ፡ አለማዳንህ ፡ ሕግህን ፡ ባልጠብቅ ፡ ነዋ ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፤ ንስሓዬ፡ እውነተኛ፡ ባይሆን ፡ ነዋ ።

ክፍል ፡ ፲፮ ፡ ጸደ ፡ ብሂል ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ።

ጸደ ፡ ማለት ፡ ጻድቅ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ፡ ፋጸ። ከመ ፡ ፋጸ ፡ ቀጢን ፡ ወከመ ፡ መሰንቆ ፡ ሐዋዝ ፡ ያስተፈሥሐኒ ፡ በሰሚየቱ ፡ እንዲል ።

፻፻፯ ፤ ጻድቅ ፡ አንተ ፡ እግዚአ ፡ ወርቱዕ ሎ ፡ ፍ ና ዊ ከ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፤ ሕግህም ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፻፰ ፤ ወአዘዝከ ፡ ስምዐከ ፡ በጽድቅ ።

አምልኮትህን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ ብለህ ፡ አዘዝህ ።

ወርቱዕ ፡ ፈድፋደ ።

ይኸውም ፡ ፈጽሞ ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፻፱ ፤ መስወኒ ፡ ቅንዓተ ፡ ቤትከ ።

ለቤተ ፡ መቅደስህ ፡ አንድም ፡ ለሕግህ ፡ የቀናሁት ፡ መቅናት ፡ እንደሳት ፡ አቃጥሎኛልና ።

እስመ ፡ ረስዑ ፡ ትእዛዘከ ፡ ጸላዕትየ ።

ባቢሎናውያን ፡ ሕግህን ፡ ስለ ፡ ዘነጉ ፡ ኢሳ ፡ ፳፮ ፡ ፯ ።

፻፸፤ ርሱን ፡ ቃልከ ፡ ፈድፋደ ።

ሕግህ ፡ ፈጽሞ፡ የጋለ፡ የፈላ፡ ነው ።

ወኀብርከሰ ፡ አፍቀሮ ።

ሕግህ ፡ እንዲህ ፡ የጋለ ፡ የፈላ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ባሪያህም ፡ እጠብቀዋለሁ ።

፻፸፩ ፤ ወሬዛ ፡ አነ ፡ ወትሑት ።

እኔ ፡ ትሑት ፡ ወሬዛ ፡ ነኝ ፤ የጕል ማሳ ፡ ልቡ ፡ ከደረቱ ፡ እንዳለው ፡ ያለሁ ፡ አይደለሁም ።

ሕገከሰ ፡ አረሳዕኩ ።

ሕግህን ፡ አልዘነጋሁም ።

፻፸፪ ፤ ጽድቅከሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘለዓለም ።

ሕግህ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ እውነተኛ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ወቃልከኒ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ።

ኢታምልክም ፤ አንድም ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ያልከው ፡ ቃልህ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

፻፸፫ ፤ ሕማም ፡ ወምንዳቤ ፡ ረከበኒ ።

መከራ ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ፡ አገኘኝ።

ወትእዛዝከሰ ፡ ተምህርየ ፡ ውእቱ ።

ሕግህ ፡ ግን ፡ መምሬ ፡ ትምርቴ ፡ ነው ።

፻፸፬ ፤ ጽድቅ ፡ ውእቱ ፡ ስምዕከ፡ለዓለም

አምልኮትህ ፡ ለዘላለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ እውነተኛ ፡ ነው ።

አለብወኒ ፡ ወአሕይወኒ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ሕግህን ፡ ግለጽልኝ ፤ ከመከራ ፡ አድነኝ ።

ክፍል፡፲፱ ፤ ቆፍ ፡ ብሂል ፡ ቅሩብ ፡ እግዚአብሔር ።

ቆፍ ፡ ማለት ፡ ቅሩብ ፡ እግዚአብሔር ማለት ፡ ነው ።

፻፸፭ ፤ ጸራኅኩ ፡ በሶሉ ፡ ልብየ ፡ ስምዐኒ ፤ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናዬ ፡ ለምኖለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወኀሠሥኩ ፡ ኮነኒከ ።

ሕግህን ፡ ሻሁ ።

፻፸፮ ፤ ጸራኅኩ ፡ ኀቢከ ፡ ስምዐኒ ፡ ወአድኀነኒ ።

ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለምኖለሁና ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ አድነኝ ።

ወእዕቀብ ፡ ስምዐከ ።

አምልኮትህን ፡ ልጠብቅ ።

፻፸፯ ፤ በጸሐኩ ፡ ማዕከለ ፡ አድባር ፡ ወከላሕኩ ።

በተራሮቹ ፡ መኻል ፡ ደርሼ ፡ ጮህኩ ፡ ማለት ፤ ምነው ፡ ጊዜው ፡ ደርሷል ፡ አታወጡኝምን ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ።

እስመ ፡ ቃልከ ፡ ተሰፈውኩ ።

ሕግህን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌአለሁና ።

፻፸፯ ፡ በጽሑ ፡ አዕይንትየ ፡ ለኀይሥ ።

ዐይኖቼ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመ ገሥገሥ ፡ ደረሱ ፤ ጊዜው፡ ሳይደርስ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሁኖ ፡ ታይቶት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። አንድም ፡ በተስፋ ው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንዳለ ፡ ሁኖ ፡ በጽሑ ፡ አለ ።

ከመ ፡ እንብብ ፡ ቃለከ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ገብቼ ፡ ሕግህን ፡ እነ ግር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፻፸፱ ፡ ስማዕ ፡ እግዚኦ ፡ ቃልየ ፡ በከመ ፡ ሥ ዐ ል ከ ።

አቤቱ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

መአሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ፍትሕከ ።

ፈርደህ ፡ አድነኝ ። አንድም ፡ ፍር ድህን ፡ እንደ ፡ መጠበቂ ፡ አድነኝ ።

፻፸ ፡ ቀርቡ ፡ አለ ፡ ርዱኢ ፡ በዐመፃ ።

በግፍ ፡ የሚጠሉኝ ፡ የከበቡኝ ፡ ጠላ ቶቼ ፡ ባቢሎናውያን ፡ እኔን ፡ ለማ ጥፋት ፡ ወደኔ ፡ ቀረቡ ።

መእምሕግከሰ ፡ ርኅቁ ።

ቀርቡም ፡ ማለቴ ፡ እኔን ፡ ለማጥ ፋት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሕግህ ፡ ግን ፡ ራቁ። አንድም ፡ ኢርሕቁ ፤ እነዚያ ፡ ቢርቁ ፡ እኔ ፡ አልራቅሁም ።

፻፸፩ ፡ ቅሩብ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ቅሩብ ፡ ነህ ።

ወርቱዕ ፡ ኵሉ ፡ ፍናዊከ ።

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ የቀና ፡ ነው ።

፻፸፪ ፡ ምእትካት ፡ አእመርኩ ፡ ስምዐከ።

ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ አምልኮትህን ፡ ዐወቅሁ ።

ከመ ፡ ለዓለም ፡ ሣረርኮን ።

ለዘላለም ፡ አጽንተህ ፡ እንደ ፡ ሠራ ኻቸው ።

ክፍል ፡ ፳ ፡ ሬስ ፡ ብሂል ፡ ርኡስ ፡ እግ ዚአብሔር ።

ሬስ ፡ ማለት ፡ ርኡስ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ቢገኝኝ ፡ ኳራ ፡ ፀሓይ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ አብ ፡ ኳራ ፡ ወልድ ፡ ኳራ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኳራ ፡ እንዲል ፡ አገው ፤ አብ ፡ ፀሓይ ፡ ወልድ ፡ ፀሓይ ፡ መ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀሓይ ፡ ሲል ።

፻፸፫ ፤ ርኢ ፡ ሕማምየ ፡ መአድኅነኒ ።

መከራዬን ፡ አይተህ ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ ኢረሳዕኩ ፡ ሕገከ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ያልከውን ፤ አንድ ም ፡ ሕግህን ፡ አልዘነጋሁምና ።

፻፸፬ ፤ ፍታሕ ፡ ፍትሕየ ፡ ወባልሐኒ ።

ፈርደህ ፡ ከመከራ ፡ አድነኝ ።

ወበእንተ ፡ ቃልከ ፡ አሕይወኒ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡ ስለ ፡ ተናገ ርህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ ስለ ፡ ጠበ ቅህ ፡ አድነኝ ።

፻፸፩ ፡ ርኑቅ ፡ ሕይወትየ ፡ እምኃጥኣን።

አናዋሬ ፡ ከባቢሎናውያን ፡ የራቀ ፡ ነው ። አንድም፡ ርሑቅ ፡ ሕይወት ፡ እምኃጥኣን ፡ ይላል ፤ እግዚኦብ ሔር ፡ ከባቢሎናውያን ፡ የራቀ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ አድሮባቸው ፡ አይኖርም ።

አስመ ፡ ኢኀሠሡ ፡ ሥነኒከ ።

ሕግህን ፡ አልሹምና ።

፻፸፪ ፡ ብዙኅ ፡ ሣህልከ ፡ እግዚኦ፡ፈድፋደ

አቤቱ ፡ ይቅርታህ ፡ ፈጽሞ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

መአሕይወኒ ፡ በከመ ፡ ኵነኔከ ።

ፈርደህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ፡ መጠበቄ ፡ አድነኝ ።

፻፸፫ ፡ ብዙኃን ፡ እለ፡ሮዱኒ፡ወአሠንደቡኒ

የከበቡኝ ፡ መከራ ፡ ያጸኑብኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

መኢተግኃሥኩ ፡ እምስምዕከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ቢበዛ ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብዬ ፡ ከሕግህ ፡ አልራቅሁም ።

፻፸፬ ፡ ርኢኩ ፡ አብዳነ ፡ ወተከዝኩ ።

ባቢሎናውያን ፡ ሕግህን ፡ ሲያፈርስ ፡ አይቼ ፡ አዘንሁ ፡ እንጂ ፤ ኢተግሕሥኩ ።

አስመ ፡ ኢዐቀቡ ፡ ቃለከ ።

ሕግህን ፡ አልጠበቁምና ።

ሐዘ ፡ ፱ ፡ ፬ ። ፪ ፡ ኤጥ ፡ ፪ ፡ ፭ ።

፻፸፭ ፡ ርኢ ፡ ከመ ፡ አፍቀርኩ ፡ ትእዛዘከ

ሕግህን ፡ እንደ ፡ ጠበቅሁ ፡ ዕወቅ ።

እግዚኦ ፡ አሕየወኒ ፡ በሣህልከ ።

አቤቱ ፡ እንደ ፡ ይቅርታህ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ አድነኝ ።

፻፸፮ ፡ ቀዳሚ ፡ ቃልከ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ።

የዘጠኙን ፡ አበጋዝ ፡ ኢታምልክ ፡ ናት ።

ወለዓለም ፡ ኵሉ ፡ ሥነኒከ ፡ ጽድቅ ።

እውነተኛ ፡ የሚሆኑ ፡ ዘጠኙ ፡ ሕግጋትም ፡ ለዘላለም ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ። አንድም፡ለዘላለም፡ጸንተው ፡ የሚኖሩ፡ ዘጠኙ ፡ ሕግጋት፡ ናቸው።

ዘኁል ፡ ኀፈ ፡ ሳን ፡ ብሂል ፡ ሰፋኢ ፡ እግዚኦብሔር ።

ሳን ፡ ማለት ፡ ሰፋኢ ፡ እግዚኦብ ሔር ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ ስቡሕ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ፡ ሰፋኢ ፡ ይህን ፡ ሰፋኢ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ያን ፡ ስቡሕ ።

፻፸፯ ፡ መላእክት ፡ ሰደዱኒ ፡ በእንቲአ ።

መላእክት ፡ ከሀገሬ ፡ አስወጥተው ፡ ሰደዱኝ ፡ ማለት ፤ ባኡ ፡ ከለዳውያን ፡ ወፂውዎሙ ፡ ለዕብራውያን ፡ ብለው ፡ በር ፡ ከፍተው ፡ ቴሃ፡ ቴሃቸውን ፡ አብርተው ፡ አስማረኩኝ ። አንድም ፡ ጎጢአት ፡ ሳልሠራ ፡ ጣዖት ፡ ሳላመልክ ፡ ኤኮን

ያን ፡ ሴደቅያስ ፡ ጎጢአት ፡ ሠር
ተው ፡ ጣዖት ፡ አምልከው ፡ አስ
ማረኩኝ ። አንድም ፡ እለ ፡ ናቡከደ
ነጾር ፡ በግፍዕ ፡ ማረኩኝ ።

ወአምኃልከ ፡ ደንገፀኒ ፡ ልብየ ።

በነቢያት ፡ በካህናት ፡ አድረህ ፡
ፂዋዊ ፡ ይደረጋል ፡ ከማለትህ ፡ የተ
ነሣ ፡ ልቡናዬ ፡ ደነገፀብኝ ። አን
ድም ፡ በአሕዛብ ፡ አድረህ ፡ ተማ
ረክ ፡ ተማረክ ፡ ከማለትህ ፡ የተ
ነሣ ፡ ልቡናዬ ፡ ተሸበረብኝ ።

ጀኀጊ ፡ ወበቃልከ ፡ ተፈሣሕኩ ።

ኋላ ፡ ግን ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ብለህ ፡
በተናገርከው ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

ከመ ፡ ዘረከበ ፡ ምሕርካ ፡ ብዙኀ ።

ብዙ ፡ ምርኮ ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ፡
ደስ ፡ አለኝ ።

ጀኀጊ ፡ ዐመሃ ፡ ጸላዕኩ ፡ ወአስቈረርኩ ።

የዐመፅን ፡ ሥራ ፡ ማለት ፡ ጣዖትን ፡
ጎጢአትን ፡ ጸላሁ ፤ ተጸየፍሁ ።

ወሕግከሰ ፡ አፍቀርኩ ።

ሕግህን ፡ ግን ፡ ወደድሁ ።

ጀኀጊ ፡ ሰብዐ ፡ ለዕለትየ ፡ አሴብሖከ ።

ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ቀን ፡
ሰባት ፡ ጊዜ ፡ አመሰግንሃለሁ ። አን
ድም ፡ ሰብዓ ፡ ይላል ፡ ሳታነሣ ፡
ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ ፡ ቀን ፡
ሰባት ፡ ጊዜዋን ፡ አመሰግንሃለሁ ።

በእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ጽድቅከ ።

እውነተኛው ፡ ሕግህ ፡ ተገዙ፡ ብሎ፡
ስላዘዘ ።

ጀኀጊ ፡ ሰላም ፡ ብዙኀ ፡ ለአለ ፡ ያፈቅሩ
ስ መ ክ ።

ስምህን ፡ መጽራት ፡ ለሚወዱ ፡
ለነቢያት ፡ ለካህናት ፤ አንድም ፡
ለሁሉ ፡ ብዙ ፡ አንድነት ፡ ፍቅር ፡
አላቸው ። አንድም ፡ ይደረግላቸ
ዋል ፤ ይደረግላቸው ።

ወአልቦሙ ፡ ዕቅፍት ።

መከራ ፡ ዕቅፍተ ፡ ሥጋ ፡ ዕቅፍተ ፡
ነፍስ፡ የለባቸውም፤ አይኑርባቸው ።

ጀኀጊ ፡ ተሰፈውኩ ፡ አድኅኖተከ ፡ እግዚኦ

አቤቱ ፡ ትድግናህን ፡ ተስፋ ፡ አደ
ረግሁ ።

ወዐቀብኩ ፡ ትእዛዘከ ።

ሕግህንም ፡ ጠበቅሁ ።

ጀኀጊ ፡ ዐቀበት ፡ ነፍስየ ፡ ስምዐከ ።

ሰውነቴ ፤ አንድም ፡ ልቡናዬ ፡ አ
ምልኮትህን ፡ ጠበቀች ።

ወአፍቀረቶ ፡ ፈድፋደ ።

ፈጽማ ፡ ወደደችው ።

ጀኀጊ ፡ ዐቀብኩ ፡ ትእዛዘከ ፡ ወስምዐከ

ዘጠኙን ፡ ቃላት ፡ ኢታምልክንም ፡
ጠበቅሁ ።

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ፍናውየ ፡ ቅድሜከ፡ እግዚኦ

ሥራዬም ፡ ሁሉ ፡ ከፊትህ ፡ ነው ፡
ማለት ፤ ወነበቦ ፡ ወነበቦ ፡ ያለው

ም ፡ ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፤ እጠብቀዋለሁ ።

ክፍል ፡ ፳፪ ፤ ታው ፡ ብሂል ፡ ትጉህ ፡ እግዚአ'ብሔር ።

ታው ፡ ማለት ፡ ትጉህ ፡ እግዚአ ብሔር ማለት ፡ ነው ፤ ቢገናኝ ፡ ሰታው ፡ እግዚእ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ሴቴ ፡ ማረማ ፡ እንዲል ፡ ዐረብ ፡ እግዝእት ፡ ሲል ።

፻፷፱ ፡ ለትቅረብ ፡ ስእለትየ ፡ ጎዚክ ፡ እ ግ ዚ አ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድረስ ።

መበከመ ፡ ቃልከ ፡ አለብወኒ ።

ወሰብዓ ፡ ዓም፡ ብለህ፡ እንደ፡ ተናገርህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ ዕውቀት ፡ ግለጽልኝ ።

፻፸ ፡ ትብጸሐ ፡ አስተብቍዖትየ ፡ ቅድሜከ ፡ እ ግ ዚ አ ።

አቤቱ ፡ ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድረስ ።

መበከመ ፡ ቃልከ ፡ አድጎንኒ ።

ወሰብዓ፡ ዓም፡ ብለህ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ፤ አንድም ፡ ሕግህን ፡ እንደ ፡ መጠበቄ ፡ አድነኝ ።

፻፸፩ ፡ ጕሥዐ ፡ ከናፍርየ ፡ ስብሐቲከ ።

አንደበቴ ፡ ሕግህን ፤ አንድም ፡ ጌትነትህን ፡ ተናገረ ።

አስሙ ፡ ምህርከኒ ፡ ዚኣከ ።

ሐግህን ፡ ገልጸህልኛል ፡ አስተምረኸኛልና ።

፻፸፪ ፡ ነበበ ፡ ልሳንየ ፡ ቃለከ ።

አንደበቴ ፡ ሕግህን ፡ ተናገረ ።

አስሙ ፡ ጽድቅ ፡ ዚሉ ፡ ትእዛዝከ ።

ሕግህ ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ ነውና ።

፻፸፫ ፡ ይኩነኒ ፡ የማንከ ፡ ከመ፡ ያድኅንኒ

ሥልጣንህ ፡ ያድነኝ ፡ ዘንድ ፡ የሚያድነኝ ፡ ይሁን ።

አስሙ ፡ ትእዛዘከ ፡ አፍቀርኩ ።

ሕግህን ፡ ወድጃለሁና ።

፻፸፬ ፡ አፍቀርኩ ፡ አድኅኖተከ ፡ እግዚኦ

አቤቱ ፡ ትድግናህን ፡ ወደድሁ ።

ወሕግከሰ ፡ ተምህርየ ፡ ውእቱ ።

ሕግህም፡ መምሬ ፡ ትምርቴ ፡ ነው ።

፻፸፭ ፡ ትሕየኒ ፡ ነፍስየ ፡ ወእሰብሐክ

ሰውነቴ ፡ ከመከራ ፡ ትዳንልኝ ፤ እኔም ፡ ከመከራ ፡ ያዳነኝ ፡ ብዬ ፡ አመሰግንሃለሁ ።

ወይርድአኒ ፡ ኵነኔ ፡ ዚአከ ።

ሕግህም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ይርዳኝ ።

፻፸፮ ፡ ተረሣዕኩ ፡ ከመ ፡ ብግዕ፡ዘተገድፈ

እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ ተዘነጋሁ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከተመረረ ፡ በግ ፡ ከበረረ ፡ እንዲሉ ። አንድም ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ በግ ፡ ኮንሁ ፡ ማለት ፤ ከማኅበረ ፡ መላእክት ፡ ተለየሁ ።

ጎሥም ፡ ለጉብርከ ፡ አስመ ፡ ትእዛዛቲከ ፡ አረሳዕኩ ።

ሕግህን ፡ አልዘነጋሁምና ፡ እኔን ፡ ባሪያህን ፡ ፈልገኝ ፡ ማለት ፤ ከባ ቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አውጣኝ ። አንድም ፡ ቃልህን ፡ አልዘነጋሁምና ፡ ከሲኦል ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አውጣኝ ፡ ይላል ፡ አዳም ።

መዝሙር ፡ ፻፲፱ ።

፩ ፡ ጎቤከ ፡ እግዚኦ ፡ ጸራሕኩ ፡ ኦቤ ፡ ተመንደብኩ ፡ መሰማዕከኒ ።

በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተና ግሮታል ፤ እግዚኦ ፡ ጎቤከ ፡ ጸራ ሕኩ ፡ ሲል ፡ ነው ። አቤቱ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በጎልያድ ፡ ጊዜ ፡ ልመ ናዬን ፡ ሰምተኸኛልና ፡ አሁንም ፡ መከራ ፡ ባገኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመንሁ ።

፪ ፡ እግዚኦ ፡ አድኅና ፡ ለነፍስየ ፡ አምኀ ኀፍረ ፡ ዐመፃ ።

አቤቱ ፡ በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ ከሚናገሩ ፡ ከሰራዊቱ ፡ አድነኝ ።

ወአምልሳን ፡ ጽልሑት ።

በአንደበቱ ፡ ክዳትን ፡ ተንኰልን ፡ ከሚናገር ፡ ከሳኦልም ፡ አድነን ።

፫ ፡ ምንተ ፡ ይሁበከ ፡ ወምንተ ፡ ይዌስ ኩከ ፡ በእንተ ፡ ከናፍረ ፡ ጕሎት ።

ሳኦል ፡ በከዳተኛ ፡ አንደበት ፡ ስለ ፡ ተናገርህ ፡ ፍትፈቱ ፡ ርትዑ ፡ ሥላ ሴ ፡ ምን ፡ ይሰጡሃል ፤ መንግሥ ሥቱን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰጥተውሃል ።

፬ ፡ አሕላዑ ፡ ለጎያል ፡ ስሑል ።

አሕጻ ፡ ካለ ፡ ስሑላን ፡ ስሑል ፡ ካለ ፡ ሐጽ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፤ ልማደ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ነው ። የጎያል ፡ ወልድ ፡ አ ሕጻ ፡ መዓቱ ፡ የጋሉ ፡ የተቡ ፡ ና ቸው ።

ከመ ፡ አፍሐመ ፡ ሐቅል ።

እንደ ፡ በረሓ ፡ ቋያ ፡ ነው ፡ ማለት ፤ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የቀረኝ ፡ በዚህ ፡ ይጥፋበት ።

፭ ፡ ሰዶ ፡ ልየ ፡ ዘርኅቀ ፡ ማኅደርየ ።

ማደሪያዬ ፡ ለራቀ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ። አንድም ፡ ለዘርሕቁ ፡ እማኅደርየ ፡ ይላል ፤ ከማደሪያዬ ፡ ለራቅሁ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ፡ ወዮታ ፡ አለብኝ ፤ ወዮ ፡ ሊሉልኝ ፡ ይገባል ።

ወኀደርኩ ፡ ውስተ ፡ አዕጻዳተ ፡ ጌዳ ር ።

በዘላን ፡ ቤት ፡ ላደርሁ ፤ አንድም ፡ ውስተ ፡ አዕጻዳት ፡ ይላል ፤ እንደ ፡ ዘላን ፡ ለሆንሁ ፡ ለኔ ፡ ወዮልኝ ። ዘላን ፡ ነቀል ፡ ተክል ፡ ነው ፤ ካደ ረበት ፡ አይውልም ፡ ከዋለበት ፡